**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2015-08

# þÿ è ¢ , { ` Ó ¨ c ` - ` ó & 3 È ( ò

þÿ ` 5 • s è , s ð 0

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/15075

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

ፎክሎር (ባህል ጥናት)ትምህርት ክፍል

ድሕረ ምረቃ መርሃ ግብር


# "የኢሬቻ በዓል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ"

ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ሟሟያ የቀረበ ጥናት


በ ስንታየሁ ታደሰ



ጥር፣2015ዓ.ም

ባሕር ዳር

# “የኢሬቻ በዓል አከባበርበሎዶ ሄጦሳ ወረዳ”

## በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## በሂዩማኒቲ ፋኩልቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል

በ ስንታየሁ ታደሰ

አማካሪ፡ ሞገስ ሚካኤል (ዶ/ር)

ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥር፣2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር

# በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# በሂዩማኒቲ ፋኩልቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል

# የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# “የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ”

**ስንታየሁ ታደሰ**

**የፈታኝ ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ሞገስ ሚካኤል (ዶ/ር) | ------------ |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| ዋልተንጉስ መኮንን (ዶ/ር) | ----------- |
| የውጪ ፈታኝ | |
| ብርሃኑ አሰፋ (ዶ/ር) | ----------- |

# ማረጋገጫ

“የኢሬቻ በዓል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ” በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በሌላ አጥኚዎች ያልተሰራ መሆኑን እንደሚከተለው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ ስንታየሁ ታደሰ

ፊርማ

ቀን

# ምስጋና

በመጀመሪያ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን እንድማር የነጻ ትምህርት እድል ላመቻቸልኝ ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ከርዕሰ ጉዳይ መረጣ ጀምሮ ጥናቴን እስካጠናቅቅ ድረስ አቅጣጫ በማሳየትና ማስተካከያዎችን በመስጠት ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ ላገዙኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ሞገስ ሚካኤል ምስጋናየ ከልብ ነው፡፡ ዶክተር ትልቅ ምኞቴ የነበረው ሁለተኛ ዲግሪዬን ባንተ መማር ነበር ያለህን እውተኛ እውቀት ካንተ አሳልፌህ ስላስጨበጥከኝ ምስጋናይ ከልብ ነው፡፡ ይህን ትምህርት ለመማር ባሰብኩበት ወቅት በዩኒቨርሲቲው የነጻ ትምህርት እድል መውጣቱን መረጃ በማቀበልና  እንድማር በማበረታታት ለረዳኝ ለዶ/ር ተመስገን በየነ የላቀ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስልኝ ዶክተር ይህ ሁሉ ያንተ ጥረት ውጤት ነውና ፈጣሪ ውለታህን ይክፈልልኝ፡፡ ጥናቱን በምሰራበት ወቅት የጥናቱን ቦታ ካርታ በመስራት ለተባበረኝ ጓደኛዬ የGIS የሁለተኛ ዲድሪ ተማሪ ለሆነው እዩኤል አሰማህኝ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: በመስክ ስራ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ ስሄድ አብረሽኝ በመሄድ በርድና ዝናቡን በመቻል አብረሽኝ ብዙ ለፍተሽል እና እግዚአብሄር የልፋትሽን ዋጋ ይክፈልልኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል በመስክ ቆይታ ወቅት በፈቃደኛነት መረጃውን በመስጠት ለተባበራችሁኝና ስራዬ ከግብ እንዲደርስ የምጠይቃችሁን መረጃ ሳትሰለቹ ለሰጣችሁኝ መረጃ አቀባዮቼ ምስጋናየ ይድረስ፡፡ በተለይ ለአቶ ተሾመ በቀለ፣ለአቶ በቀለ ታደሰ እና ለአቶ ከተማ በቀለ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ስለወረዳው አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ መረጃ ለሰጣችሁኝ የሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች ከልቤ አመሰግናችዋለሁ፡፡ በመጨረሻም ይህን ትምህርት እንድማር ከጎኔ በመሆንና በማበረታታት እንዲሁም በገንዘብ እርዳታ በማድረግ ላበረታታችሁኝ እናቴ ወ/ሮ ሸዋዬ ስዩም፣ ወንድሜ ግዛው ታደሰ እህቴ ሃና ታደሰ እና በላይ ታደሰ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፈጣሪ የልባችሁን ሀሳብ ያሳካልኝ፡፡

# ሙዳዬ ቃላት

| የኦሮሚፋ ቃላት | የኦሮሚፋ ቃላት አነባበባቸው | ትርጉማቸው |
|---|---|---|
| Qanfaa | ቀንፋ | ሴቶች በሚወልቁበት ጊዜ በግንባራቸው የሚያደርጉት የክብር ጌጥ ነው፡፡ |
| Gudifaachaa | ጉደፈቻ | ልጅ ያሌላቸው ብዙ ልጆች ካላቸው ወስደው እንደራሳቸው ልጆች ለማሳደግ የሚወስዱበት ስርአት ነው፡፡ |
| Sinqee | ሲነቄ | እናቶች የሚይዟት ቀጭን ዘንግ |
| ababboo birraa | አባቦ ቢራ | አደይ አበባ(በመስከረም ወር የሚበቅል ቢጫ አበባ) |
| Hayichii | ሃይቻ | አዋቂ |
| Gommii | ጎሚ | ቂም |
| Korboo | ኮረቦ | ክብ ነገር በመሬት ላይ የሚንከባለል |
| Sadiqqaa | ሰዲቃ | ገበጣ(መሬት ላይ ጉድጓድ በማጎድጎድ ጠጠር ሞልተው የሚጫወቱበት) |
| Wadarroo | ወደሮ | ገመድ |
| Garmamaa fardaa | ገርማማ ፈርዳ | የፈረስ ጉግስ |
| Calee xubuqoo | ጨሌ ጡቡቆ | እናቶች ጨሌያቸውን ፈጫሳ በሚሉበት ወቅት ብቻ የሚለበስ ልብስ |
| Ciincaa | ጪንጫ | ለመስዋዕትነት የሚጠበስ ስጋ |
| Kalachaa | ከለቻ | ከሰማይ የወረደ መብረቅ በእርቅ ጊዜ የሚወጣና እሱ ባለበት ምንም አይነት ወሸት የማይዋሸና እውነትን ማውጫ ነው እንዲሁም ቃል መግቢያ ነው፡፡ |
| Caaccuu | ጫጩ | ከጊደር ቆዳ የሚሰራ በእርቅ ጊዜ ከከለቻ ጋር የሚያዝ የሴቶች የክብር ልብስ |
| Bokkuu | ቦኩ | አባ ገዳዎች የሚይዙት የክብራቸው መገለጫ የሆነ ዱላ ነው፡፡ |
| Alngee | አለንጌ | አለንጋ (ከጉማሬ ቆዳ የሚሰራ) |
| Margaa kichuu | መርጋ ኪቹ | እርጥብ ቀንበጥ ሳር |
| naxalaa kula | ነጠላ ኩላ | ጥቁር ወይም ነጭ ጥለት ያለው ነጠላ |
| Okole | ኦኮሌ | ማለቢያ |
| Jaarsuma | ጃርሱማ | ሽምግልና |
| darbanaa ebboo | ደርበና ኤቦ | ጦር ውርዋሮ |
| Dorgomi figicho | ዶርጎሚ ፊጊቾ | የሩጫ ውድድር |
| daammoti kormaa | ዳሞቲ ኮርማ | ሌሊት የቀንደ ከብቶች ወደግጦሽሲወጡ አባ ወራው የሚለኩሰው ችቦ፡፡ |
| Facaasa | ፈጫሳ | እናቶች አቴቴ (ጨሌ) ቂንጬ በማዘጋጀት የሚያከብሩበት ጨሌዋን ቅቤ እየቀቡ የሚያከብሩት ነው፡፡ |

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ማረጋገጫ ..... i

ምስጋና ..... ii

ሙዳዬ ቃላት ..... iii

ማውጫ ..... iv

አጠቃሎ ..... vii

ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 6

1.3. የጥናቱ አላማ ..... 7

1.3.1 የጥናቱ ዐብይ አላማ ..... 7

3.3.2. የጥናቱ ንኡስ አላማዎች ..... 7

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 8

1.5. የጥናቱ ወሰን ..... 9

ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ..... 10

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 10

2.1.1. ከሚከበሩበት ቦታና ወቅት አንጻር ..... 10

2.1.2. በጸደይ ወቅት በወንዝ ዳር የሚከወኑ ከበራዎች ..... 11

2.1.3. በበልግ ወቅት በዛፍ ስር የሚከወኑ ከበራዎች ..... 15

2.1.4. በበልግና በመኸር ወቅት በተራራ ላይ የሚከበሩ ስርአተ ከበራዎች ..... 19

2.2.1. የስርዓተ ከበራ ምንነት ..... 20

2.2.2. እምነት እና ስርአተ ከበራ ..... 24

2.2.3. የስርአተ ከበራ አይነቶች ..... 26

2.2.4. የስርዓተ ከበራ ባህርያት ..... 28

2.2.5. የስርዓተ ከበራ አላባውያን ..... 29

2.2.6. የስርዓተ ከበራ መሰረቶች ..... 31

2.2.7. ስርአተ ከበራ እና ክዋኔ ..... 31

2.2.8. የስርዓተ ከበራ ጠቀሜታ ..... 33

2.2.9. የኢሬቻ ምንነት ..... 35

2.3. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ..... 36

2.3.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ (performance theory) ... 36
2.3.2. ስነ ትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብ (Semiotics theory) ... 38
2.3.3. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functionalism theory) ... 41
ምራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ስነ-ዘዴና የመስክ ተሞክሮ ... 43
3.1 የጥናቱ ስነ ዘዴ ... 43
3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ... 43
3.2.1 የተጠኝ ቦታ አመራረጥ ... 43
3.2.2. የመረጃ አቀባይ አመራረጥ ... 44
3.3. ካልዓይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አሰባሰብ ... 45
3.3.1. ካልዓይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ... 45
3.3.2. ቀዳማይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ... 45
3.3.2.1. ምልከታ ... 46
3.3.2.2. ቃለ-መጠይቅ ... 49
3.3.2.3.ተተኳሪ ቡድን ውይይት ... 49
3.4. የጥናቱ መረጃ አተናተንና አተረጓጎም ዘዴ ... 50
3.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ... 51
3.6. የመስክ ተሞክሮ ... 53
ምእራፍ አራት፤ ጥናቱ የሚደረግበት አከባቢ መልካ ምድራዊና ማህበረ ባህላዊ ገጽታ ... 56
4.1. ካርታዎች ... 56
4.2.የሎዴ ሂጦሳ ወረዳ አጠቃላይ ዳራ ... 56
4.2.1. የወረዳው አጭር መግለጫ፣ አየር ጠባይ፣ መልክዐ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ... 56
4.2.2. የህዝብ ሁኔታ፣ቋንቋና ሀይማኖት ... 58
4.4. የወረዳው መልካም ባህላዊ እሴቶች ... 60
4.4.1. ሰላምን ከማረጋገጥ አንጻር ያሉ መልካም እሴቶች ... 60
4.5. የዝምድና መፍጠሪያ መንገዶች ... 63
በአከባቢው ማህበረሰብ የተያዩ የዝምድና መፍጠሪያ ስርአቶች ሲኖሩ እነዚህም ስርአቶች ባብዘኛው ታዋቂ የሆኑት ጉዲፈቻ፣ ጋብቻ ፣ክርስትና ጡት መጣባትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡63
ምዕራፍ አምስት፤ የመረጃ ትንተናና ትርጓሜ ... 68
5.1. በዶኒ አድባር የኢሬቻ ስርአተ ከበራ አጀማመርና የአድባሩ ስያሜ፡፡ ... 68
5.2. የኢሬቻ በዓል አከባበር በሎዴ ሂጦሳ ወረዳ ... 71
5.2.1. ለኢሬቻው ስርአተ ከበራ የሚከናወኑ ቅድመ ዝግጅቶች ... 71

5.3. የጊዜ ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ........ 75
5.3.1. የኢሬቻ ስርአት አከዋወን ........ 79
5.3.1.1. ለኢሬቻው ስርአት ሳርና አበባ አመራረጥና ኢሬቻ አቀራረብ ........ 85
5.3.1.2. ፈረሰኞች በኢሬቻው ስርአት ላይ ያላቸው ተሳትፎ ........ 87
5.3.1. የመስዋዕት አቀራረብ ........ 87
5.3.3. ለዶኒ አድባር የሚቀርቡ ስእለቶች ........ 91
5.3.5. ለኢሬቻው ስርአት ከበራ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ምግብ ........ 92
5.3.3. የወጣቶች ጨዋታ ........ 93
5.3.5.1. በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚካሄዱ ባህላዊ ውድድሮች ........ 99
5.4. የድህረ ኢሬቻ ስርአተ ክዋኔ ........ 104
5.5. በሎዴሄጦሳ ወረዳ የሚካሄደው የኢሬቻ በአል አከባበር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ 106
5.5.1.ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ........ 106
5.5.2 ማህበራዊ ጠቀሜታ ........ 108
5.5.3. ስነ-ልቡናዊ ጠቀሜታ ........ 109
5.5.4. ስነ-ምግባራዊ ጠቀሜታ ........ 110
ምእራፍ ስድስት፤ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ ........ 112
6.1. ማጠቃለያ ........ 112
6.2. የይሁንታ ሃሳብ ........ 115
ዋቢዎች ........ 117
አባሪ ........ 121
አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ግላዊ ዳራ ........ 121
አባሪ ሁለት ፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች ........ 122
አባሪ ሶስት፡- በስርአተ ከበራውና በመረጃ ማሰባሰቢያ ወቅት የተነሱ ምስሎች፡፡ ........ 122
አባሪ 4. ጥናቱ በቦታው መከናወኑን የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡ ........ 125

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት"የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው፡፡ የጥናቱ አቢይ አላማ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረውን የኢሬቻ ስርአተ ከበራ መግለጽ እና የከበራውን ፋይዳዎች ማሳየት የሚል አላማ የያዘ ሲሆን ይህንንም ከግብ ለማድረስ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች በቃለ-መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃዎቹም ይዘት ግልጽ እንዲሆን በክዋኔያዊ፣ በስነ ትእምርት እና በተግባራዊ ቲወሪ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ የተጠኚ ቦታ እና መረጃ አቀባዮችን በአላማ ተኮርና በጠቋሚ የናሙና ስልት በመምረጥ መረጃዎቹን ሰብስቧል እነዚህም መረጃዎችም በክዋኔያዊ፣ ስነ ትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ተዳሰው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከአርሲ ኦሮሞዎች በፊት በአከባቢው ይኖሩ የነበሩት ሀዲያዎች መሆናቸውና አርሲ ኦሮሞዎች ባከባቢው መኖር ሲጀምሩ ድርቅ በመከሰቱ አቶ መንጃ ቦቄና ዲዶ ገዳ የሚባሉ ሁለት አባቶች በቦታው ነጭ ግመልና ዳለቻ ኮርማ በሬ አርደው ፈጣሪን በመለመን ዝናብ አግኝተዋል በዚህም የተነሳ ቦታው ከክፉ ማእበል እንዳዳናቸው በማሰብ መርከብ (donii) በማለት ሰይመውታል፡፡ ስርአቱም በአመት አንድ ጊዜ መስከረም 17 ቀን እዲከበር በመወሰናቸው በቦታው ሀይማኖት፣ ብሄርና ጾታ ሳይል በየአመቱ በዚሁ ቀን የማህበረሰቡን ባህል በሚያሳዩ ጭፈራዎችና እስፖርቶች ታጅቦ በድምቀት ይከበራል፡፡ በዚህ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚቀርቡ የሰርዶ ሳርና አዴ አበባ ማስቀመጥ የመስዋእት ከብት ማረድ እንዲሁም የተለያዩ ዘፈኖች የሚቀርቡት ፈጣሪ በቸርነቱ ወቅቶችን እንዲያፈራርቅ፣ ልጆች፣ ከብቶችና የተዘራውን አዝመራ ጠብቆ እንዲያኖራቸው የሚያቀርቡት የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡ ወጣቶች የአከባቢውን ባህል ይዘው እንዲያድጉ ፎልዎች በተለያዩ ዘፈኖቻቸው በማስጠንቀቅና አልፎም "ሲገባ" ሲገኝ በመቅጣት ባህል ያስጠብቃሉ፡፡ ልጃገረዶች ለዘመን መለወጫ አበባ አየሾይ በመጨፈር ያገኙትን ገንዘብ ከረሜላ ገዝተው በመግዛት በኢሬጫው ቀን ይከፋፈላሉ በዚህ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የመመረቅ ኀላፊነት ያላቸው ጥንት ስርአተ ከበራውን ያስጀመሩ አባቶች የመንጃ ቦቄና የዲዶ ገዳ ዘር የሆነ ሰው ሲሆን በሶስተኝት የባልቻ ያደቴ ዘር ሰው ነው፡፡በዚህም ስርአት ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርቡት አዴ አበባና ሰርዶ ሳር ነው፡፡ የመስዋእት እንሰሳት ከብት ነጭ፣ ዳለቻ ወይም ቡሌ ከብት መቅረቡ አንደኛ አድባር የምትወደው መልክ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በተጨማሪም ወቅቱ የሽግግር ወቅት በመሆኑ የሚመጣውን ብርሃናማ ወቅት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለፈጣሪ የሚቀርበው ሰርዶ ሳር ያልተበጣጠሰና ንጹህ የሆነ ነው ይህም የዋቃን ንጽህና የሚያሳይ ሲሆን አደይ አበባው መጪውን የብርሃን ወቅት የሚያሳይና በአበባ ላይ ያለውን አዝመራ ወደ ፍሬ ቀይርልን የሚል መልካም ምኞታቸውን የሚገልጽ ነው በአሁኑ ዋቅት የዲዶ ገዳና የመንጃ ቦቄ ዘር በስርአቱ ላይ ባለመሳተፋቸው እንደ ኦሮሞ ባህል የገላንና የገላን ኮራ ጂዳ ጎሳ አባል የሆነ አባቶች ስርአቱን በምርቃት ያስጀምራሉ፡፡ በኢሬቻው ሰርአተ ከበራም የሚከወኑት ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች የማህበረሰቡን ሰላምና ጤና ለመጠበቅ ለቤት እንሰሳቶቻቸው ደህንነትና መራባት፣አዝመራውን ከተፈጥሯዊ አደጋ ክስተቶች ለመታደግ እና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ማህበረ ባህላዊ ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡*

# ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ

ይህ ጥናት የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጣሳ ወረዳ በሚል ርእስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን፤ በምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማ፣ ጠቀሜታ እና ወሰን ያካተተ ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ከተመረጠው የጥናት ርዕስ ጋር በይዘት የሚቀራረቡ ጥናቶች በሚከበሩበት ወቅት፣ ጊዜና ቦታ ተዳሰው ቀርበዋል፡፡ በዚህም በፀደይ ወቅት በወንዝ ዳር የሚከወኑ ከበራዎች፤ በበልግ ወቅት በዛፍ ስር የሚከወኑ ከበራዎችና በበልግና በመኸር ወቅት በተራራ ላይ የሚከወኑ በማለት በርእስ ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን የሚገልጹ ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች የቀረቡ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት የመስክ ተሞክሮ ምን እንደሚመስል እና ጥናቱ የተከተለውን የአጠናን ዘዴ በተመለከተ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና የመተንተኛ ሞዴሎች እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበውበታል፡፡ በምዕራፍ አራት ደግሞ ጥናቱ ስለተካሄደበት አካባቢ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣መልክዓ ምድር ኢኮኖሚያዊ ሁኔታና ባህላዊ እሴት በተወሰነ መልኩ ገለጻ የቀረበበት ሲሆን በምዕራፍ አምስት በመረጃ መሰብሰቢያ አማካይነት የተገኙ መረጃዎችን ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ከጽንሰ ሃሳቦችና ከመተንተኛ ትውሮች ጋር በማመሳከር ትንተና የተሰጠበት ክፍል ሲሆን በተጨማሪ ጥናቱ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ፣ ስነ-ልቡናዊ ጠቀሜታና ስነ-ምግባራዊ ጠቀሜታ በውስጡ አካቶ የያዘ ጥናት ነው፡፡ በምራፍ ስድስት ማጠቃለያ፣ አባሪዎችና የይሁንታ ሀሳብ ተካተው የቀረቡበት ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ከሚያጋጥመው ከባድ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ለመዳን እና በተፈጥሮ የሚያገኛቸውን መልካም ነገሮች ለማስቀጠል የበላይ አካል ለሚለው ፈጣሪው ወይም ልእለ ሰብ በአመቱስጣ ወቅቶችን እየጠበቀ ለፈጣሪው ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ ለበደለው ምህረትን ለመጠየቅ ፈጣሪም ቸርነቱ በክፉ ነገር ሳይቀጣው ጠብቆ ከዘመን ወደ ዘመን ስላሻጋገረውና ላጋጠመው መልካም በረከት ምስጋና የሚያቀርብበት የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን ይፈጽማል፡፡ በከበራዎቹም አማካይነት የበላይ አካል ከሚለው ሃይል የራሱንና የዘሩን ህልውና እንዲጠበቅለት ለፈጣሪው በከበራው አማካይኝት ላለፈው ቸርነቱ ምስጋናውን ለወደፊቱም መልካም ምኞቱን በምስጋናው ያስጠብቃል፡፡ በሎዴ

ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ማህበረሰቡ አርሶ አደር እና ከፊል አርሶ አደር በመሆኑ ከወቅቶች መፈራረቅ ጋር በማያያዝ የክረምቱን ጭጋጋማ ወር በሰላም ማለፋንና ወደ ብርሐናማው ወቅት በሰላም መሽጋገራቸውን በማስመልከት ለዋቃ (ለአንድ ፈጣሪ) የሚያቀርቡት የምስጋና ኢሬቻ ነው፡፡ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የማህበረሰቡን ጥንታዊና ነባር ባህል እንዲሁም ማህበራዊ አደረጃጀት የሚገልጽ በመሆኑ ቢጠናና በዶክመንት መልክ ቢቀመጥ በአሁን ወቅት የሚገኘውን የማህበረሰቡን ወግና ልማድ ለቀጣይ ትውልድ በማስተላለፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ የሰው ልጅ በሚኖርበት አከባቢ ሁሉ የከበራው አይነት ይብዛም ይነስ የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን በማከናወን ህልውናቸውን ያስጠብቃሉ፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢርቻ ስርአተ ከበራ ባከባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ተቀባይነት ያለውና ማህበረሰቡም በየዓመቱ መስከረም አስራ ሰባትን እየጠበቀ በድምቀት የሚያከብረው የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡ ይህ ስርአተ ከበራ የአከባቢውን ማህበረሰቡን ባህል፣ ጥንታዊ ማንነት፣ የመተዳደሪያ ኢኮኖሚና የአኗኗር ሁኔታ የሚያሳይ የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡

Sims and Stephens (2011፡103) በርካታ የከበራ ስርአቶች መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ስርአቶችን አጣምረው የሚይዙና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ውስብስብ የሆኑ የእምነት ስርአት እና ማህበራዊ ህይወት ይገልጻሉ በማለት ያብራራሉ፡፡ ከዚህም አንጻር በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚከናወኑ ዓለማዊና መንፈሳዊ ስርአቶች የማህበረሰቡን ነባርና የዳበረ ባህሉን መግለጽ የሚችሉ በመሆናቸው ስርአተ ከበራዎችና ያከናውናሉ፡፡ የኢሬቻ ስርአትም ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሰው ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡

በየወቅቱ የሚከበሩ ስርአተ ከበራዎች ከሚከበሩበት ወቅት እና ይዘት በመነሳት በተለያዩ ክፍሎች ይመደባሉ በማለት Bell (1997፣94) የስርአተ ከበራ አይነቶች ብላ በስድስት ከከፈለቻቸው መካከል የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የመሸጋገሪያ ከበራ (Rites of Passage) እና ቀነ ቀመራዊ ከበራ (Calendrical Rites) ስርአት ስር የሚመደብ ነው፡፡ የሰው ልጅ በሚኖርበት አከባቢ ቀናትን በመቁጠርና በምክንያት በመምረጥ የተለያዩ የአምልኮ ስርአቶችን በቤትና በአምልኮ መፈጸሚያ ስፍራዎች ያከብራሉ፡፡ በዚህም አማካኝነት ስርአተ ከበራዎች የተለያየ ይዘት እና አይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ Sims and Stephens (2005፡ 94-95)

Rituals are associated with birth, puberty, marrage, death and rituals establish their own entry to or exit from different parts of life or group experience. Because they are sometimes so ceremonial, rituals are often filled with customes. Folklorists study rituals. Because their complexity and dramatic qualities make them dense with meaning.They are significant exprations of agroup traditions, beliefs, values, and identity.

በማለት ሲገልጹ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የተለያዩ ስርአተ ከበራዎች እንደ ሆኑ እና ስርአቶቹም ሲከወኑ የከዋኛቸውን ማህበረሰብ ባህል ፣እምነት፣እሴት፣ ማንነት እና የዘራቸውን አመጣጥ በከበራው አማካይነት ያሳያሉ እንዲሁም ለቀጣይ ትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡ ይህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ማህበረሰቡ በአመት አንድ ጊዜ በዶኒ አድባር ስር በመውጣት ላለፈው ቸርነቱ ምስጋና በማቅረብ መጪውንም ጊዜ በቸርነቱ እንዲጠብቃቸው የሚለማመኑበትና ምስጋናቸውን የሚያቀርቡበት ስርአት ሲሆን ይህም ስርአተ ከበራ ከነ Sims የከበራ አመዳደብ ጋር የሚካተት ነው፡፡

Jones and Legare (2016፣43) (McElreath, Boyd, &Richerson, 2003፡127) በመጥቀስ የአምልኮ ሥርዓት ከበራዎች በቡድን የተመሰረቱ፣ በማህበራዊ ደረጃ የተደነገጉ በመሆናቸው፣ ተመሳሳይነትን የሚያሳዩ ውጤታማ መንገዶች ናቸው፡፡ ግለሰቦች በተደነገገው ስርአት ውስጥ ተባባሪዎችን እንዲወስኑ ያስችላቸዋል። ግለሰቦች ተመሳሳይ እምነቶችን እና እሴቶችን የሚጋሩ ታማኝ አድራጊዎች የመሆን እድላቸው ሰፊ መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶችን ይሰጣሉ። ተሳታፊውን በተፈቀዱ ስርአቶች እንዲወያዩ ከመፍቀዱም በላይ መልካም የሚያስቡና ጥሩ የሆኑ ሰዎችን መለየትና መምረጥ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

Watson-Jones and Legare (2016፡43) (Chudek & Henrich, 2011)

> ስርአተ ከበራዎች በአንድ ማህበረሰብ ውሰጥ የተለመዱ ችግሮችን ይፈታሉ፡፡ ይህም (ሀ) የቡድን አባላትን መለየት፣ (ለ) ለቡድን እሴቶች ያላቸውን ቁርጠኝነት ማሳየት፣ (ሐ) ከማህበራዊ ጥምረቶች ጋር ትብብርን ማመቻቸት እና (መ) የማህበራዊ ቡድን ትስስርን በማሳደግ ከቡድን ጋር ተያይዘው የሚመጡ መላመዶች ችግሮችን እንዲፈቱ የማድረግ ሃይል አላቸው።

ስርአተ ከበራዎች ማህበረሰብን በቡድን በማደራጀት በቡድኑ ውስጥ ያለው ማህበረሰብ በመወያየት ለችግሩ መፍትሄ እንዲሰጥ ይረዳል፡፡ በመቀራረብ እና በመወያየት ደግሞ መልካም እሴት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የአከባቢው ማህበረሰብ የአከባቢውን መልካም እሴት እንዲጠብቁ የማድረግና ማህበረሰቡን እርስ በርስ የማቀራረብ፣ የማደራጀትና የማስተሳሰር ሃይል ያለው ስርአተ ከበራ በመሆኑም ከዚህ ሃሳብ ጋር ተደጻጻፊነት አለው፡፡

በየአከባቢው የሚከወኑ ስርአተ ከበራዎች ያንያክል ለአንባቢያን በጥናት ተደራሽ ሆነዋል ተብሎ መውሰድ ባይቻልም ማህበረሰቡ የሚያከናውናቸው ስርአተ ከበራዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ከነዚህም ምሁራን መካከል sims and Stephen (2o11፡101) "እምነታቸውን እና እሴቶቻቸውን የሚገልጹ የአምልኮ ሥርዓቶች  በመተግበር የቡድኑን አባላት በማነሳሳት ስርአቱ በደነገጋቸው መርሆች እንዲኖሩ በማድረግ እሴቱን አክብሮ የሚይዝ እና የሚጠብቅ ጠንካራ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላሉ በማለት ይገልጻሉ"፡፡ ስርአተ ከበራዎች በሚከበሩበት ወቅት ማህበረሰቡ ያለውን ጠንካራ እሴት፣ ባህል እና አመለካከት ለትውልድ በማስተማር ባህሉንና እሴቱን የሚጠብቅ ትውልድ ይፈጥራል፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የሚያመለክተን ማህበረሰቡ በረጅም ጊዜ ውስጥ ህልውናውን ለማስጠበቅ ሲል ከረጀም ዘመን በፊት ጀምሮ ሲያከብረው የነበረ የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡

Sims and Stephen (2005፡95) (Myerhoff 1977) በመጥቀስ "ስርዓተ ከበራ ሰዎች በተከታታይና በተደጋጋሚ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በቡድን ተደራጅተው መዋቅራዊ በሆነ መልኩ የሚከውኑት ወይም የሚተገብሩት፣ ለቡድኑ ትርጉም ያለው፣ መልዕክት የሚያስተላልፉ በትና የሚያከብሩት ልማድ ነው"፡፡ ሲሉ ይገልጻሉ እንደዚህ ሃሳብ ገለጻ ስርአተ ከበራዎች ለአከባሪው ማህበረሰብ ቡድን እንዲመሰርት እና በስርአቱም መግባባት እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የምስጋናው ኢሬቻ ስርአተ ከበራ የአከባቢውን ማህበረሰብ ባህል እና እሴት እንዲሁም ማህበረሰቡ ለአለም ያለውን አመለካከትና የአኗኗር ዘዬ ለመረዳት የሚያስችል ምስጋናዊ ስርአተ ከበራ ነው፡፡

Sims and Stephes (2o11፡99) "ስርዓተ ከበራዎች በአንድም ሆነ በሌላ ከክዋኔ ጋር ተያይዘው የሚገለጹ ሲሆን በተለያዩ ዝግጅቶች በተደጋጋሚ የሚከወኑ ለከዋኛቸውም የራሳቸው የሆነ ውክልና ትዕምርታዊ አገልግሎት የተለያየ ጠቀሜታ የሚሰጡ እንደሆነ

ገልጸዋል"፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ በሚከበረው በምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ አማካኝነት ማህበረሰቡ ለዘመናት ያዳበረውን እሴትና ባህል መለየት የሚያስችል ስርአት በመሆኑ ይህ ስርአተ ከበራ ማህበረሰብን ከማህበረሰብ በማስተሳሰር በቀጣይነትም ትውልዱ ባህሉን እንዲጠብቅ የሚያደርገው በምንድነው የሚለውን ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡

Thomas (1944፡259) "periodic celebration representing through traditional observances, performances, rituals, and games the world view of a culture or social group Virtually universal, festival may be the most complex social and symbolic event to persist in tradition" ወቅታዊ ከበራዎች ብዙን ጊዜ ትኩረታቸው በስርአተ ክዋኔው ላይ በሚተላለፉት ስርአተ አምልኮ እና በባህላዊ ጨወታዎች አማካይነት ማህበረሰቡ ለዓለም ያለውን አመለካከትና ፍልስፍና የሚያሳዩ ስርአቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በኢሬቻው ክብረ በአል አማካይነት የማኅበረሰቡን ጥንታዊ አምልኮ ስርአት አፈጻጸም እና በአከባቢው ሲኖር ለአምልኮ ስርአት ማስፈጸሚያ የሚጠቀምባቸው ቁሶች ያላቸውን ተቀባይነት ከአከባቢው ኢኮኖሚ እና የአየር ንብረት አንጻር ማኅበረሰቡ የሚያከብረው ስርአተ ከበራ ለአለም ያለውን አመለካከት የሚያስረዳ ሲሆን በስርአቱ ላይም የዘሩን አመጣጥ ምንዓይነት ውጣ ውረድ አሳልፎ ህልውናውን አስጠብቆ እዚህ እንደ ደረሰ በባህላዊ ጨወታዎች አማካነት እንዴት መግለጽ ይችላሉ የሚለውን በዚህ ስርአተ ከበራ ለማወቅ ይቻላል፡፡

Jones and Legare (2016፡42) Whitehouse & Lanman, 2014) Durkheims (1915)ን በመጥቀስ "ተመሳሳይ ዘር ባለው ማህበረሰብ መካከል የሚካሄድ ስርአተ ከበራ የቡድኑን ትስስር በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይጠቅሳል"፡፡ ከዚህም አንጻር ይህ የምስጋና ኢሬቻ ስርአት የተለያየ ዘር እና ሃይማኖት ባላቸው ማህበረሰቦች መካከል ቢካሄድም በቋንቋ እና ባከባቢ እንዲሁም በኢኮኖሚ ተመሳሳይ በመሆናቸው ማህበረሰቡን ከማጠናከርና ከማስተሳሰር አንጻር ያለውን አስተዋጽኦ ለመረዳት የJones እና Legare ጽንሰ ሃሳብ ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት እንዳጠና ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ሁለት ጉዳዮች አነሳሽ ሲሆኑኝ ከቦታ አንጻር ደግሞ እንዲሁ ሁለት ጉዳዮች ትኩረቴን ስበውኛል፡፡

ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር **አንደኛው፡-** በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የአካባቢውን ማህበረሰብ አገር በቀል እውቀት፣ እሴት እና አጠቃላይ የማህበረሰቡ ልማድ በስርአተ ከበራው ክዋኔ እንዴት ይገለጻል የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በጥናቱ መመለስና ማመላከት ካለኝ ጽኑ ፍላጎት የሚሉት አነሳሽ ምክንያት ሲሆኑ ከዚህም አንጻር አብዛኛው የአከባቢው ማህበረሰብ ከስርአቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑትን ባህላዊ የፈረስ ጉግስ፣ የሩጫ፣ የጦር ወርውሮ፣ የገበጣና የገመድ ጉተታ ጨዋታዎች በጉጉት መጠበቃቸው ከምን አንጻር ነው የሚለው ሃሳቤን ገዝተውኛል፡፡

**ሁለተኛው** በኢሬቻ ስርአተ ከበራ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በማይበት ጊዜ በሁለት ወቅቶች (በጸደይ ወራት/በውሃማ ስፍራዎች/ እና በበልግ ወቅት/ በጋራ) የሚከወኑ ጥናቶች በማየቴና ከእነዚህ ውጪ በአድባር ስር የሚከበር መሆኑን ማመላከት እንዳለብኝ ስላሰብኩ ሲሆን በዚህም ዙሪያ ካነበብኳቸው ጥናቶች መካከል ጥሩነህ ሬቡማ፤ በ2011 ዓ/ም `The cultural significance of Irreechaa at melkaa ateetee`በሚል ርእስ የቀረበ ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ የሚካሄደውን የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ማሳየት ነው፡፡ የሚል አላማ መነሻአድርጎ የተሰራ ጥናት፤ ዳምጠው በንቲ በ2011ዓ/ም የኢሬቻ በአል ስርአተ ከበራ በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ፣በሚል ርእስ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ይዘት የኢሬቻን ስርአት እና ባህላዊ እሴቶቹን በአጠቃላይ በኦሮሞ ህዝብ እና በተለይም በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ማሳያነት ያለውን የኢሬቻ ስርአት መመርመር እና መተንተን ነው የሚል አላማ ያለው ሲሆን በተጨማሪም Leykun (2014) “Irreecha” Ceremony among Shoa Oromo በሚል ርእስ የቀረበ መጽሄት ሲሆን የጥናቱ አላማ በሆራ አርሰዴ እና በሆራ ቢሲል የሚካሄዱትን የኢሬቻ ስነ ሥርዓቶች በንጽጽራዊ ጥናት ያቀረበ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ጥናቶች ኢሬቻ በመልካ እና ጋራ ላይ ብቻ እንደ ሚከበር የሚያሳዩ ሲሆኑ በዚህ ዙሪያ ያለውን የእውቀት ውስንነት በማሳየት ኢሬቻ ስርአት በጸደይ ወራት በአድባር ስር እንደሚከበር በተወሰነ መልኩ ያሳውቃል ተብሎ ስለታሰበ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

ከቦታ አንጻር ይህ ጥናት የተካሄደው በምስራቅ አርሲ ዞን በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ በቱሉ የንቦ ቀበሌ በዶኒ አድባር ስር ነው፡፡ ይህ አከባቢ የተመረጠበት ምክኒያት በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ የቆየ ማህበረሰብ በመሆኑና በስርአተ ከበራው ላይ አብዛኛው ማህበረሰብ በምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራው ላይ የሚሳተፉ በመሆናቸው እንዲሁም በሌላ አዲስ መጥ ባህል ያልተበረዘ ስርአት በመሆኑ ጥናቱ በዚህ አካባቢ ቢካሄድ ትክክለኛ እና በቂ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል በመሆኑ ጥናቱን በዚህ አካባቢ ላይ እንዳደርግ ትኩረቴን ስቦታል፡፡

**ሁለተኛው፡-** ርእሱን እንድመርጠው ያነሳሳኝ በአከባቢው ስኖር በተለያዩ ቦታዎች የአድባር፣ የቦረንትቻና የፊጫፊ ስርአትን ምክንያት በማድረግ እንዲሁም አንዳንድ አመት ዝናብ ከሚዘንብበት ወቅት ሲዘገይና ያለወቅቱ ሲዘንብ ማህበረሰቡ በሃይማኖታዊ ቦታዎች እንዲሁም በልማዳዊ አምልኮ መፈጸሚያ ቦታዎች እንደ አድባር፣ መልካ፣ ጋራ(ጎራ) እና በቤት ውስጥ የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን ያካሂዳሉ፡፡ በሃማኖታዊ ስርአት ማለትም ለደብረ ታቦር የጅራፍ ግርፍ ጨዋታ፣ ዘመን መለወጫ፣ መስቀል፣ ጥምቀትና አስተሪኦ ማሪያም፣ የኢርቻ ክብረ በአላትን ምክንያት በማድረግ ማህበረሰቡ በስፋት በመውጣት ስርአቱን በፈረስ ጉግስ/ግልቢያ ጨዋታ ያጅባል፡፡ እነዚህ ሃይማኖታዊ እና ልማዳዊ ስርአቶች ባከባቢው በስፋት ጎልተውና ወቅታቸውን ጠብቀው መከበራቸው በአከባቢው የሚኖረው ማህበረሰብ የዳበረ ሃይማኖታዊ እና ልማዳዊ ስርአትን የሚያከናውን መሆኑ ያላቸውን ባህላዊ ልምድ ለማውቅ ካለኝ ፍላጎት በመነሳት በምስጋናው ኢሬቻ ስርአተ ከበራ አማካይነት ለመመርመር ስል ጥናት አድርጌያለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉት አብይና ንኡስ አላማዎች አሉት፡፡

### 1.3.1 የጥናቱ ዐብይ አላማ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚከበረውን የኢሬቻ በአል አከባበር መመርመርና ማሳየት ነው፡፡

### 3.3.2. የጥናቱ ንኡስ አላማዎች

- የኢሬቻውን ክዋኔ መግለጽ፤
- የኢሬቻውን የተለየ ባሕርይ ማሳወቅ፤
- በክብረ በአሉ ወቅት የሚታዩ ትእምርቶችን መፈከር፤

- የክብረ በዓሉን ፋይዳዎች ማብራራት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ ለአንባቢያን፣ ባህና እስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም ለተለያዩ ተቋማትን በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል እነዚህም ጠቀሜታዎች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በዚህ ወቅት ያለውን የኢሬቻ ስርአተ ከበራ በጥናቱ ቀርሶ በማስከመጥ በባህልና ቱሪዝም አማካይነት ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡
- የህግ አካልት ይህን ጥናት በማየት ያከባቢው ማህበረሰብ ያለውን አብሮነት እና የመደጋገፍ ባህል በስርአተ ከበራው ላይ በሚያሳዩት አብሮ የመኖር የመተጋገዝና የመተባበር እሴት በመረዳት ባከባቢው ያሉ የህግ አካላት በቀላሉ ከማህበረሰቡጋር በመግባባት አካባቢውን ለማስተዳደር እና ለማልማት ያስችላቸዋል በተጨማሪም ይህን ያከባቢውን መልካም እሴት በመውሰድ እንደ ሃገር የወረዳዋን የመቻቻል እሴት በመጥቀስ የህግ አካላት አስተዳደራዊ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ በተወሰነ መልኩ ሊረዳ ችላል፡፡
- ይህ ጥናት በአከባቢው ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ለሚፈልጉ ግለሰቦች እና ተቋማት ስለ አከባቢው ማህበረሰብ አኗኗር፤ እምነት፤ ያመጋገብ ስርአት፤ ስለ አከባቢው ኢኮኖሚ ሁኔታ እና …ወዘተ የመሳሰሉ ጉዳዮችን በተወሰነ መልኩ መረጃ በመስጠት አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይታሰባል፡፡
- ይህ ጥናት በድህረ ገጽና በመጻህፍት ቤት በመቀመጥ ለአንባቢያን በሎዴ ሄጦሳ ወራዳ የሚካሄደውን የኢሬቻ ስርአተ ከበራ እና ያከባቢውን መልካም ገጽታ ላንባቢያን በማስተዋወቅ ጎብኚዎች ወደ አካባቢው እንዲሄዱ አስተዋጽኦ ያበረክታል በዚህም ባከባቢው ያሉ የትራንስፖርት ሰጪ አካላት ሆቶል ቤቶች እና ነጋዴዎች ከዘርፉ ተጠቃሚ በማድረግ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ሊያነቃቃ ይችላል፡፡
- የኢሬቻው ስርአት ዘር፣ሀይማኖት ሳይለይ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የሚሳተፍበት በመሆኑ ለማህበራዊ ሰላምና አንድነት ያለውን ፋይዳ ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ስርአቱ እንደማጣቀሻ ቢጠቀመው የትምህርት ዘርፉን በተወሰነ መልኩ መደገፍ ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ካሉ ንኡስ ክፍሎች  በከበራና በክብረ በዓላት ላይ ሆኖ ወቅትን ጠብቀው ከሚከበሩ ከበራዎች ውስጥ በኢሬቻ በዓል አከባበር ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህ የተወሰነበት ምክንያት የአከባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ስርዓተ ከበራዎችን የሚከውን ሲሆን ወቅትን ጠብቀው ከዘመን ወደ ዘመን ከወቅት ወደ ወቅት በሰላም ላሻጋገረው ፈጣሪ ላለፈው ቸርነቱ ምስጋና እንዲሁም ወደፊት በቸርነቱ እንዲጠብቃቸው ጸሎትና ልመና ለማቅረብ የፈጣሪ መንፈስ ያድርባቸዋል በሚባሉ አድባር ፣መልካ እና በጎራ(ጋራ) እንዲሁም በሃማኖታዊ ቦታዎች ላይ የተለያዩ የአምልኮ ስርአቶችን ይፈጽማሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት  መስከረም አስራ ሰባት ቀን በዶኒ አድባር ስር በሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ ብቻ ነው፡፡

ከቦታ አንጻር ይህ ጥናት የተካሄደው በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ ካሉ 22 ቀበሌዎች መካከል በቱሉ የንቦ፣ በፉርሳ፣ በጉዴለቻ እና በወረዳው ዋና ከተማ በሁሩታ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በነዚህ ቀበሌዎች የተወሰነበት ምክንያት ቀበሌዎቹ ለዶኒ አድባር ባላቸው ቀረቤታ እና በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ አብዛኛው ነዋሪዎች የስርአተ ከበራው ተሳታፊዎች በመሆናቸው ጥናቱ በነዚህ ቀበሌዎች ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ርእስ ስር ከለአይ መረጃዎች ከቤተ መጻህፍት፣ ከድረገጽ ከመዛግብቶች፣ከመጽሄቶች ፣ ከጋዜጦች እና ወዘተ... በመፈተሽ ለዚህ ጥናት ማጠናከሪያ (መረጃ ጠቋሚ) የሆኑ ሃሳቦች ከየሰነዶች ተፈትሸው ቀርበውበታል፡፡

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በወረዳው በተደረገ ፍተሻ ከዚህ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው ምርማሮች ባይገኙም በተለያዩ ቦታዎች በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በተደረገ ፍተሻ ሁለት ጥናቶች ከፎክሎር ትምህርት ክፍል እንዲሁም ከኦሮሚፋ ፎክሎር ትምህርት ክፍል አንድ፣ ጥናትና ከአንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል አንድ ከኦሮሚፋ ትምህርት ክፍል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በእንግሊዘኛ ትምህርት ክፍል በአንቦ ዩኒቨርሲቲ የተሰራ መጽሄትእና ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንድ ከፎክሎር ትምህርት ክፍል ተዳሰው የቀረቡ ሲሆን እነዚህም ጥናቶች ከሌሎች በተለየ የተመረጡበት መስፈርት በተመለከተ በስርዓተ ከበራ ላይ የተካሄዱ ከመሆናቸውም ባሻገር ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ከሌሎች ጥናቶች በተሻለ ሁኔታ ተዛማጅነት ስላላቸው ነው፡፡

### 2.1.1. ከሚከበሩበት ቦታና ወቅት አንጻር

የሰው ላጅ በሂዎት ዘመኑ የበላይ አካል ከሚለው አምላኩ ጋር የሚገናኝባቸው የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን ያከናውናል በነዚህ ስርአተ ከበራዎች ፈጣሪው በበረከት እንዲባርከው፣ ጥናውን እኒሰጠውና ልጆቹን በጥና ጠብቆ እንዲያሳድግለት ፈጣሪውን ይለምናል ይማጸናል እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉለትም ፈጣሪውን በተለያየ ወቅትና ቦታዎች በግልና በቡድን በመሆን ያመሰግናል፡፡ የኢሬቻ ስርአተከበራም በተለያዩ ወቅትና ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች የሚከበሩ ሲሆን ከነዚህ ከተለያዩ ቦታዎችና ጊዜ አንጻር ደግመሞ ይህ የኔ ጥናት በጸደይወቅት በአድባር ስር የሚቀርብ የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡ በዚህም ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው ጥናቶች በጸደይ ወቅት በወንዝ ዳር የሚከወኑ ከበራዎች፣በበልግ ወቅት በዛፍ ስር የሚከወኑ ከበራዎች፣ በበልግና በመኸር ወቅት በተራራ ላይ የሚከበሩ ስርአተ ከበራዎች ፣ በበልግ ወቅት በዛፍ ስር የሚከወኑ ከበራዎች እናበበልግና በመኸር ወቅት በተራራ ላይ የሚከበ ሩ ስርአተ ከበራዎችን በመምረጥ ተዳሰውን ተመርምረው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.2. በጸደይ ወቅት በወንዝ ዳር የሚከወኑ ከበራዎች

በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡ ጥናቶች ከቦታ አንጻር በወንዝ እና ከወቅት አንጻር ደግሞ በጸደይ  የሚከወኑ ስርአተ ከበራዎችን መሰረት አድርገው የተጠኑ ናቸው፡፡

Leykun (2014)፡- “Irreecha” Ceremony among Shoa Oromo በሚል ርእስ Jornal of science and sustainable development (jssd) ambo university collej of social sciences and humanities department of English and literature ላይ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በሆራ አርሰዴ እና በሆራ ቢሲል የሚካሄዱትን የኢሬቻ ስነ ስርት በንጽጽራዊ ጥናት ያቀረበ ነው፡፡

ኢሬቻን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውሉትን ደረጃዎች መለየት እና መመዝገብ፤ ማህበራዊ ባህርይን የሚመሩ ባህላዊ ህጎችን እና ደንቦችን መለየት፡፡ የሚሉ ሁለት አላማ የያዘ ሲሆን

በዚህ ስርአት ላይ በሆራ ቢሲል እና በሆራ አርሰዴ በሁለቱም ቦታ በአካል በመገኘት ከዋዜማው እስከ ፍጻሜው ያለውን ስርአት በመከታተል በስርአቱ ላይ ያሉትን ህጻናት፣ ልጃገረዶች፣ ወጣቶች ፣እናቶች፣ ሽማሌዎች፣ ቃሉዎች፣ አባ ገዳዎች ያላቸውን ድርሻ በምልከታ በቃለ መይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ሰብስቧል በዚህም ሂደት በሆራ ቢሲል እና በሮራ አርሰዴ ያለው ስርአት ተመሳሳይ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

በሁለቱ ቦታዎች ያሉ ልዩነቶች በሆራቢሲል ሀይቅ በዋዜማው በመውጣት ትናንሽ ልጃገረዶችና ወጣቶች በኦዳስር በመውጣት የሚዘፍኑ ሲሆን ቃሉዎች በቦታው በመገኘት በኦዳው ስር የተለያዩ ጭሶችን ሲያጫጭሱና ዛፉን ቅቤ ሲቀቡ ይታያሉ ወጣት ልጃገረዶችም የቃሉ መንፈስ ያለባቸውን ለመርዳት ሲረባረቡ ይታያል አባገዳዎችም የተሰበሰቡትን ይመርቃሉ በመጨረሻም አባ ገዳዎቹ በወጣቶች ታጅበው ወደቤት ይሸኛሉ፡፡

በእለቱም ልጅ አዋቂ  ወንድ ሴት ሳይል ባንድነት ወደ መልካ/ወንዝ በመሄድ ሳር እና አበባ በመልካው እየነከሩ ፊታቸው ላይ በመርጨት ለዋቃ ጸልየው ሲረጩ መሬሆ በማለት ይዘፍናሉ አዋቂዎች ኮርማ በማረድ መስዋእት ሲያቀርቡና የመጣውንም እንግዳ በመጋበዝ ስርአቱን ያከብራሉ፡፡ ይህ ስርአት በተመሳሳይ ሁኔታ በሆራ አርሰዴም የሚፈጸም ቢሆንም ነገር ግን በሆራ አርሰዴ ልጃገረዶች ቃሉዎችን ለማገልጋል ሲረባረቡ እንደማይታይ እና አባገዳዎች በዋዜማው በቦታው ተገኝተው ህዝቡን እንደ ማይመርቁ በጥናቱ ጠቁሟል፡፡

የጥናቱ ጠንካራ ጎን፦ ሁለቱንም ቦታዎች በማነጻጸር በስርአት ቅደምተከተላቸውን በመጠበቅ ያቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ድክመት ቃሉዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ከበሬታ እና በስርአቱ ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ አልገለጸም እንዲሁም ከአባገዳዎች ጋር እኩል ተሰልፈው ስርአቱን የሚያከናውኑ ሀዳ ሲንቄዎችን ተግባር አልጠቀመም፡፡

ከኔ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎእና ልዩነት ሁለቱም ጥናቶች ሁለቱም ጥናቶች በከበራስር የሚገኙታቸው እና በኢሬቻ ስርአተ ከበራ ክዋኔ ላይ ማተኮራቸው ሲያመሳስላቸው፡፡ ልዩነት ከቦታ አንጻር የኔ ጥናት በምስራቅ አርሲ ዞን በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን የሱ ጥናት በሆራ አርሰዴ እና በሆራቢሲል የሚካሄድ ነው፡፡ የኔ ጥናት በአድባር ስር የሚከወን ሲሆን የሱ በሆራ(በሀይቅ) ላይ የሚካሄድ ስርአት መሆኑ እንዲሁም የሱ በአጠቃላይ ከእምነቱ ላይ ብቻ ሲያተኩር የኔ ጥናት በስርአቱ ላይ ከእምነቱ ውጪ ስርአቱን ለማድመቅ የሚከናወኑ ባህላዊ ጨዋታዎች ያካተተ ስርአት በመሆኑ ጥናቶቹን ያለያያቸዋል፡፡

**ጥሩነህ ሬቡማ (2011)፦** Tiruneh Rebuma (2o11) the Cultural Significance of Irreechaa at Malkaa Ateetee School of Graduate Studies in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Social Anthropology Addis Ababa University የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ የኢሬቻ ስርአት እና ባህላዊ እሴቶቹን በአጠቃላይ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ምን ይመስላል የሚለውን በተለይም በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ማሳያነት ያለውን የኢሬቻ ስርአት መመርመር እና መተንተን የሚል አላማ የያዘ ነው። የጥናቱ አስፈላጊነት በኦሮሞው ማህበረሰብ መካከል ያለውን ባህላዊ ጠቀሜታ ለማወቅ እና ለመረዳት ያለመ ነው፡፡ በኢሬቻ ስነ ስርአት ላይ ያለውን አወዛጋቢ ጉዳይ ይህም አቴቴ ከስርአቱ ጋር ያለው ግንኙነት በተለይም መልካ አቴቴ ለምን ተባለ? ይህ ጥናት በኢሬቻ የአምልኮ ስርአት እና በስነ ስርአቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳወቅ የሞከረ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ በዋናነት በልዩ ዞኑ በሚኖሩ የቱለማ ኦሮሞዎች በሚያካሂዱት የኢሬቻ ስርአት ላይ ያተኮረ ሲሆን አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች በአላማ ተኮር የተመረጡ ሲሆን እነዚህም በመልካ አቴቴ ዙሪያ በገጠርም በከተማም ካሉ ነዋሪዎች አባ ገዳዎች፣ያገር ሽማግሌዎች እና በባህልናቱሪዝም ቢሮ ካሉ ሰዎች መረጃውን ሰብስቧል፡፡

በጸደይ ወራት የሚቀርብ ኢሬቻ መልካ የሚባለው በአብዛኛው ማህበረሰብ የሚከበር እና በበጋ ወራት የሚከናወን ኢሬቻ ጋራ መሆናቸውን በሁለት በመክፈል ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ሁለቱም ለዋቃ መጸለይ እና ምስጋና የሚያቀርቡበት የኢሬቻ ስርአት እና የአቴቴ ስርዓት ያለውን ግንኙነት አሳይቷል። አቴቴ የሚከናወነው በሴቶች ብቻ ሲሆን ለምነት፣ ለጤንነት እና ለሰላም የሚከበር ሲሆን እንደ ኢሬቻ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከወናል፡፡ አቴቴ እና ኢሬቻ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው፡፡ የኢሬቻ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ህብረተሰቡ በቤቱ የአቴቴውን ስርአት እንደ ሚያከናውኑ ጠቁሟል።

የዚህ ጥናት ግኝት እንደሚያሳየው የኢሬቻ ሥነ ሥርዓት ለተለያዩ ዓላማዎች የሚደረግ መሆኑን ነው። ግኝቱም የሚያሳየው ለጤና፣ ለመራባት፣ ለበረከት፣ የተሻለ ምርት ለማግኘት እና መልካም ዝናብ ለማግኘት፣ በሰዎች እና በተፈጥሮ መካከል መልካም ግንኙነትን ለመፍጠር እና ምስጋና ለአንድ ፈጣሪ ለማቅረብ የሚከበር ስርአት መሆኑን የሚገልጽ ጥናት ሲሆን ስርአቱ ጠንካራ ሀገርን ለመመስረት የሚረዳ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም የኢርቻን ስርአት የሚመለከቱ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህም አብዛኛው ስርአታቸው ተመሳሳይ የአከዋወን ስርአት ያለው ቢሆንም ኢሬቻ ቢራ ወይም በጸደይ ወራት የሚከበረው በአብዛኛው ኦሮሞ ዘንድ በውሃማ አካላት የሚከበር ሲሆን የኔን ጥናት ልዩ የሚያደርገው ውሃ በሌለበት ቦታ በአድባር ዛፍ ስር መከበሩ ነው፡፡ እንዲሁም ሁሉም ማህበረሰብ የሚሳተፍበት መሆኑ ማለትም ሙስሊም እና ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች በጋራ የሚያከብሩት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

**ዳምጠው በንቲ** (2011)፡- የኢሬቻ ባአል ስርአተ ከበራ በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ፡፡ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኦሮሚፋ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ የሚካሄደውን የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ማሳየት የሚል አላማ ይዞ የተነሳ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ትኩረት በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ በሚካሄደው የኢሬቻ በአል አከባበር ላይ ሲሆን ቦታው የሚገኘው በአዲስ አበባ ዙሪያ በኦሮሚያ ልዩ ዞን በሆነችው በሰበታ ከተማ ነው፡፡ ቀዳማይ መረጃዎችን በስርአተ ከበራው ወቅት በመገኘት በምልከታ እንዲሁም በቃለ

መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ከአባ ገዳዎች፣ ካገር ሽማግሌዎች፣ ከሃዳ ሲንቄ እና ከፎሌዎች ሰብስቧል፡፡

በጥናቱም ለኢሬቻ እድገት እንቅፋት የሆኑ በማለት የእስልምና የክርስትና ሓይማኖ መስፋፋት  እንዲሁም ቀደምት ነገስታት ተጽኖ እንደ ሆኑ ጠቁሟል፡፡ በኢሬቻ ከበራ ወቅት ማንኛውም ሰው እንደ ፈለገው ወደ መልካው በመሄድ ኢሬፈና ማካሄድ አይችልም ስርአትና ደንብ ያለው ሲሆን ሁሉም የኢሬቻውን በአል አክባሪ ከአባ ገዳ ቀድሞ ኢሬቻውን ማድረግ እንደማይችል የተገለጸሲሆን በስርአቱ ላይ ሴቶች ከአባ ገዳ ቀድመው መሄድ ይችላሉ፡፡ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ለሴቶች ነጻነት የሚሰጥ መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

ለኢሬቻና የሚመጡ ሰዎች የሚይዟቸውን ቁሶች ከነጠቀሜታቸው የገለጸ ሲሆን ከአለባበስ አንጻር ነጭ በቀይ እና በጥቁር ቀለም የተሰራ ልብስ የሚለበስበት ነው፡፡ አባ ቦኩ(አባ ገዳ የሚይዘው ዱላ)፣አለንጋ፣ ሲንቄ፣ ጨሌ እና የመሳሰሉ እነደ ሆኑ ተጠቁሟል  በተጨማሪም አዴ አበባ(Abaabbo birra) እና እርጥብ ሰርዶ ሳር(marga kichu) ይዘው ወደ ኢሬቻው የሚመጡ ሲሆን አበባው ተስፋን ብርሀንን የሚያሳይ መሆኑን እርጥቡ ሳር ደግሞ የዘርን መስፋፋት እና ቀጣይነትን የሚያሳይ ተምሳሌት እንዳለው ጠቁሟል፡፡

የጥናቱ ግኝት፡- ማንኛውም ሰው ወደ መልካ ለኢሬፈና ሲሄድ የቦታውን ስርአት ጠብቆ የሚገኝ መሆኑን እና በስርአቱም ዘፈን፣ ምርቃት እና የተለያዩ መልእክቶች መኖራቸውን፣ በኢሬፈና ስርአት ላይ የሚሳተፉ አባ ገዳዎች እና ሃዳ ሲንቄዎች እንዲሁም ግለሰቦች የሚይዟቸውን ቁሶች ጠቁሟል፡፡

የዚህ ጥናት ተንካራ ጎን፡- በአዋሽ መልካ ቁንጡሬ የሚካሄደውን የኢሬቻ ስርአት ቅድመ፣ግዜ እና ድህረ ያለውን ስርአት በቅደም ተከተል ገላጭ በሆነ መልኩ ያሳየ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ድክመት፡- አለምገና ከተማ ከሚለው ስያሜ ወደ ሰበታ አዋስ ስያሜ ሲቀየር ያለውን የምክር ቤት ቃለ ጉበኤ ካንድ እስከ አምስት እና ያከባቢውን ማህበረሰብ የዘር አመጣጥ በማለት  ሰፊ ቦታ ሰቶ በጥናት ማካተቱ እንደ ድክመት ተመልክቼዋለሁ፡፡

ተመሳስሎ፡- ሁለቱም ከበራዎች የሚካሄዱት በተመሳሳይ ወቅት ሲሆን ስርአቱን የሚያከብሩ ሰዎች እርጥብ ሳር አበባ እና የተለያዩቁሳቁሶችን በመያዝ በከፊል ያመሳስላቸዋል

ልዩነት፡- የጡሩነህ ጥናት የተጠናው በአዲስ አበባ ዙሪያ ካሉ የኦሮምያ ልዩ ዞኖች መካከል በሰባታ ሲሆን የኔ ጥናት የሚካሄደው በአርሲ ዞን በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ነው፡፡ ከቦታ አንጻር የተለያዩ ሲሆኑ ሌላው የኔ ጥናት መልካ በሌለበት መካሄዱ የተለያዩ ክዋኔዎች እንዲኖሪት ያደርጋል፡፡

### 2.1.3. በበልግ ወቅት በዛፍ ስር የሚከወኑ ከበራዎች

**ከበደ መንገሻ** (2011) "ለአድባር የሚቀርቡ መስዋእቶች ስርአተ ከበራ በደቡብ ምእራብ ሸዋ በቶሌ ወረዳ" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኦሮሚፋ የፎክሎር ትምህረት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙዋያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በደቡብ ምእራብ ሸዋ በቶሌ ወረዳ ያለውን ለአድባር የሚቀርቡ መሰዋዕቶች መግለጽ፡፡ የሚል ዋና አላማ ይዞ የተነሳ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ትኩረት በደቡብ ምእራብ ሸዋ በቶሌ ወረዳ ውስጥ ባሉ የዋቄፈታ እምነት ተከታይ ኦሮሞዎች ዘንድ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ስልትን የተከተለ እና መረጃዎቹንም ከቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ሰብስቧል፡፡ በዚህ ጥናት ገለጻ  አድባር ማለት ትልቅ ዛፍ ጥላ ያለው ማህበረሰቡ ከፈጣሪያቸው ስለ ፍጥረት የሚለማመኑበት ቦታ መሆኑን የግልጻል፡፡

በአድባር ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉት ትላልቅ አባቶች፤ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ልጆች እና ህጻናት ሲሆኑ በስርአቱ ወቅት የሚያስፈልጉ ምግቦች  ገንፎ፣ ቂንጬ፣ ቅቤ፣ ስጋ፣ ኑግ፣ ጠላ፣ ማር፣ወተት እና ቡና መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

ስርአቱንም ለማካሄድ የሚያስፈልጉ እርጥብ ሳር ይህም ሳሩ መራባትን (የዘርን መብዛት) ምሳሌ የሚሰጥ ሲሆን በስርአቱ ላይ የደም መስዋት የሚቀርበው ደም የእርቅ ምሳሌ ስለሆነ እና በዚህም ፈጣሪ ለጥፋታቸው ምህረት እንዲያደርግላቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡ የጨሌ ተምሳሌት ሴቶች በአንገታቸው የሚያደርጉት ጌጥ ሲሆን ይህም በአድባር፣ በቦረንትቻ፣ በአቴቴ ስርአት እና ሴቶች በእርግዝና ወቅት ምጥ ሲይዛቸው በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት

የዚህ ጥናት ግኝት የአድባር ስርአተ ከበራ በፆታ እና በእድሜ እንደማይወሰኑተጠቁሟል፤ በአድባር ከበራውም የተለያዩ ምግብ እና መጠጥ እንደሚዘጋጅ ታውቋል፤ የአድባር ስርአቱም የሚካሄደው ባመቱስጥ በጸደይ ወቅት እና በበልግ ወቅት በግንቦት እና ሰኔ

መግቢያ ላይ ይካሄዳል፤ በአድባር ስርአቱም የተለያዩ ቁሶች ሀይማኖታዊ ተምሳሌት ይዘው እንደ ሚቀርቡ ተጠቁሟል፡፡

**የጥናቱ ጠንካራ ጎን፡-** በስርአቱ ላይ የሚቀርቡትን ክዋኔዎች ባጠቃላይ ከነተምሳሌታቸው ያቀረበ ሲሆን መረጃውም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

**የጥናቱ ድክመት፡-** የሚጠናው በሃገረሰባዊ ልማድ ስር ሲሆን በጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳ ላይ የሚቀርበው ሃሳቡን የሚያጠናክር ሆኖ ሳለ በጥናቱ አብዛኛውን ክፍል የያዘው ስለ ፎክሎር አራት ዘርፎች ምንነት  በመፃፍ በርካታውን ክፍል ማሲያዙ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው፡- ሁለቱም በሃገረሰባዊ ልማድ ስር የሚገኙ ከበራ መሆናቸው እና አድባር ስር መካሄዳቸው መስዋዕት ማቅረባቸው በተመሳሳይነት እርጥብ ሳር በመያዝ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብ የሚለማመኑበት ቦታ እና የተለያዩ ክዋኔዎች የምርቃት ስርአት መካሄዱ ባብዛኛው የሚያመሳስላቸው ነው፡፡

ልዩነት ፡- ከርእሰ ጉይ አንጻር የኔ ጥናት የኢሬቻ ስርአት ሲሆን የከበደ ጥናት የአድባር ከበራ የሚል ነው፡፡ ከቦታ እና ከማህበረሰብ እምነት አንጻር ደግሞ የኔ ጥናት የሚካሄደው በምስራቅ አርሲ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ ሃይማኖት ፣ጎሳ/ ብሄር/ እና ጾታ ሳይለዩ በያመቱ መስከረም አስራ ሰባት በበርካታ ቡድኖች የሚከበር አመታዊ ክብረ በአል ሲሆን የከበደ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ምእራብ ሸዋ በቶሌ ወረዳ ውስጥ በኦሮሞው ማህበረሰብ በዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ዘንድ የተካሄደ መሆኑ ከቦታ፤ ማህበረሰቡ ከሚከተለው ሃይማኖት እና ከሚከበሩበት ቀን አንጻር ይለያያሉ እንዲሁም ስርአቱን ከሚመሩት ሰዎች አንጻር በሱ ጥናት በእድሜያቸው ትልቅ የሆኑ አባቶች እና እናቶች የመለማመን ስርአት እና የመመረቅ ስርአት እንደ ሚያቀርቡ ሲገልጽ በኔ ጥናት ላይ በማህበረሰቡስጥ ታዋቂ የሆኑ አባቶች እና ቃሉዎች ባንድ ላይ በመሆን  ስርአቱን ያከናውናሉ፡፡

**ፀዳለ ታደሰ**(2007)፡- “በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች” በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፤ ለአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወራና ወረዳ ስር በሚገኘው የቀይት ንዑስ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች መነሻቸውን፣ ይዘታቸውን እና

ከበራቸውን በጥልቀት ማሳየት፡፡ የሚል ሲሆን በዚህም ስር በንኡስ ወረዳው ስር ከሚካሄዱ እምነቶች መካከል ጫት መቀቀል፣ ጭዳ፣ አድባር፣ ቦረንትቻ እና አቴቴ/ፊጫሳ/ ናቸው፡፡ መነሻቸው፣ ፋይዳቸው፣ ሀይማኖታዊ ትስስራቸው፣ ከበራቸው እንዲሁም በአካባቢው ማህበረሰብ ለዕምነቶቹ ያለውን አመለካከት በጥናቱስጥ ተዳሰዋል፡፡

በዚህ ጥናት አምስት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የሚከወኑት ራስን፣ ቤተሰብን፣ ንብረትን እንዲሁም ቀዬን ከክፉ ነገሮች ቀድሞ ለመከላከልና ከተከሰቱም ምህረትን ለማግኘት እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ የተገለጸ ሲሆን ማህበረሰቡ እነዚህን ክዋኔዎች በመከወናቸው ከተመላኪዎቹ አካላት ጥበቃን እናገኛለን ብለው ስለሚያምኑ መንፈሳዊ ዕረፍትን እረፍትን እንደ ሚያገኙ ተጠቁሟል፡፡

በጥናቱ የቀረቡትን ሃገረሰባዊ እምነቶች በስርአት የአከዋወን ሂደታቸውን ከነወቅታቸው ለማቅረብ ሞክራለች እንዲሁም ጥናቱ የያንዳዶቹን እምነቶች ስርአት ለየብቻ ተንትኖ ያቀረበ ነው፡፡ በየወሩ ለመስዋዕት የሚቀርቡ የበግ እና ዶሮ ቀለም(መልክ) ለማሳየት የሞከረ ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት በንኡስ ወረዳው የሚከበሩ ሀገረሰባዊ እምነቶች ያሳየ ሲሆን እያንዳዳቸው ስርአቶች የሚከወኑበትን ቦታ ሲከወኑም ከተሳሳቱ የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ለማሳየት መሞከሩ የዚህ ጥናት ጥንካሬው ሲሆን ስርአቱን ከመዘርዘር ይልቅ የሚከወንበትን ቤት በጎላ መልኩ ማቅረቡ ከአላማው ወቷል፡፡

የጥናቱደካማ ጎን፡- ይህ ጥናት "በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች" ብሎ የተነሳ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ርእስ በጣም ሰፊና አንድ ርእሰ ጉዳይን በስፋት መዳሰስ የማይችል ነው በዚህም የተለያዩ አምስት ሃገረሰባዊ እምነቶችን የዳሰሰ ጥናት ሲሆን ስርአተ ከበራዎቹንከማስተዋወቅ በስተቀር በጥልቀት ያልመረመረ ጥናት ነው፡፡ እነዚህም ስርአተ ከበራዎች የሚከበሩት በቤትና ከቤት ውጪ በመሆኑ ከከበራ ቦታቸው የተለያዩ ስርአተ ከበራዎች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስልው፡- ጉዳይ ሁለቱም ጥናቶች በከበራ ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸው፡፡ የኔ ጥናት በአድባር ስር የሚካሄደውን ስርአት ሲመለከት የጸዳለ ጥናት ደግሞ አድባርን ጨምሮ ሌሎች አራት ሃገረሰባዊ እምነቶችን የዳሰሰ ነው፡፡

የጥናቱ ልዩነት የጸዳለ ጥናት የተካሄደው በአማራ ክልል በቀይት ወረዳ ውሥጥ በኦርቶዶክስ እምት ተከታዮች ዘንድ ነው፡፡ የኔ ጥናት ደግሞ በኦርቶዶክስ እና በስልምና ሃማኖት ተከታዮች ዘንድ ያተኮረ ነው፡፡ በተጨማሪም የስርአቶቹ አከዋወን በተለያየ ቦታ እና ግዜ የሚካሄዱ በመሆናቸው ቢለያዩም የተወሰኑ ሃገረሰባዊ እምነቶች በአድባር ስር መከበራቸው ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡

**ኮማንደር ማሃመድ**(2005)፡- "የበሪ ሀገረሰባዊ ዕምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፤ ለአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረት በአሪ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከወነውን የበሪ ዕምነት ከከበራ ፅንሰ ሀሳብ መመርመር ሲሆን በዕምነቱ ስር ያሉትን ባቢዎች፣ ጎድሚዎችና አንጀት አንባቢዎች ያላቸውን ተሳትፎ ያከዋወን ስርአታቸውን እንዲሁም የክዋኔ ጊዜያቸውን ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም በሪ የሴት አምላክ ስትሆን ይችም አምላክ መኖሪያዋ  እንደማይታወቅ በመግለጽ የዝችን አምላክ ህግጋት የሚያስፈጽሙት ባቢ(ባላባት) እና ጎድሚዎች ናቸው፡፡ ባቢዎች የሚመረጡት በዘር ንጹህ ከሆነ ቤተሰብ ሲሆን ስልጣኑም የሚተላለፈው አባት ሲሞት ቀጥታ እድሜው ለደረሰ ወንድ ልጅ ነው፡፡ ወንድ ልጅ ካሌለ ለወንድም ካልሆነም በስጋ ዝምድና ላላቸው ዘመዶቹም ሆነ ላማች ይሰጣል፡፡

ጎድሚዎች ከማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል የሚመረጡ ሲሆን ስልጣናቸው ለታላቅ ልጅ ወንድም ሆነ ሴት የሚተላለፍ ነው፡፡ እንዲሁም  የተለያዩ ጎድሚዎች እንዳሉ የጠቀሰ ሲሆን እነሱም የዝናብ ጎድሚ(ጥሩ ዝናብ እንዲዘንብ የሚለምኑ)፣ የከብት ጎድሚ (ለከብት ጤንነትእና እንዲራቡ የሚለምኑ) የሰው ጎድሚ(ስለሰው ጤንነት የሚለምኑ)፣የሰብልጎድሚ(የተዘራው አዝመራ ጥሩ እንዲያፈራ የሚለምኑ) እና ወዘተ ናቸው ሲል ጠቁሟል፡፡ በዚህ ጥናት ባቢ እና ጎድሚዎች በፈጣሪ (በበሪ) ልዩ ጸጋ የተቸራቸውና በሰውም የተመረጡ እንደሆኑ ይታመናል በመሆኑም እነዚህ ሁለቱም በበሪ እና በሰው መካከል እንደ ድልድይ ሆነው እንደሚያገለግሉ እንዲሁም ዋና ተግባራቸው የህዝቡን ደህንነት መጠበቅ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡

ባቢና ጎድሚዎች የበሪ አገልጋዮች ሲሆኑ እነሱም ከበሪ ጋር በህልም፣በምልክት፣በመንፈስ እየተገናኙ እና መስዋእት እያቀረቡ ህዝቡን መጠበቅ ከበሪ የተሰጣቸውን ጸጋ እና

ከህዝቡም የተረከቡት አደራ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የበሪም ሃገረሰባዊ እምነት የሚፈጸመው በአካ፣ በአድባር እና ማል የሚባሉ ቦታዎች ላይ ሲሆን ለከበራው እንደ ምክኒያትነት ከሚጠቀሱት መካከል ለመኸር አዝመራ የሚያስፈልገው አየር እንዲኖር፣ በሰው ፣በእንሰሳት እና በሰብል ላይ የሚመጣውን ወረርሽኝ ለመከላከል፤ በሚች እና በኗሪው መካከል ያለውን ግንኙነት ለማስተካከል፤የቤተሰብን ንጽህናና የበሪን ክብር ለማስጠበቅ፤ምርትን በበሪ አስባርኮ ለመጠቀም፤እና…ወዘተ ናዎቹ እንደ ሆኑ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ ጥናቱ የሀገረሰባዊ ስርዓተ ክዋኔና የክዋኔ መቼት ከማሳየት ባለፈም የዕምነቶቹን ስነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነምግባራዊ ፋይዳዎች እንዳሉት በጥናቱ አሳይቷል፡፡ ከኔ ጥናት ጋር ያለው ግንኙነት ሁለቱም በሀገረሰባዊ ከበራ ስር የሚገኙ መሆናቸው ነው፡፡ የኩማንደር ማሃመድ ጥናት ከሌሎቹ ቦታዎች በተጨማሪ በአድባር መከበሩ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

### 2.1.4. በበልግና በመኸር ወቅት በተራራ ላይ የሚከበሩ ስርአተ ከበራዎች

**አስቻለው ተስፋዬ** (2014 ዓ.ም)፡- ‹‹የጉዲት አምልኳዊ ስርዓት-ከበራ በመሐል ሳይንት ወረዳ ማህበረሰብ ማሳያነት›› በሚል ርእስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲ ፌኩልቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል ለድሕረ ምረቃ መርሃ ግብር ለፎክሎር ሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሚያነት የቀረበ ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት በጉዲት የእምነት ስርዓት የሚያምኑ የመሀል ሳይንት ወረዳ ማህበረሰቦች በአምልኮ ስርዓተ ከበራው የአከዋወን ሂደት ውስጥ የሚያገኙትን ማህበረ ባህሊዊ ፋይዳ መመርመር የሚል አብይ አላማ ያቀረበ ጥናት ሲሆን በአላማው መሰረት በጉዲት ተራራ ላይ የሚከበረውን የጉዲት አምልኮአዊ ስርአት ለማሳየት የሞከረ ጥናት ነው፡፡ በዚህም የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ማህበረሰቦች በግል ህይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን ውስጣዊ ችግሮች እና የአካባቢ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ራሳቸውን ለመጠበቅና ለመከላከል ሲል በግል እና በቡድን በመሆን ጉዲት ጎራ ላይ የሚከውኗቸውን ቡና ማፍላት፣ የመስዋእት ዶሮ ወይም በግ ማረድ፣ እጣን ማጨስ፣ እርጥብ ሳር መነዝነዝ፣ ድንጋይ ላይ ቅቤ መቀባት፣ ቡና ቁርስ ማዘጋጀት፣ ምርቃት፣ ወድቅዳቂ ቆሻሻን ማቃጠል የሚል አምልኳዊ ስርዓት ክዋኔዎችችን እነደሚያከናውኑ የሚተቁም ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ስልትን የተከተለ ሲሆን መረጃ አቀባዮችን በአላማ ተኮርና በጠቋሚ ናሙና በመምረጥ መረጃዎች በምሌከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡዴን ተኮር ውይይት

ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በክዋኔያዊ፣ በተግባራዊ እና ስነልቡናዊ ትውሮች አማካይነት ተዳሰው በገለጻና በይዘት የቀረበ ጥናት ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡

የጉዲት አምልኮታዊ ስርዓተ ከበራ የተጀመረበት ዘመን በውል አለመታወቁን በመጥቀስ የአከባቢው ማህበረሰብ ከአያት ቅማቶቻቸው ተቀብለው የሚከውኑት የእምነት ስርዓት እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ የጉዲት ስአተ ከበራ ከንግስት ዮዲት የንግስና ከ8ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአምልኮ ስርዓተ ከበራ እንደሚፈጸምበት የጠቆመ ሲሆን ማህበረሰቡም በህይወቱ ዙሪያ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ቀድሞ ለመከላከል ሲደርሱበትም ለማስወገድ የራሱ የሆነ የመከወኛ ወቅትና ጊዜ ለይቶ በማስቀመጥ ስርዓተ ከበራ እንደሚከውኑገልጧል፡፡

በአምልኳዊ ስርዓተ ከበራውም የሚከወኑት ልማዲዊ ድርጊቶች የማህበረሰቡን ሰላም ለማስጠበቅ ፣ለህጻናት እና ለቤት እንሰሳት ጤና እንዲሁም መራባት፣ለአዝመራ መባረክ እና ከተፈጥሯዊ ክስተቶች ቀድመው የሚከውኑት የተማጽኖና የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡ በስርዓተ ከበራው የሚከወኑ ልማዶች ሁሉ ለጉዱት መንፈስ የልመና እና ምስጋና ማቅረቢያ በመሆን ግለሰባዊና ቤተሰባዊ ህይወትን የመጠበቅና የማጠናከር ማህበረ ባህሊዊ ፋይዳ እንደሚያሰገኙ ጠቁሟል፡፡ ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም በከበራና ክብረ በአል ስር የሚገኙ መሆናቸው ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የበላይ አካል ለሚሉት ልእለ ሰብ ምስጋና የሚያቀርብ ስርአተ ከበራ ማቅረባቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ **ልዩነት፡-** የአስቻለው ጥናት ለራስ ለልጆችና ለቤት እንሰሳት ጤና እንዲሁም ለአዝመራ መባረክ የሚቀርብ የልመና ና ተማጽኖ ስርአተ ከበራ ሲሆን የኔ ጥናት ለራስ ለልጆችና ለቤት እንሰሳትን ጤና ጠብቆ አዝመራውን ባረኮ ከወቅት ወደ ወቅት ላሸጋገራቸው ፈጣሪ የሚቀርብ የምስጋና ስርአተ ከበራ በመሆኑ ያለያያቸዋል፡፡

### 2.2.1. የስርዓተ ከበራ ምንነት

ስርአተ ከበራ ማለት በአንድ ሰው ወይም በርካታ ሰዎች በቡድን በመሰባሰብ ባንድ በተወሰነ ቦታ የሚያከብሩት ስርአት ነው፡፡ ማህበረሰቡም በሚያከብረው ስርአተ ከበራ አንዳች ጥቅም እንደሚያገኙ በማመን ሲሆን ስርአተ ከበራዎች የሚከበሩበት ወይም የሚከወኑበት ጊዜና ቦታ አላቸው፡፡ ስርአተ ከበራ ማህበረሰቡ በጋራ በመሆን ባንድ በተወሰነ ቦታ አንድን ጉዳይ ታሳቢ በማድረግ የሚያከብረው (የሚያከናውነው) የልመና፣ የአደጋ ጊዜ ወይም የምስጋና ስርአት ነው፡፡ ደስታ (1962፣737) ከበራ “ሰዎች በአንድ ላይ በመሆን የሚያከብሩት የከበራ አይነት ወይም አንድን ጉዳይ በማሰብ የሚያሳልፉበት ቀን

ነው፡፡” በማለት ሲገልጹ በተጨማሪም የበዓል ክብር፣ ገናን፣ ጥምቀትን፣ ትንሳኤን፣ ጰራቅሊጦስን፣ መስቀልን ለመሰለ በአል የሚደረግ ማህሌት ዘፈን ንግስ እልልታ እና ደስታ ነው፡፡ በማለት ሲገልጹ እነዚህ ስርአተ ከበራዎች ወቅትን ጠብቀው በአመት አንድ ጊዜ የሚከበሩ ናቸው፡፡ ከዚህም አንጻር የኢረቻ ስርአተ ከበራ በአመት ሁለት ጊዜ በበጋና በፀደይ ወቅት ቢከበርም ይህ ጥናት የቀረበው ወቅቱን ጠብቆ በጸደይ ወቅት የሚከበረው የምስጋና ኢርቻ ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ደስታ በዚሁ ገጽ ላይ ስራ አለመስራት መንገድ አለመሄድ ነው፡፡ በማለት የገለጹ ሲሆን “ከበራ” ማለት ደግሞ ስራ ተወ በአል አደረገ ማለት ነው ሲሉ ደስታ (1962፣736) ላይ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የምስጋና ኢሬቻው ስርአት ላይ የሚከናወን ዘፈን፣ እልልታ እና ደስታና ፈንጠዝያ ባጠቃላይ ከወቅት ወደ ወቅት ላሰተላለፈ ፈጣሪ የሚደረግ ምስጋና ነው፡፡ ይህ የምስጋና ስርአተ ከበራ ማህበረሰቡን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ከስራ ውጭ በአሉን በማሰብ የሚውሉበት በመሆኑ ከደስታሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡

የኢሬቻ ስርአተ ከበራ በአመት ሁለት ጊዜ ወቅትን ጠብቀው የሚከበሩ የምሰጋናና የተማጽኖ ስርአተ ከበራ ሲሆኑ ወቅትን ጠብቀው የሚከበሩ ከበራዎችን አስመልክተው የኢትዮጵያ ቋንቋች ጥናትና ምርምር ያማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣375) ክብረ በአል ለሚለው በየአመቱ የሚከበር ትልቅ መንፈሳዊ በአል በማለት ይፈቱታል፡፡ የዚህ መዝገበ ቃል ሃ ሳብም ከሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡ ስርአተ ከበራዎች ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ እና ማህበረሰቡ ወቅቱን እየጠ በቀ በተደጋጋሚ የሚያከብራቸው ስርአተ ከበራ ነው ናቸው፡፡

ከነዚህ ከሁለቱ ሃሳቦች የምንረዳው በአል ማለት ማህበረሰቡ እለቱን በማሰብ ስለ በአሉ የተለያዩ ስርአቶችን በማከናወን የሚያሳልፍበት ስርአት መሆኑን ነው፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአት ከበራ ማህበረሰቡ ባጠቃላይ የእድሜ እና የጾታ ገደብ ሳይኖር በአንድነት በዓመት አንድ ጊዜ መስከረም አስራ ሰባት የሚያከብሩት የምስጋና ስርአት በመሆኑ ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የምሁራን ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡ Frank (2004፡6) ሥር አተ ከበራ ልዩ ተግባር ሲሆን ስርአቱን የሚመሩ (የሚያስፈጽሙ) ሰዎች ይፈልጋል (ስርአቱ እን ዲከወን የሚያስተባብሩ ግለሰቦችን የሚፈልግ ነው)፡፡

ማንኛውም ስርአተ ከበራ የሚከበረው ስርአቱን በሚያውቁና የከበራውን ሂደት ለማከናወን ህጉን ጠብቆ የሚከውን ሰው እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ሃሳብ ነው፡፡ የስርዓተ ከበራን ምንነት በተመለከተ በርካታ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ሲሰጡት ይታያል፡፡ ከምደባ አንጻር

ስርዓተ ከበራዎች በሀገረሰባዊ ልማድ የፎክሎር ዘውግ ስር እንደሚመደቡ (Dorson 1972፡2-5) ገልጸዋል፡፡

**Reynolds and Erikson (2017፡2)** (Chwe፡ 2003; Clawson፡ 2004; Collins፡1981,)….ወዘተ በመጥቀስ "ስርአተ ከበራዎች አስደሳች የሆነ ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ምድብ ነው። የአምልኮ ሥርዓቶች ማህበራዊ ትስስርን ይጨምራሉ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማዘዝ እና የስርአተ አምልኮው ተካፋዮች ስለ አለም ያላቸውን ግንዛቤ የሚያደራጁበት መዋቅር ይፈጥርላቸዋል" በማለት የገለጹ ሲሆን ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ስርአተ ከበራዎች ማህበረሰብ በአንድነት እንዲ ወያይ የአከባቢውን ህግ እና ስርአት እንዲጠብቅ እንዲሁም የቡድኑን ደንብ ማህበረሰቡ እንዲማረው እና የቡድኑ አባላት ስለ አለም እውቀት የሚያገኙበት ሲሆን እንዲሁም በህግ የሚመራ ጠንካራ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በዚህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው ምስጋና ኢሬቻ ማህበረሰቡን ከማቀራረቡን ከማቀራረብም አልፎ የተለያዩ ችግሮች ቢከሰቱም እንኳን በአድባሩ ስር ምስጋና ለማቅረብ ሁሉም በቅድሚያ ችግሩን እንዲፈታ በማድረግ በአንድ መንፈስና በአንድነት ለፈጣሪያቸው ምስጋናቸውን የሚያቀርቡበት ስርአት ነው፡፡

Rappaport (1999:25) ስርአተ ከበራዎች በእጅጉ ከሀይማኖት ጋር የተቆራኙ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ሃሳብ ረገድ በሎዴ ሄጣሳ ወረዳ የሚከበረው የምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ከሃይማኖታዊ ስርአት ጋር በማያያዝ ማህበረሰቡ ለፈጣሪው ምስጋናና የተማጽኖ የጸሎት የሚያቀርብበት ስርአት በመሆኑ ከዚህ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነት አለው፡፡ **Rossano** (2015፡80) Rossano (2012)ን በመጥቀስ ሥርዓተ ከበራዎች ብዙውን ጊዜ ተደጋጋሚ የሆነና ለቡድኑ ስርአትን የሚያስገነዝቡ ሲሆን ስርአቱም የማይለዋወጥ ተከታታይ ምልክቶች ወይም ድምጾች በመፍጠር በማህበረሰቡውስጥ እንዲሰርጹ ያደርጋል፡፡ ስርአተ ከበራዎች በአብዛኛው ቋሚ ህግ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳን ስርአተ ከበራዎች በክዋኔያቸው ተደጋጋሚ ስርአት ሲሆኑ ይህም ህግጋቶቹን በቡድኑ ለማስረጽ እንዲረዳው እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

ስርአተ ከበራዎች ለማህበረሰብ ህግጋትን የሚያስተምሩ እና ግለሰቦች የተለያዩ ችግሮችን በትግሰት እንዲያልፉ እራስ መቆጣጠርን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ በዚህም ላይ Rossano (2015፡82) Mirsky (1937) በመጥቀስ

> Costly rituals demanding great self-control is commonly used for setling disputes and making peace. For example, feuds and disagreements among the Ammassalik of Greenland are often addressed using a traditional “drum mac h,”where the aggrieved parties stand face to face drumming and singing about the other’s personal and familial faws.

አምልኮዊ ስርአተ ከበራዎች ራስን መቆጣጠር የሚያስተምሩ ሥርዓቶች ናቸው። በግለሰቦች መካከል አለመግባባት ሲኖር ለመፍታት እና ሰላም ለመፍጠር የሚጠቅሙ እንዲሁም ማህበረሰቡን እንደ ባህሉ ግብረ ገብነትና መታገስን የሚያስተምሩ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

Thomas (1997፡300) ፌስቲቫሎች በተለምዶ የውድድር ሥርዓቶችን ያካትታሉ። ጨዋታዎቹም በልማድ የሚገለጹ ሲሆኑ እንደ ውድድር በልዩ ህጎች የተደነገጉna ብዙን ጊዜ ከውድድሩ አሸናፊ ሽልማት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ከዚህ ሃሳብ አንጻር ይህ የምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ጋር ተያይዘው የሚከበሩ ባህላዊ የስፖርት ውድድሮች ለስርአቱ ድምቀት ከመሆንም አልፈው በማህበረሰቡ ዘንድ ደስታ እና ፈንጠዝያን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ Rossano (2015፣82) አምልኮአዊ ከበራዎች ጠንካራ ማህበረሰቦችን በመገንባት ረገድ ውጤታማ ናቸው፡፡ ማህበረሰብን በአመለካከት አንድ ከማድረግና ከማደራጀት አኳያ ትልቅ ሚና ሲኖራቸው ማህበረሰቡ ለስርአቱ ጥሩ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ አምልኳዊ ሥርዓቶች ረቂቁን ባህል የሚያመለክቱ ትርኢቶችን ያካተቱ ናቸው። በአምልኮአዊ ስርአቶች የከበራውን ውስጣዊ ምንነት ለመረዳት የሚጠቅምና የማህበረሰቡን ባህል ከባለቤቱ ከራሱ ለመረዳት የሚያስችሉና መግለጽ የሚችሉ ናቸው፡፡

Zegeye (2017፡16) (Orent፡1969) (Yiheew፡2002) እና Yeshambel፡2009) በመጥቀስ ስርአተ ከበራ ጠንካራ አካባቢያዊ እውቀት የሆነ፤ በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው፣ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ዋጋ ሰጥቶ የሚያዘጋጀው ነው፡፡ ምስጋና፣ መስዋዕት እና ስጦታ የመሳሰሉ ስርአቶች የሚቀርቡበት ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ስርአተ ከበራዎች በማህበረሰቡስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና ስርአቱን ጠብቀው በትልቅ ዝግጅት እንደሚያከብሩት የሚያስረዳ ገለጻ ሲሆን የምስጋናው ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ማህበረሰቡ በአመት አንድ ጊዜ መስከረም አስራ ሰባትን በመጠበቅ የሚያከብረው ስርአት

ሲሆን ማህበረሰቡ ከበራውን በባህላዊ እስፖርቶች በማጀብ ፈጣሪውን እያመሰገነ የሚያከብረው ስርአት ነው፡፡

### 2.2.2. እምነት እና ስርአተ ከበራ

ስርአተ አምልኮ አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ የበላይ አካል ነው ብሎ ለሚያምነው ለፈጣሪው ወይም ከፈጣሪ ጋር ያገናኙኛል ባጠፉ ይቀጠኛል ይምረኛል ዘሬን ይባርክልኛል ባከባቢዬ ላይ በረከት ይሰጠኛል በማለት የሚፈጽሙት ታማኝነት(መታመን) ነው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበቃላት (1992፡11) ሃይማኖት ማለት ቃሉ እምነት ማለት ሲሆን "የሃይማኖት መሰረት የሰው ምርምር ሳይሆን እግዚአብሄር በተፈጥሮና በመጽሀፍ ቅዱስ መገለጥ ነው፡፡ ለዚህም መገለጥ ሰው የሚሰጠው ተገቢ የሆነ አጸፋ ምላሽ ማመንና መታዘዝ ነው"፡፡ የሚል ትርጉም ሲሰጠው ይታያል ይህ ማለት ማህበረሰቡ ከክፉ ነገር ይጠብቀኛል፣ ያድነኛል ባጠፉ ይቀጣኛል ይኮንነኛል መልካም ብሰራ ይምረኛል ወይም ያጸድቀኛል በማለት ለአንድ ፈጣሪው ወይም የበላይ አካል ነው ለሚለው ልእለ ሰብ የሚሰጡት መታመን ሲሆን ለዚህም ምላሻቸው የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን በማዘጋጀት ምስጋናውን የሚያቀርብበት ስርአት ነው፡፡ ፈቃደ (1991፡14) ሀገረሰባዊ ሃይማኖትን አስመልክተው ሲገልጹ

> የሀገረሰባዊ ሃይማኖት ምርምርም በልዩ ልዩ በዓላት ላይ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በሃይማኖት ቦታዎች (መስጊድ፣ ቤተክርስቲያን፣ ምኩራብ… ወዘተ) የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፤ በልደት፣ በግርዘት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን (interactions) ያጠናል፡፡ ሲሉ ይገልጻሉ

ከዚ ሃሳብ የምንረዳው አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ በእምነት ከፈጣሪው ጋር የሚያደርጋቸው መስተ ጋብሮች ውስጥ የተለያዩ ስርአተ አምልኮ የሚከበሩት በእምነት ቦታዎች እና በመኖሪያ ቤት የሚከወኑ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው፡፡

Rappaport (1999:25) ሁሉም ስርአተ ከበራዎች ከሃይማኖት ጋር ተያያዥ እንዳልሆኑ ሲገልጽ ሁሉም ሃይማኖታዊ ስርአትም የከበራ ስርአት እንዳሌለው ይጠቁማል፡፡ ሃይማኖታዊ እና አለማዊ ስርአትን በአንድነት አጣምረው የያዙ ስርአተ ከባራዎችም አሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የምንችለው ስርአተ ከበራዎች ሶስት አይነት መሆነቸውን እነሱም ሃማኖታዊ ስርአቶች አለማዊ ስርአቶች እና ሁለቱን ባንድነት አጣምረው የሚይዙ ስርአተ ከበራዎች

እንዳሉ የሚጠቁም ሲሆን ከዚህ አንጻር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአት መንፈሳዊ እና አለማዊ ስርአቶችን አካቶ የያዘ የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡

Sims and Stephens (2011፥61) "One of the types of cultural information most often communicated within groups is belief. Belief may be expressed in a multitude of ways, and it is likely to be present in almost every folk group–and across cultures–regardless of whether or not we identify those groups as having separate, particular belief systems." በማለት ይገልጻሉ፡፡ በእምነት አማካይነት ቡድኖች እንደሚፈጠሩ እና ሰዎች በአንድላይ እንዲወያዩም መንገድ የሚከፍትላቸው እንደ ሆነ ነው፡፡ Rappaport (1992፥7) ደግሞ እምነት በእያንዳዱ አማኝ ሰው ውስጥ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የሚኖር እና የሚጠበቅ እውነት ነው፡፡ ሰዎች የሚያምኑበት ነገር ለህይወታቸው ዋስትና እንደሆነ በማሰብ ማህበረሰቡ የራሱ የሆነ ህግ የደነገገለትና ሁሌም አባል የሆነ የሚያከብረውና የሚገዛበት ነው፡፡

ሶሎሞን (2011፥174) Durkheim(1995) በመጥቀስ "ሃይማኖትን ከተቀደሱነገሮች (sacred thing s) የተዛመዱ እምነቶችና ድርጊቶችን ያዋሀደ ስርአት መሆኑን ይገልጻል፡፡" በተጨማሪም ሃይማኖት የባህል፣ የስርአት፣የእምነት እና የአለማዊ ማንጸሪያ ስብስብ ሲሆን ማህበረሰቡን ከመንፈሳዊነት ስሜት ጋር የሚያገናኝ፣ በእለት ተለት ህይወት ዕንቅስቃሴዎቹ የሚያምነውና የሚተገብረው ስርአት ነው"፡፡ በማለት ያብራሩ ሲሆን ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ሃይማኖት ማህበረሰብን በእለት እለት ህይወቱ መንፈሳዊነትን እንዲያስብ እንዲሁም አለማዊውን ከመንፈሳዊው ስርአት የሚለይበት እንደሆነና ማህበረሰቡም ስርአቱን የሚጠብቅና የሚያከብር እንደ ሆነ ነው፡፡

Magill (1995፥1094) "እምነቶች፣ ምልክቶች እና የአምልኮ ሥርዓቶች የሁሉም ሀይማኖቶች ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው፡፡" ሁሉም የእምነት የራሱ የሆነ ስርአት ምልክት ያለው እና ምልክቶቹም የእምነቶቹ መገለጫ ወይም መለያ እንደ ሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

Rappaport (1999፥22) Erikson (1966) ን በመጥቀስ ሥርዓተ አምልኮ እና ሥርዓተ ከበራ ብዙ ማኅበራዊ ዝግጅቶችን ሊወስኑ እንደሚችሉ የገለጸ ሲሆን በተጨማሪም ሁሉም ከበራዎች ደግሞ ሀይማኖታዊ ስርአት እንዳልሆኑ ገልጧል፡፡ Lan (2018) እምነት የሰውን ተፈጥሮ ለመገምገም የሚያስችል ከሰው ልጅ መፈጠር ጋር ተያይዞ የመጣ ዓለማቀፊዊ

ውክሌና ያሉ ስርዓተ ከበራዎችም በሱ ላይ ተመርኩዘው የሚተገበሩ ናቸው፡፡በማለት ሲገልጽ Salamone (2004፥27-28) ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች በመላው ዓለም የሚገኙ በከተማም ሆነ በገጠር ነዋሪዎች ዘንድ የሚከበሩ ናቸው። እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ሰዎች ከአማልክት እና ከሌሎች መናፍስት ጋር የሚግባቡባቸው ዘዴዎች ወይም መድረኮች ሆነው ይታያሉ። በማለት ሲገልጽ ይህ ሃሳብ ከበራዎችን በማከናወን ማህበረሰቡ ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት መንገድ እንደ ሆነ እና በዚህም ከፈጣሪ ምህረት የሚለምንበት ለፈጣሪም ምስጋና የሚያቀርብበትመድረክ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከዚህም አንጻር ይህ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ከዚህ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡

Rappaport (1999:31) ስርአተ ከበራ ማንኛውንም ዓይነት ነገር ለመግለጽ አማራጭ መንገድ ብቻ ሳይሆን ከአንዳንድ ትርጉሞች በተሻለ ሁኔታ ሊገልጹ የሚችሉ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ እምነቶች፣ ምልክቶች እና የአምልኮ ሥርዓቶች የሁሉም ሀይማኖቶች ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳው ስርአተ ከበራዎች በተሻለ ሁኔታ ሃይማኖትን መግለጽ እንደሚችሉና የሰውን ልጅ ሃሳብ ለመረዳት የሚጠቅሙ መሆኑን እንዲሁም እምነቶች፣ ምልክቶች እና የአምልኮ ስርአቶች የሃይማኖት መገለጫ ቁልፍ መሆናቸው የሚያስረዳ ነው፡፡

Salamone (2004፥5) የአምልኮ ሥርዓቶች ተሳታፊውን ማህበረሰብ ያገለግላሉ ማህበረ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ተምሳሌታዊ ትርጉም ያላቸው እንዲሁም ኃይልን ያካተቱ የአምልኮ ሥርዓቶች ማህበራዊ ትርጉም ያላቸው እና ተምሳሌታዊ ድርጊት ያላቸው ክስተቶች ናቸው፡፡ ሁሉም ሃይማኖት በሚከተለው አማኝ ዘንድ የራሱ የሆነ ስያሜ ሲኖረው በሚከበርበት ጊዜም ስርአቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ተምሳሌታዊ ትርጓሜ የሚሰጣቸውና ሃይማኖቱም ለተከታዩ ማህበረሰብ አንጻራዊ ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡ ከዚህ ገለጻ አንጻር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ በሚካሄደው የአምልኮ ስርአቶች ለአማኙ ማህበረሰብ የጤና፣ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣የሰላም እና ...ወዘተ ጠቀሜታዎችን እንደሚሰጡ እንረዳለን፡፡

### 2.2.3. የስርአተ ከበራ አይነቶች

በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚከወኑ በርካታ መንፈሳዊ እና አለማዊ ስርዓተ ከበራዎች አሉ፡፡ ስርዓተ ከበራዎች ከሚቀርቡበት ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ምክንያቶች፣ ከተሳ ታፊዎች አይነት እና ከሚከወኑበት አካባቢ ወይም መልካዓ ምራዊ ሽፋን አንጻር አይነታቸው የ

ተለያየ መኑንሶሎሞን (2011፡162) ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ምሁራን  በተለያ ዩ አይነቶች ይመድቧቸዋል፡፡ ከነዚህም ምሁራኖች መካከል Sims and Stephens (2011፡113 - 124) የህይወት ሽግግር ስርዓት (rites of passage)፣ የእድሜ ሽግግር ስርዓተ ከበራዎች (coming of age rituals)፣ የመነሳሻ ስርዓተ ከበራዎች (initiation rituals) እና የስም አወጣጥ ስርዓተ ከበራዎች (naming ritual) በሚል በአራት የከፈሉት ሲሆን Bell (1997፡94) ደግሞ የህወይት ሽግግር ስርዓት (rites of passage)፣ ቀነ ቀመራዊ ከበራ (Calendrical Rites)፤ የልውውጥ እና የትስስር ከበራ (Rites of Exchange and Communion)፣የመከራ ጊዜ ከበራ (Rites of Affliction)፣ ግብዣ፣ ፆምና ክብረ በዓል (Feasting, Fasting, and Festivals) እና ፖለቲካዊ ከበራ (Poletical Rites) በማለት  በስድስት ትከፍላቸዋች፡፡

ከነዚህ ሃሳቦች በመነሳት ይህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የሚካሄደው ጊዜውን ጠብቆ በአመት አንድ ቀን የሚከበር ሲሆን የከበራው አለማ ከክረመት ወራት ወደ በጋው ወራት በሰላም መሸጋገራቸውን በማስመልከት ለፈጣሪ ምስጋና ለማቅረብ የሚካሄድ ስርአት ነው፡፡ የኢሬቻው ስርአተ ከበራ በቀነ ቀመራዊ ከበራ (Calendrical Rites) እና የመሸጋገሪያ ከበራ (Rites of Passage) ስር ይካተታል፡፡

ቀነ ቀመራዊ ከበራ ማለት በአመቱስጥ ወይም በወሩስጥ ያሉ ቀናትን በመቁጠር አንዱን ቀን በምክኒያት በማስደገፍ ከዘመን ዘመን በዛው ቀን ላይ የሚከበር ሲሆን  ይህን ሃሳብ አስመልክታ Bell (1997፡102) ቀነቀመራዊ (Calenderical rites) ዕለታዊ፣ ወረሃዊና ዓመታዊ በሆነ መልኩ ጊዜያቸውን ጠብቀው በጊዜ ቀመራዊ የሚከበሩ ስርዓተ ከበራዎች ከተያዘላቸው ቀን እንዲያልፉ አይፈለግም፡፡ ስትል ትገልጻለች Thomas (1997፡296) ፌስቲቫሎች በባህላዊ መልኩ ዓለማዊ ወይም ሀይማኖታዊ ተብለው ይከፋፈላሉ። ዓለማዊ በዓላት ወደ ሀይማኖት ያመራሉ ተፅእኖአቸውን እና ማህበራዊ ጠቀሜታቸውን የበለጠ ለማሳደግ ሃይማኖታዊ ፌስቲቫሎች ሁሌም ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች አሏቸው፡፡ ፌስቲቫል በርካታ የአምልኮ ሥርዓቶችን እና ዝግጅቶችን ያቀፈ ሁሉንም የማህበረሰብ አባላት የሚነካ በግልፅ እሴቱን እና ርዕዮተ ዓለሙን ማህበረሰቡ የሚጋራው የአለም እይታ የማህበራዊ ማንነታቸው መሰረት ነው። ከዚህ አንጻር ስርአተ ከበራዎች ያንድን ማህበረሰብ ማንነት መግለጽ የሚችሉናቸው፡፡ ከበራዎች አለማዊ እና ሃይማኖታዊ ገጽታ ያላቸው ሲሆኑ እነሱም በተለያየ መንገድ እራሳቸውን ከጥቅም ጋር ያስተሳስራሉ በተጨማሪም

ማህበረሰቡ ስለ አለም ያለውን አመለካከት እና ፍልስፍና በከበራ ውስጥ አካተው የያዙ ናቸው፡፡

ማህበረሰብ በተለያዩ መንገዶች በየአከባቢው የተለያላዩ ተፈጥሮአዊ ችግሮች እንዳይከሰቱ በማለት ስርአተ ከበራዎችን ይፈጽማል ከዚህም መካከል ከግብርናው ስርአት ጋር በማያያዝ የሚከበሩ ስርአቶች ይጠቀሳሉ ይህንንም አስመልክቶ Salamone (2004፡27-28) የግብርና ስርአተ ከበራዎች ባምስት ይከፈላሉ እነዚህም (1).አብዛኛው የግብርና ሥነሥርዓት ረጅም ታሪክ ያለው እና እንዲያውም የቆዩ የአደን ሥርዓቶችን ያካተተ ነው፡፡ (2).የግብርና ሥነ-ሥርዓቶች ከማደግ፣ ከአደን፣ ወይም ከአሳ ማጥመጃ ወቅቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ (3).የግብርና ሥነ-ሥርዓቶች ሰዎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ካንዱ ወቅት ወደ ሌላው በሰላም ለመተላለፍ የሚያከብሩትነው፡፡ (4).የባህል ተዋረድን ለማስቀጠል ብዙን ጊዜ የግብርና ሥርዓቶች መመረጣቸው። (5). ለሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ለአገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ክታቦች እና ሌሎች ሃይማኖታዊ ነገሮች አዘጋጅቶ የያዘ መሆኑ። እነዚህ ነገሮች ለመሥዋዕት የሚሆኑ መሠዊያዎች፣ የአምልኮ ሥርዓቶች ጭምብሎች፣ እና ለግል ጥቅም የሚውሉ ትናንሽ ቶቴዎችን ያካተተ ነው፡፡ በሚል በአምስት ምድቦች ያስቀመጡት ሲሆን ከነዚህ ከአምስቱ የአምልኮ ስርአቶች መካከል የኢሬቻው ስርአት ሰዎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ካንዱ ወቅት ወደ ሌላው በሰላም ለመተላለፍ የሚያከብሩት በመሆኑ በሃሳብ ያመሳስላቸዋል፡፡

### 2.2.4. የስርዓተ ከበራ ባህርያት

የስርዓተ ከበራ ባህሪያትን አስመልክቶ ሶሎሞን (2011፡160-162) Rappaport (1999) በመጠቀም የስርዓተ ከበራ ገጽታዎች በሚል በአምስት በመክፈል ያቀርቧቸዋል፡፡ እነዚህም ባህሪያት ከከዋኞቹ በተጨማሪ በሌላ ተሳታፉዎች መታወቃቸው፣ ስርዓታዊነት፣ ቋሚነት፣ ክወና፣ መደበኛነትና የአካል ብቃት በማለት ሲከፍላቸው Bell (1997፣ 138 159) ደግሞ መደበኛነት፣ ኢ-ተለዋዋጭነት ወይም ቋሚነት ስርዓታዊነት (ደንባዊነት)፣ መንፈሳዊ የሆነ ትዕምርታዊነት እና ተከዋኝነት በሚል አከፋፈል የመደበች ሲሆን የሁለቱም ሃሳብ ተቀራራቢነት ያለው ነው፡፡ ስርአተ ከበራዎች የራሳቸው የሆነ ባህርይ ያላቸው መሆናቸውን እና በዚህም አብዛኛዎቹ ከበራዎች በባህርይ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት ስር የሚካተት ስርአት ነው፡፡ በመሆኑም ስርአቱ ወቅቱን ጠብቆ ከመከበሩም በላይ በአከባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚታወቅ ስርአት ነው፡፡ በተጨማሪም ኢ-ተለዋዋጭነት ወይም ቋሚነት ስርዓታዊነት (ደንባዊነት)፣ መንፈሳዊ የሆነ ትዕምርታዊነት እና ተከዋኝነት የሚሉ ባህሪያቶች የሚንጸባረቁበት ስርአተ ከበራ ነው፡፡

## 2.2.5. የስርዓተ ከበራ አላባውያን

የስርአተ ከበራ አላባውያን የከበራውን ሁኔታ የምንመለከትባቸው ማንጸሪያ ሲሆኑ እነዚህም አላባውያን የሚቀርበውን የፎክሎር ዘውግ ከመለየት አንስቶ ባጠቃላይ አውዱን የምንመለከትበት ነው፡፡ ስርዓተ ከበራዎች የተለያዩ አላባዎች (Elements) አሏቸው፡፡ የስርዓተ ከበራ አላባውያንን አስመልክተው Cooke and Macy (2005፡52-53) በተለያየ መንገድ በመከፋፈል ያስቀምጧቸዋል፡፡ እነዚህም

1ኛ/ እያንዳንዱ የአምልኮ ሥርዓት አንድ ማህበረሰብ ዓለምን እንዴት እንደሚረዳ እና የአምልኮ ሥርዓቱ ራሱ እንዴት ያንን ግንዛቤ ለመቅረጽ እንደሚችል ሁለቱንም ይገልጻል። በሌላ አባባል የአምልኮ ሥርዓቶች በአለም ላይ ያለን ብዙ ልምዶችን እንዴት መረዳት እንዳለብን ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ ሥርዓቶች አንዱ የ‹‹hermeneutic of experience››ነው፡፡ ማኅበረሰብ ዓለምን የሚተረጉምበት ማለት ነው። አንድ የአምልኮ ሥርዓት ልደት, ጉርምስና, ጋብቻ እና ሞት ስለ ምን እንደሆኑ የሚገልጽ ነው፡፡

2ኛ/የአምልኮ ሥርዓት የእምነቱ ተከታዮች እንዲጠነክሩ እና በሳል የአምልኮ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች እንደገና እያንዳንዱን አማኝ በራሱ መንገድ የሚያጠነክር ነው፡፡ በይበልጥ ከራስ ወዳድነት ነፃ እንዲሆኑ ይረዳል ባጭሩ እርስ በርስ መዋደድን ይፈጥራል ። እያንዳንዱ የአምልኮ ሥርዓት ለተጨማሪ የሀሳብ ስሌት እድል ይሰጣል፡፡ ይህ ሃሳብ አክባሪው ማህበረሰብ እርስ በርሱ እንዲዋደድ እና እንዲደጋገፍ እድል የሚፈጥር ማህበረሰቡም እርስ በርስ የመደጋገፍ ልማድ እንዲያዳብሩ የሚረዳ ነው፡፡

3ኛ/ ማህበረሰቡ በስርአተ ከበራው ላይ የሚያምነውን መንፈስ የማይሞት ሕያው (ዘላለማዊ) በሰማይ እንዳለ እና በመንፈስ ከነሱእንደማይለይ አድርገው ያምናሉ፡፡ በዚህም አንድ

ማህበረሰብ ስርአተ ከበራዎችን በሚያከብርበት ጊዜ የሚያመልኩት አምላክ ከሞትም በኋላ ቢሆን እንደማይተዋቸው በማሰብ ነው፡፡

4ኛ/ አማኞች ከሚያምኑት መንፈሳዊ ኃይል (አካል) ማግኘት የሚፈልጉትን ጥበቃ (Salvation) ለማግኘት በሚል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ይህ አገልግሎትም የጥበቃ ዋስትና ማግኛ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ የተራቡትን ማብላት፣ የተጠሙትን ማጠጣት፣ እንግዳ መቀበል፣ የታረዙትን ማልበስ፣ የታመሙትንና የታሰሩትን መጎብኘት ነው፡፡ እርስ በረስ መደጋገፍን የሚያዳብር ሃሳብ ነው፡፡

5ኛ/ ስርአተከበራዎች የወዳጅነት ማጠናከሪያ መድረኮች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡም ስርአተከበራዎችን ለመፈጸም በሚሰባሰብበት ወቅት አጋጣሚውን እርስ በርስ በመረዳዳት ይጠቀምበታል፡፡ ማህበረሰቡ በታላቅ ደስታ ወይም በታላቅ ሀዘን ጊዜ ለጋራ ድጋፍ ይሰበሰባል ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ለመሳቅ፣ ለማልቀስ፣ ለመብላት፣ ለመጠጣት፣ ለዳንስ እና ለመዘመር ይሰበሰባሉ። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ጓደኝነትን ይፈጥራሉ እና ያጠናክራሉ በጣም ጥሩ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሁሉም የአምልኮ ሥርዓቶች ሰዎችን እንደ እህት እና ወንድማማችነት ያሰባስባሉ በዚህም ማህበረሰቡ እርስ በርስ የሚተዋወቅበትን መድረክ የሚፈጥርለት ስርአት ነው፡፡ በማለት በአምስት የከፈለቻቸው ሲሆን እነዚህ አላባውያን ከክርስትና እምነት ስርአተ ከበራ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህ የስርአተ ከበራ አላባውያን በሁሉም ሃማኖታዊ ከበራ ስርአት ውስጥ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

ሶሎሞን (2011፣46) ፎክሎሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ህይወት እንዲኖራቸው ፣ትርጉም እንዲሰጡ፣ ቅርጻቸውን እና ይዘታቸውን ሳይለቁ እንዲቀርቡና ተስተላልፎዋቸውም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲቀጥል በውስጣቸው የምናገኛቸው አላባውያን (Elements) አስተዋጽኦ

ከፍተኛ ነው፡፡ የፎክሎር አላባውያን የሚባሉት አሀድ(Text)፣ገጽታ(Texture)፣አውድ(Context)፣ እና ክወና(Performance) ናቸው፡፡ በማለት ይገልጻል፡፡ እነዚህ አላባውያን የአንድ ፎክሎር መሰረት በመሆናቸው ሁሌም ከፎክሎር ተለይተው የሚታዩ አይደሉም ፎክሎር እና አላባውያን ተደጋጋፊ ናቸው፡፡

### 2.2.6. የስርዓተ ከበራ መሰረቶች

ስርዓተ ከበራን ለመከወን በመሰረታዊነት የማይቀሩና አስፈላጊ የሆኑ አብረውት የሚነሱ ሌሎች ፎክሎራዊ ገጽታዎች አሉ እነዚህ ገጽታዎች ከበራውን ማስተካከል እና የስርአቱን ሂደት የሚመሩ ናቸው:: እነዚህን የስርዓተ ከበራ መሰረቶች አስመልክቶ ሰሎሞን (2010፡26) Firth (1967)፣ Rappaport(1992)፣ Gruenwald (2003) እና(Cooke and Macy፣2005)ን በመጥስ ክወና (Performance)፣ ትዕምርት (Symbol)፣ሚት (Myth) እና መንፈሳዊ ሙዚቃ ናቸው፡፡ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው የትኛውም ስርአተ ከበራ መነሻው እና ስርአተ ከበራም በሚከበርበት ጊዜ ልዩ ትርጉም የሚሰጡና ፎክሎሩ ስርአቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚያደርጉት ሲሆን በተጨማሪም የስርአተ ከበራ ዋና ቁልፍ ሆነው የሚቀርቡ ስርአቶች ናቸው፡፡

### 2.2.7. ስርአተ ከበራ እና ክዋኔ

ክዋኔ የከበራዎች አንዱ አላባውያን ሲሆን ማንኛውንም ፎክሎራዊ ገጽታዎች ለማቅረብ እና ለመከወን የሚረዳን ነው፡፡ በተጨማሪም ፎክሎር ያለክዋኔ ክዋኔም ያለ ፎክሎር ቅንጣቶች የሚታሰቡ አይደሉም በዚህም ፎክሎር እና ክዋኔ የተጣመሩና የማይለያዩ ሁለት ቅንጣቶች ናቸው፡፡ አንድን የፎክሎር ስርአት ለማቅረብ ክዋኔ ትልቅ ጠቀሜታ አለው ይህን በተመለከተ Rappaport (1992፣ 250) “ክዋኔ ከሌለ ከበራ የለም” ይህ ማለት ከበራዎችን ለማካሄድ የግድ ክዋኔዎች እንደ ሚያስፈልጉ የጠቀሰበት ነው፡፡

በተጨማሪም የክዋኔና የክብረ በዓል ትስስርን በተመለከተ Rappaport (1992, 250) ላይ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡“…there is no performance, there is no ritual; performance itself an aspect of that which is performed. The medium is a part of the message; more precisely, it is a metamessage about what ever is encoded in the ritual”. ሃሳቡ የሚያመለክተን ከበራ እና ክዋኔ ተደጋጋፊ መሆናቸውንና አንዱ የላንዱ እራሱን ችሎ መቅረብ የማይችል ሲሆን በተጨማሪም የክዋኔዎች የከበራውን መልእክት ወይም ሃሳብ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡

Grimes (1985፣92) ክዋኔ እና ሃይማኖታዊ አምልኮ ሥርዓቶች የተቀረጹና የተገደቡ የተለያዩ የተግባር ዘውጎች ተብለው ተለይተዋል። ባጠቃላይ ሃማኖታዊ ከበራዎች ክዋኔያቸው በታዳሚው የሚታወቁ ስርአቶች ናቸው፡፡ …በክወና አማካኝነት መልእክት

ለማስተላለፍ ከዋኝ (performer) እና ታዳሚ (audience) የግድ የሚያስፈልግ ሲሆን እነዚህ አላባውያን በየትኛውም ስርአተ ከበራ ላይ የሚከወኑ ስርአቶች ሲኖሩ ከዋኝ እና ታዳሚ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ Gillitt (2013፣280) (Schechner 1992:9) ን በመጥቀስ

> Performance is about more than the enactment of Eurocentric drama.Performance engages intellectual, social, cultural, historical, and artistic life in a broad sense. Performance combines theory and practice. Per-formance studied and practiced inter culturaliy can be at the core of a "well-rounded education." That is because performed acts, whether actual or virtual, more than the written word, connect and negotiate the manycultural, personal, group, regional, and world systems comprising today's realities. Performance of course, includes "the arts" but goes beyond them. Performance is a broad spectrum of entertainments, arts, rituals; politics, economics, and person-to-person interactions.This broad spectrum enacted multiculturally and interculturally can do much to enhance human life.

ይህ ሃሳብ የሚያመለክተን ክዋኔ በማንኛውም የሰው ልጅ ህይወት ውስጥ እንደ ሚገኝ እናበተለያ ስርአቶች ማለትም በከበራው፣ በመዝናኛው፣በሃይማኖታዊ ስርአቱ…ወዘተ ሁሉ እንደ ሚጠቅም የሚያሳየን ነው፡፡

Don Lee (2009፣6) (Schechner 1973፣25) በመጥቀስ ስርአተ ክወኔዎችን በስምንት ይከፍሏቸል

> 1) In everyday life-cooking, socializing, 'just living'. 2) In the arts. 3) In sport and other popular entertainments. 4) In business. 5) In technology. 6) In sex. 7) In ritual-sacred and secular 8) in play…The performing arts, sports, and games are playful, but they often use the processes of ritual. We cannot go through a day without performing dozens of rituals. There are religious rituals, the rituals of everyday life, the rituals of roles, the rituals of profession, and the rituals of politics, business, and the judicial system.

በማለት ይዘረዝራቸዋል ከዚህም አንጻር የኢሬቻው ስርአተ ከበራ Schechner ከከፈላቸው ሃሳቦች መካከል በሥርዓተ ከበራዎች መካከል መንፈሳዊ፣ ዓለማዊ እና የጨዋታ…ሥነ ጥበባት፣ስፖርት እና ጨዋታዎች በሚሉት ክዋኔዎች ስር የሚካተት ነው፡፡

### 2.2.8. የስርዓተ ከበራ ጠቀሜታ

ስርአተ ከበራዎች በማህበረሰቡስጥ የተለያዩ ጠቀሜታዎችን የሚሰጡ ናቸው ከነዚህም መካከል ማህበረሰቡ በማክበሩ መንፈሳዊ እርካታ የሚያገኙባቸው ሲሆኑ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ስርአት መቅረጽ እና ማስተካከል ይችላሉ፡፡ ይህን በተመለከተ Salamone (2004, 361) A ritual is an ordered system of symbolic activities that is performed by either a person or a group of persons for the purpose of serving some function. As a symbolic event, a ritual expresses a tradition or history while simultaneously reaffirming the importance and place of that history in the future. ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ስርአተ ከበራዎች ያለፈን ታሪክ ወይም ሃይማኖታዊ ስርአቶችን በአንድ ጊዜ የታሪኩን አስፈላጊነት እና ቦታ ወደፊት የማረጋገጥ አቅም እንዳለው የሚገልጽ መሆኑን ነው።

ስርአተ ከበራዎች ወቅታቸውን ጠብቀው መከበራቸው የተለያየ ጠቀሜታ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ይህንንም ሃሳብ በመደገፍ HAILU (2019:174) ማህበራዊ ዝግጅቶች ብዙን ግዜ የሚከናወኑት የጋራ ባህል ባላቸው ግለሰቦች ነው፡፡ ጥቂቶቹ የእኩልነት ተካፋይ የተለያየ ባህል ሊኖራቸው ይችላል የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች ለመነብኘት፣ ለመዝናኛ እና ለሌላ ዓላማ በበዓሉ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ የዝግጅቱ አላማ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ባህላዊ ወይም ሀይማኖታዊ ሊሆን ይችላል ሰዎች ለነጠላ ዓላማ ሲሰባሰቡ በዚያ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ አመለካከት እና አላማ አላቸው። በተሳታፊዎች መካከል አንድነትን እና ፍቅርን ያጠናክራሉ፣ ማንነትን ይገልጻሉ፣ የቱሪዝም ምንጭ ሆነው በማገልገል ባህልን ጠብቀው ያሳድጋሉ።

በማህበረሰቡስት ስርዓተ ከበራዎች ባላቸው ሀይማኖታዊ እና ማህበራዊ ተቀባይነት ትልቅ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ Sims and Stephens (2011፡103) ስርዓተ ከበራዎች በባለቤታቸው ዘድ እንደቅዱስ ተደርገው በሚታዩ መርሆዎች እና በሰው ልጅ አለማዊ ህይወት ውስጥ በሚገኙ ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ እሴቶች መካከል ያሉትን ውስብስብ ግንኙነቶች

እንደሚገልጹ እንዲሁም ሰዎች ስርዓተ ከበራዎችን አስመልክተው እራሳቸውን በተለያየ ጌጣጌጥ እና አልባሳት እንዲዋቡ ለማድረግ እንደሚጠቅሙ ያስረዳሉ:: በተጨማሪም Sims and Stephens (2011፥99) ስርዓተ ከበራዎች በአንድም ሆነ በሌላ ከክዋኔጋር ተያይዘው የሚገለጹ፣ በተለያዩ ዝግጅቶች፣ በተደጋጋሚ የሚከወኑ ለከዋኛቸውም የራሳቸው የሆነ ውክልና፣ ትዕምርታዊ አገልግሎት እና በርካታ የሆነ የተለያየ ጠቀሜታ የሚሰጡ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ገለፃ አንጻር ይህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚካሄደው የኢሬቻ ስነስርአት ለማህበረሰቡ ሃማኖታዊ፣ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ እና ወዘተ የመሳሰሉ ጠቀሜታዎችን የሚሰጥ ስርአተ ከበራ ነው፡፡ Robbins (2001 594)“a ritual creates a specific state, that performance communicates indexically that state has been produced” ስርአተ ከበራዎች በሚያካሂዱት ክዋኔ አማካይነት የራሳቸውን አካባቢ ሊወስኑና ሊፈጥሩ እነደ ሚችሉ የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡

Jones and Legare (2016፣43) (Tooby, Cosmides & Price, 2006) ን በመጥቀስ የአምልኮ ስርአተ ከበራዎች ለቀጣይ መስተጋብር ሊታመኑ የሚችሉትን የቡድኑን አባላት ይለያሉ ቡድኑም የተለያዩ የንብረት ብዝበዛ እንዳይደርስበት ይጠብቃል፡፡ ሌብነትን ለመከላከል አንዱ መንገድ ለቡድኑ ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ግለሰቦችን በመምረጥ ነው። የአምልኮ ስርአተ ከበራዎች የተለያዩ የህዝብ ገንዘብን ከመበዝበዝ የሚጠብቁ ታማኙ ግልሰቦችን ለሃይማኖት ጠባቂ እንዲመረጡ መንገድ የሚያመቻች እንደ ሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

Jones and Legare (2022፥45) የአምልኮ ሥርዓተ ከበራዎች የቡድን ችግሮችን የሚፈቱ አራት ነጥቦችን በውስጣቸው ያካተቱ ናቸው እነዚህም ነጥቦች (ሀ) ለቡድን አባልነት አስተማማኝ ምልክቶችን ይሰጣሉ፣ (ለ) ለቡድኑ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ፣ (ሐ) ማህበራዊ ጥምረት ወይም ትብብር እንዲኖር ማመቻቻት እና (መ) የማህበራዊ ቡድን ትስስርን ማሳደግ ናቸው። መንፈሳዊ ከበራዎች ሲከወኑ እነዚህን አራት ነጥቦች በውስጣቸው የያዙና በነዚህ ነጥቦች አማካይነት ስርአቱን የሚመሩ እና ሃላፊዎችን እንደሚመርጡ የሚያሳይ ነው፡፡ ሃማኖታዊ ስርአተ ከበራዎች በቡድኑስጥ የተለያዩ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ማስተካከል የሚችል እና የቡድኑንም አባላት ባንድነት ማስተሳሰር የሚችሉ ስርአቶችን በውስጣቸው አካተው የያዙ ናቸው፡፡

### 2.2.9. የኢሬቻ ምንነት

ኢሬቻ (Irreecha) ማለት ሁሉን ለሰጠ ፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብ ስርአት ነው፡፡ የኢሬቻ አይነቶች የተለያዩ ሲሆኑ እነዚህን የኢሬቻ አይነት በማስመልከት gammachuu እና sisayi(2019;176-182) ኢሬቻ ስርአት የተለየዩ ናቸው፡፡ እነዚህም የኢሬቻ አይነቶች በማለት ያስቀመጣቸው የሰላምና የእርቅ ኢሬቻ (Irreecha Nagaa fi Araaraa)፣ የጋብቻ ኢሬቻ (Irreecha gaa`elaa)፣ በአዳራሽ የሚከበር ኢሬቻ (Irreech Galmaa)፣ (በበልግ ወቅት የሚከበር ኢሬቻ ወይም ኢሬቻ ቱሉ (Irreecha Arfaasaa; Irreech Tulluu)፣ ኢሬቻ መልካ/ በወንዝና በሀይቆች ላይ የሚከበር (Irreecha Malkaa) በማለት በአምስት ይመድቧቸዋል፡፡ በዚህ ምድብ ከተዘረዘሩት መካከል ይሕ በዱኒ አድባር የሚከበርው የኢሬቻ ስርአት በመልካ ከሚከበረው ኢሬቻ ጋር በተመሳሳይ ወቅት የሚከበር ስርአት ነው፡፡

ኢሬፈና ማለት የኢርቻውን አከባበር ስርአት ሂደት የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም ኢሬቻ ሁለት አይነት ሲሆን እነሱም ኢሬቻ ጋራ እና ኢሬቻ መልካ ይባላሉ ይህንን አስመልክተው ከገለጹ ምሁራን መካከል፡፡ Serawit(2018) Tiruneh(2019) DAAMXOO(2019) Samuel (2014) ኢሬቻ ለመማፀን እና ፈጣሪን ለማመስገን የሚደረግ የአምልኮ ሥርዓት ነው። ሁለት ዋና ዋና ዓመታዊ ክብረ በዓላት አሉ ኢሬቻ ቱሉ (ከተራራ ጫፍ) እና ኢሬቻ ማልካ (በወንዝ ዳር)። ኢሬቻ ቱሉ (ከተራራ ጫፍ) በበጋ ወቅት የሚካሄደው ዋቃ (ፈጣሪ) ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ዝናብ እና ጥሩ የግብርና ምርትን ለመለመን ነው። ኢሬቻ መልካ (በወንዝ ዳር)። ደግሞ ከዝናባማ ወቅት ወደሞቃታማው ወቅት ላሸጋገረ ፈጣሪ የሚቀርብ የምስጋና ሥርዓት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኢሬቻ መልካ ሽግግር ሲሆን ከክረምት ወራት ወደ ጸደይ (መኸር) ወቅት በሰላም ላሸጋገራቸው ፈጣሪ የሚያቀርቡት የምስጋና ስርአት ነው፡፡

በሎዴ ሄጦሳ ወራዳ የኢሬቻ ስርአት የሽግግር ስርአት ሲሆን ስርአቱ የሚፈጸመው በመልካ ሳይሆን በአድባር ዛፍ ስር መካሄዱ ለየት ያደርገዋል፡፡ ይህ የምስጋና ኢሬቻ ማህበረሰቡ ባከባቢው ኢሬፈና በማለት ይጠራዋል ያከባቢው ማህበረሰብ ባንድነት በመውጣት ከወቅት ወደ ወቅት ላሸጋገራቸው ፈጣሪ የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎትና ዘፈን ነው፡፡

## 2.3. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

የዚህ ጥናት መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ከተፈጥሮአዊ መቸት ከማህበረሰቡስጥ ከተሰበሰቡ ብኋላ በየዘርፉ በመመደብ ትክክለኛ መረጃ እንዲያስተላልፉና መልእክታቸው ምን ሃሳብ እንዳለው በግልጽ ለማስተላለፍ እንዲረዱ መረጃዎችን በንድፈ ሃሳብ መፈከር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ጥናት በክዋኔው ስርአት በርካታ ሃሳቦችን ያካተተ በመሆኑ እነዚህን መረጃዎች ለመተንተን ከሃሳባቸው በመነሳት ክወናዊ (performance) ንድፈ ሃሳብ፣ ትእምርታዊ (Semiotics) ንድፈ ሃሳብ እና ተግባራዊ (Functionalism) ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም መረጃዎቹን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 2.3.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ (performance theory)

በዚህ የንድፈሃሳብ መተንተኛ ዘዴ ማህበረሰቡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት ያለውን ስርአት ክዋኔ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ለመተንተን እና ለማቅረብ የተመረጠ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብን አስመልክተው Bell (1992፣38)

> In its own way, performance theory signals a strong dissatisfaction with the traditional categories brought to the study of ritual. At the same time, however, its focus on ritual, theater, or sports as 'genres' or 'universals' of performance appears to involve the construction of very traditional types of relationships and categories. Some performance theorists have explicitly aspired to transcend such conventional dichotomies as oral and written, public and private, doing and thinking, primitive and modern, sacred and secular.

ይህ ሃሳብ የሚያመለክተን ክወና በተለያየ ስርአቱስጥ ይገኛል እነዚህም በስርአተ ከበራው ላይ የሚቀርቡ፣በቲያትር፣ በስፖርት፣ በአለማዊ እና በመንፈሳዊ ስርአቱስጥ እንደሚገኙ የሚያሳይ ስርአት ሲሆን በዚህ ጥናቱስጥ ያሉ ባህላዊ እስፖርቶች በክዋኔያዊ ቲሪ ተዳሰው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም (Bell 1992፣37-38) ክዋኔ እና ስርዓተ ከበራ የተያያዙ እና የማይነጠሉ እንደሆኑ ሲገልጽ እንዲሁም ፎክሎርን ከክዋኔ ነጥሎ መመልከት የማይቻል ነው፡፡ ስርአተ ከበራን ለማጥናት ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት በዚህ የኢሬቻ በአል አከባበር ስርአት ላይ በአባቶች፣

በልጅ አገረዶች፣በፎሌዎችና በወጣት ወንዶች የሚከወኑ ባህላዊ ዘፈኖች ስርአቱን ለማስፈጸም የሚከናወኑ ስርአቶችና በስርአተ ከበራው ወቅት መከፈቻና ማጠቃለያ ላይ የሚካሄዱ የምረቃ ስርአት ላይ ያለው ያከዋወን ስርአት ምን እንደሚመስልና የማህበረሰቡ ባህል ከምን አንጻር እንደሚገለፅ ለመተንተንና ለማሳየት የሚረዳ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡

Finnegan (1992:86) (Turner (1986), Burke (1966) እና Blumberg(1988))ን ጠቅሰው "One influential approach is to take the idea of 'performance' as a fundamental key to Human action and to culture often centred round the concept." በማለት ይገልጻሉ፡፡ በዚህም ስርዓተ ከበራ ከክዋኔ ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት ያላቸው ፎክሎሮች እንደመሆናቸው ክዋኔያዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም ለመተንተን የሚያስችል ሲሆን ግለሰቦች በቡድን ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ እና የቡድኑን ሁለንተናዊ አከዋወን በስርአቱ ውስጥ በተግባር ለማየት የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ በተለይም በስርአተ ከበራው ወቅት ያለውን ከአካል እንቅስቃሴና ከቃላት ቅላጼ አንጻር በቡድኖቹ መካከል ያለው ቅብብሎሽ ያውራጅና የተቀባይ እንዲሁም በሚከውኗቸው የከበራ ስርአት ምን አይነት የአካል እንቅስቃሴና በቡድኑስጥ ያለውን የዘፈኖች ቅብብል በዚህ ንድፈ ሃሳብ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

Sims and Stephen (2011፣27) እንደሚገልጹት ክዋኔ ተኮር አቀራረብ በአጥኚው እይታ ላይ የተመረኮዘ ሆኖ አጥኚው ቡድናዊ ክዋኔውን እና ጥበቡን ከአውዱ በመነሳት ፎክሎሮቹ እንዴት እንደሚቀርቡ፣ እንደሚከወኑ እና በቡድኑ መካከል ምን አይነት የፈጠራ አይነቶች እንደሚስተዋሉ በመመልከት ጉዳዩን በጥሩ ሁኔታ ለመረዳትና ለማጥናት እንደሚያስችለው ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኛው ስርዓተ ከበራ በቡድን የሚቀርብ ክዋኔ እንደመሆኑ ይህን ተግባር በተሟላ ሁኔታ ገላጭ በሆነ መንገድ ለማሳየት ከሚያገለግሉት መተንተኛዎች አንዱ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ በክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ባጠቃላይ የኢሬቻውን ስርአተ ክዋኔ ገላጭ በሆነ መንገድ ተንትኖ ለአንባቢ ግልጽ እንዲሆን በክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትኖ ቀርቡዋል፡፡

ክዋኔዎች አውዱን እንደሚከውነው ማህበረሰብ ባህልና ስርአት ይዘታቸው የተለያየ ነው፡፡ ይህንንም እስመልክተው ዘሪሁን (1992፣22) "ክዋኔ ስነ-ቃሉ እንደፈለቀበትና እንደሚነገርበት አካባቢ ባህል የተለያዩ መልኮች አሉት"፡፡ ከበራዎች ላይ ስርአተ ክዋኔ በተለያዩ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል ከመቅረቢያ መንገዶቹ መካከል ደግሞ ስነ-ቃል አንዱ

በመሆኑ በዚህ በኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚከወኑ ስርአቶች ላይ በስነ-ቃል የሚቀርቡ ሃገረሰባዊ ዘፈኖችና የአባቶችን ምርቃት ለመመርመር እና ተንትኖ ለማስረዳት የሚያስችል ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የኢሬቻውን ስርአተ ከበራ ቅደም ተከተል ጠብቆ ያለውን ሂደት በክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበውበታል፡፡

Green (1997፣630) የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሮ እናገኘዋለን ይህም ሃሳብ በፎክሎር ውስጥ፣ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የተለመዱ የጥበብ መንገዶችን ተጠቅመው ለሌላ ተመልካች የሚያሳዩበት የአከዋወን ዘዴ በንድፈ ሀሳብ እና በአሰራር፣ የአከዋወን ጽንሰ-ሀሳብ የሚገነባው ቃሉ ብዙም ጥቅም ላይ የማይውልበትን የትርጉም መጠን ነው። እነዚህም ተግባራዊ መሆንን ከአቅም አንፃር፣ ከእውቀት ጋር በማነፃፀር፣ በአምልኳዊ ከበራ ላይ በእምነት፣ በተደነገጉ ሁኔታዎች ውስጥ የሚታይ እና በተለይም በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በዳንስ እና የድራማ ጥበባዊ ማሳያን ያጎላሉ። በማለት ይገልጻሉ ከዚህ አንጻር ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚተላለፉትን ስርአቶች የቃላት አጠቃቀም፤ የአካል እንቅስቃሴ፤ የመከወኛ ቁሶች አጠቃቀም፤ የከዋኞኝ እና የታዳሚውን ጥምረት፤ የከዋኙን የአካል እንቅስቃሴ ከታዳሚው የሚሰጡ ግብረ መልሶች ባጠቃላይ በክዋኔው ላይ ያሉ የቃላትና ያካል እንቅስቃሴ ድግግሞሽ ምን እንደሚመስል በክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበታል፡፡

## 2.3.2. ስነ ትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብ (Semiotics theory)

ስነ ትእምርት/ምልክቶች ከምን አንጻር እንደተፈጠሩ የሚያጠና ሃሳብ ነው፡፡ ትእምርቱ (ምልክቱ) ፍቺ እንዴት እንደሚፈጥር ማጥናት እንጂ ምን እንደሆነ አይደለም፡፡ ትእምርትን አስመልክተው Aksan (2009፣903) በስነ-ትዕምርት ጽንሰ-ሀሳብ መሰረት ሰዎች በተፈጥሯዊ እና በምሳሌያዊ ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ ተምሳሌታዊ መስተጋብር በአእምሮ ውስጥ ባሉ ምልክቶች በመታገዝ የተፈጠሩ ትርጉም እና እሴቶቹን የሚያጣጥም ሂደት ነው። ትርጉም በሰዎች መካከል ተቃራኒ መስተጋብር ይመሰርታሉ። ቁሶች በራሳቸው ትርጉም የላቸውም፡፡ በማለት ይገልጻል፡፡ በዚህ ሃሳብ መሰረት በየአከባቢው የሚገኙ ትእምርቶች የተለያየ ትርጉም የሚሰጡና ያከባቢው ማህበረሰብ ባህል እና አኗኗር ላይ የተመሰረቱ አከባቢያዊ ትርጉሞች እንደ ሆኑ ነው፡፡ በትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብ አማካይነት የኢሬቻው ስርአት ላይ ማህበረሰቡ ለክዋኔ የሚጠቀማቸውን ቁሶች በስርአተ ከበራው ወቅት የሚጠቀማቸው የአልባሳት ቀለም እና በክዋኔው ወቅት የሚንጸባረቁ ድግግሞሻዊ

ስርአቶች ማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ትርጉም ከክዋኔው አንጻር የሚያስተላልፉት መልእክት ምን እንደሆነ በስነ ትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም Aksan (2009፣903) ስነ ትእምርት ንድፈ ሃሳብ እውነታዎች በምልክት ላይ የተመሰረቱ እና የሚመሩ ናቸው ይላል። የዚህ ጽንሰ ሐሳብ መሠረቱ ትርጉም ነው፡፡ ተምሳሌታዊ መስተጋብር ግለሰቦች በማህበራዊ አካባቢ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በሚያደርጉት የእርስ በርስ መስተጋብር የሚወጡትን ትርጉሞች ይመረምራል፡፡ አንድ ማህበረሰብ በሃይማኖቱም ይሁን በቋንቋው ውስጥ የሚግባባባቸው እውነታን ያዘሉ ትእምርቶችን እንደሚጠቀም የሚያሳይ ነው፡፡

Ronald (2006) ትእምርት አካባቢያዊና ስያሜውም ማህበረሰቡ ባከባቢው ተስማምቶ ትርጉም የሰጠው ሲሆን በሁሉም ያከባቢው ማህበረሰብ የሚታወቅ፣ ተመሳሳይ እሳቤን የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ትእምርቶች በጊዜ እርዝመት ካከባቢያቸው በማለፍ ወደሰፊው ማህበረሰብ እያደጉ ይሄዳሉ በማለት ይገልጻል፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ትእምርቶች በማህበረሰቡ ስምምነት የተፈጠሩ ሲሆኑ ሁሉም ያከባቢው ማህበረሰብ በትእምርቶቹ ትርጉም ማህበረሰቡ ወጥ እና ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ትእምርቶች በመስፋፋትም እያደጉና ወደ ሰፊው ማህበረሰብ በረጅም ጊዜ ውስጥ ይዘታቸውን ሳይ ለቁ ሊስፋፉ ይችላሉ፡፡

Blumer (1969) human forms “meaning” in two ways: (1) Meaning is something attributed to objects, events, phenomenon, etc. (2) Meaning is a “physical attachment” Imposed on events and objects by human. እንደዚ ሃሳብ ገለጻ ትርጉም በሁለት መንገድ ይፈጠራል 1ኛ የሰው ልጅ ለሚጠቀማቸው ቁሶች፣ ለነገሮች እና ለክስተቶች መለያ የሚሰጣቸው በትርጉም ሲሆን 2ኛ ከነገሮች ጋር ባለው መስተ ጋብር የሚሰጣቸው ትርጉም ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ማህበረሰቡ የኢሬቻውን ስርአተ ከበራ ሲከውን ከቁሶች ጋር ባለው መስተ ጋብር አማካይነት ትርጉም ይሰጣል ከቡድኑም ይግባባበታል፡፡

እንደ Blumer (1969) ገለጻ ትእምርቶች በሶስት ነገሮች ይጸናሉ ይላል እነዚህም በቋንቋ፣ በትርጉምና በአስተሳሰብ መርህ ናቸው፡፡ ተምሳሌታዊ መስተጋብር ንድፈ ሃሳብ የትርጓሜውን መርህ እንደ ሰው ባህሪ እውቅና ይሰጣል ቋንቋ በምልክቶች አማካኝነት ለሰው ልጆች ትርጉም ይሰጣሉ እንዲሁም በነዚህ ትርጉሞች የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ያዳብራሉ፡፡ በዚህም መሰረት የሰው ልጅ የተለያዩ ትእምርቶችን የሚያገኘው ቋንቋው

ካለበት ባህል እና ከማህበረሰቡ መንፈሳዊና አለማዊ አስተሳሰብ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ማህበረሰቡ ከባህሉ እና ካከባቢው ላይ በሰረጸው አመለካከት በክዋኔው ላይ ለሚጠቀሟቸው ቁሶች ትእምርት ይሰጧቸዋል በዚህ ጥናትም እነዚህን ጉዳዮች ከማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት እንዲሁም በትውሩ አማካይነት በክዋኔው ላይ ለሚይዟቸው ቁሶች፣ በስርአቱላይ የሚጠቀሟቸው ልዩ ልዩ የሆኑ የአምልኮ ማስፈጸሚያ ቃላቶች፣ የቃላቶች ድግግሞሽ፣ አለባበስ፣ የአካል እንቅስቃሴ በስርአተ ከበራው ላይ የሚከናወኑ ሰርዶ ሳርና የአደይ አበባውን ስንት ቦታ እንደሚያስቀምጡ ሙዳ ሲሉ፣ እግዚኦ ሲሉ የከዋኞቹን የመቆሚያ ቦታ በቁጥር ስንት ጊዜ እንደሚሉ በትእምርታዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ተምሳሌታዊ መስተጋብሮች በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተመስርተው እንደ ሚጸኑ Blumer (1969) (Poloma, 1999: 224-225; Tye &Tye, 1992: 36) በመጥቀስ (ሀ) የሰው ልጅ ለነገሮች ያለውን አመለካከት የሚያዳብረው ለነገሮች በሚሰጠው ትርጉም አማካይነት ነው። (ለ) ትርጉሞች በአከባቢ ላይ የተወሰኑ መስተጋብር ናቸው። (ሐ) ትርጉሞች በሂደት ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ጋር የሚለወጡ ናቸው፡፡ ትዕምርቶች የሰውን ልጅ አመለካከት የሚያሰፉና አከባቢያዊ ስሜት ያላቸው ሲሆኑ በግዜ እርዝመቱስጥ ከሰው ልጅ አስተሳሰብ መለወጥ ጋር ሊለወጡ የሚችሉ ስርአቶች እንደ ሆኑ የሚገልጽ ነው፡፡

Udechukwu (2019:1010) ምልክቶች አንድን ክስተት ወይም ሁኔታ በመወከል፣ በመግለፅ የሚቆሙና የሚያገለግሉ ናቸው። ትዕምርቶች መልእክቶችን ለማስተላለፍ ያገለግላሉ እንዲሁም ትእምርት ሌላ ነገርን ለመተየብ ወይም ለመወከል የቆመ ረቂቅ ቁስ ነው። ትእምርቶች የሰውን ባህሪ ይመራሉ ወይም ይቆጣጠራሉ እንዲሁም ያለፈውን፣ አሁን ያለበትን ወይም የወደፊቱን ክስተት ለማሳየት የሚጠቅሙ ናቸው። ሃይማኖት፣ ሳይንስ፣ ጥበብ፣ ተረት፣ ህልም እና ሥርዓት ሁሉም የትእምርት መገለጫዎች ናቸው። ይህ ሃሳብ የሚያመለክትን በማህበረሰቡስት የሚከናወን ማንኛውም ነገር ቢሆን ከትእምርት ጋር የተያያዙ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

Udechukwu (2019) በአፍሪካ በኢግቦ ማህበረሰብ በትእምርት ላይ ያተኮረ ጥናት ባካሄደው ትእምርቶችን በስምንት ይመድባቸዋል እነዚህም ትእምርቶች የእንስሳት ምልክቶች፣ የስርአተ ከበራ ምልክቶች፣ የቁጥር ምልክቶች፣ የንጉሣዊ ምልክቶች፣ የአያት ምልክቶች፣ የባህል ምልክቶች፣ የሥዕላዊ መግለጫ ምልክቶች፣ የእርግዝና ምልክቶች፡፡

በዋናነት በኢግቦ ማህበረሰብ እንደ ሚታወቁ ይጠቁማል፡፡ ከዚህ Udechukwu ከጠቀሳቸው ትእምርቶች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር የሚገናኙት የስርአተ ከበራ ምልክቶች እና የባህል ምልክቶችን በስፋት በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የተለያዩ ስርአቶች እንደ ሰርዶአበባ ማስቀመጥ የከዋኙን ማህበረሰብ ማህበራዊ ደረጃ ጠብቆ የመቆም የእግዚአታ ድግግሞሽ ቁጥር የቁሶች ትርጉምና በእስፖርታዊ ውድድሮች ላይ የሚሸለሙ የማበረታቻ ቁሶች ያላቸውን ትርጉም በስነትእምርት አማካይነት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 2.3.3. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functionalism theory)

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አንድ የፎክሎር ቅንጣት ለማህበረሰቡ ምን ጥቅም አለው? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ Green (1997) ማንኛውም ፎክሎራዊ ጉዳይ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ጥቅም ሊያስገኙ እንደሚችሉ እና ለማህበረሰቡ የሚያስገኙት ጠቀሜታ ምን እንደሆነ በመመርመር ላይ የሚያተኩር መሆኑን ያሳያል፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ከማህበራዊ ዝምድና ውስጥ ሥርዓትን ለማውጣት የሚሞክሩ ሲሆኑ በርዕሱ ላይ ሶስት አይነት ተግባራዊ አመለካከቶች እንዳሉ Thomas (1997፡386)፤ Sato (2011፡2) በመጥቀስ የገለጸ ሲሆን እነዚህም የመጀመሪያው የMalinowski,ሃሳብ ሲሆን ይህም ሃሳብ የሰው ልጆችን ስነ-ህይወታዊ ፍላጎት በመመርመር ከቡድን ይልቅ ለግለሰቦች ጥቅም የቆመ ነው፡፡ ሁለተኛው የBrown ሃሳብ ሲሆን ይህም ሃሳብ በቡድን ውስጥ ያሉትን ማህበራዊ መዋቅሮች ተግባር ለቡድኑ ያላቸው ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ሦስተኛው የDurkheim ሃሳብ ተግባራዊነት በጋራ የአዕምሮ መዋቅሮች አማካይነት የማህበራዊ ትስስርን የሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ነው።

ከነዚህ ሀሳቦች በመነሳት በሎዴሄጦሳ ወረዳ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚከወኑ ስርአቶችን በዚህ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳቡ በክዋኔው ላይ የሚተላለፉ ስርአቶች ማህበረሰቡን እንዴት እንዳስተሳሰሩት እና ለቡድኑም የሚሠጡትን ጠቀሜታ ለመረዳት ሃሳቡ ግልጽ ሆኖ መረጃ እንዲያስተላልፍ በBrownና በDurkheim ሃሳብ መሰረት ተቃኝቷል፡፡ ይህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚከወነው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚከወኑ እምነታዊ ስርአቶች ማህበረሰቡን እንዴት እንዳስተሳሰሩትና ስርአቱ መቼ መከበር እንደጀመረ፤ ለስርአቱ መከበር መነሻ የሆኑ ሃሳቦች ወይም ተረኮች ምን እንደ ሆኑ ማህበረሰቡን እንዴት በመንፈስ እንዳስተሳሰሩት በተግባራዊ

ንድፈ ሃሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም ለስርአቱ መጀመር መነሻ የሆኑ ሃሳቦች በቃል ተረኮች በማህበረሰቡስጥ ሰርጸው እርስ በርስ በማስተሳሰር ስርአቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እየተላለፈ እንደመጣና ስርአተ ከበራው እንዴት ተደራጅቶ እንደሚቀርብ በዚህ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትኖ ቀርበዋል፡፡

Braw (1952,180) ”The function of any recurrent activity, such as the punishment of a crime,or a funeral ceremony, Is the part it plays in the social life as a whole and therefore the contribution it makes to the maintenance of the structural continuity” ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወኑ ስርአቶች ለማህበረሰቡ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የሚገልጽ ነው፡፡ የኢሬቻው ስርአት ላከባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊና ማህበረ ባህላዊ የመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ተግባር የሚያበረክት ሲሆን ይህንንም ተግባር በዚህ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ በጥናቱስጥ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

Sims and Stephen (2005:177) Functionalism is the strategy or framework that requires us to make meaning of folklore, so if there’s only one meaning, some one has to decide what the one meaning is. ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ለፎክሎር ትርጉም እንድንሰጥ የሚረዳን ስልት ወይም ማዕቀፍ ነው፡፡ ከዚህም ረገድ ባንድ ማህበረሰቡስጥ የሚከወኑ ስርአተ ከበራዎች በሚያከብራቸው ማህበረሰብ ውስጥ እንዴት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲይዙ ያደረጋቸው ሃሳቦች ከምን አንጻር እንደሆነም ተቃኝተው በጥናቱስጥ ቀርበዋል፡፡

# ምራፍ ሶስት፤የጥናቱ ስነ-ዘዴና የመስክ ተሞክሮ

በዚህ ክፍል ስር የጥናቱን መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፤ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፤ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃ ሰጪዎች አመራረጥ፣ ስለ ካልአይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አሰባሰብና የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚተነተኑባቸውን የመተንተኛ ስልቶች በመጠቀም እንዴት እንደቀረቡ የሚገለጽበት ክፍል ነው፡፡

## 3.1 የጥናቱ ስነ ዘዴ

ስለ አንድ ጉዳይ ጥናት ለማካሄድ የሚጠቅሙ ሁለት አይነት ያጠናን ስልቶች እንዳሉ ያለው (1998፣250) ለመስክ ጥናት የሚጠቅሙ ሁለት አይነት የአጠናን ስልት አሉ፡፡ እነዚህም መጠናዊ (quantitative) እና አይነታዊ (qualitative) ናቸው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚለውን ርእስ ለማጥናት የተመረጠው አይነታዊ (qualitative) የምርምር ስልት ነው፡፡ አይነታዊ የምርምር ዘዴዎች በአንድ ውስን ቦታ ስለተከሰተ ነገር ወይም ስለሚከናወን ጉዳይ ጠንካራና ሰፊ ማብራሪያ ለመስጠት እንዲሁም ምስል ከሳች በሆነ መልኩ መልዕክት ለማስተላለፍ የሚያስችል የምርምር ስልት በመሆኑ ተመርጧል፡፡ አይነታዊ የምርምር ስልት በተመራማሪው እና በመረጃ አቀባዩ መካከል ያለውን መስተጋብር እንደ ሁኔታው በመለዋወጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠር የሚችል ሲሆን በዝርዝር ለመድረስ የሚፈለግን መረጃ ለማጣራት እና ለማግኘት የሚያስችል በመሆኑ ተመርጠዋል፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የጥናት ቦታ አመራረጥና መረጃ ያላቸውን ሰዎች በምናይነት መንገድ እንደተመረጠ የሚያሳይ ስልት ነው፡፡

### 3.2.1 የተጠኝ ቦታ አመራረጥ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ ካሉ 22 ቀበሌዎች መካከል ለጥናቱ የተመረጡት 4 ቀበሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ቀበሌዎች ስርአቱ ለሚከወንበት (ለዶኒ አድባር) ካላቸው ቀረቤታና አብዛኛው የቀበሌው ኗሪ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ተሳታፊ በመሆናቸውና ለአላማው ግብ አመቺ ሆኖ በመገኘታቸው ቀበሌዎቹ ለጥናቱ አካላይ ተመርጠዋል፡፡

ለጥናት የተመረጡት በዬንቦ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን የዶኒ አድባር ቅርበት ያላቸውና ለየንቦ ቀበሌ አዋሳኝ ለሆኑ ሶስት ቀበሌዎች አማካይ ቦታ የሚገኝ በመሆኑና ማህበረሰቡም ለስርአቱ ቅድሚያ የሚሰጡ በመሆናቸው በቀበሌዎቹ ስርአቱን የሚያስፈጽሙ የረዥም ግዜ ልምድ ያላቸው አባቶች የሚገኝባቸው እንዲሁም ያከባቢው ማህበረሰብ በስርአተ ከበራው ወቅት ባብዛኛው የሚሳተፉና ስርአቱንም የሚፈጽሙ በመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ቀበሌዎች በስራ አጋጣሚ በቅርበት ስለማውቃቸው መረጃ አቀባዮቹ ያለምንም ስጋት ትክክለኛና የተሟላ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን ማግኘት ስለሚያስችለኝ ነው፡፡

### 3.2.2. የመረጃ አቀባይ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው ናሙና በዋናነት አላማ ተኮር ነው፡፡ የተመረጠበት ምክንያትም ለሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ቅርብ የሆነ ሰው ስርአቱን በመፈጸም እውቀትናና የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸውን በተለይ ስለኢሬቻው ስርአተ ከበራ ሂደት ጥልቅ እውቀት ያላቸውን ግለሰቦች ለመምረጥ አላማየን በትክክል ከግብ ለማድረስ ስለሚረዳኝ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ የተካሄደው  በስርአተ ከበራው ላይ በአካል በመገኘት ባላቸው ወቅታዊ ያከዋወን ችሎታ እና በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የረጅም ጊዜ እውቀትናና ልምድ ያላቸው ሰዎች በጠቋሚ ተመርጠዋል ምክንያቱም እኔ የማላውቃቸውና በእለቱም በስርአተ ከበራው ላይ መገኘት ያልቻሉ ግለሰቦች በትክክል ለማግኘት በአካባቢው በቅርበት የምተዋወቃቸውንና ከተላመድኳቸው ሰዎች በመጠየቅ በጠቋሚ ተመርጠዋል፡፡ በዚህም ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡት እንደመረጃው አሳታፊነት እድሜና ጾታ ስብጥር ለማካተት ሞክሯል፡፡ የተመረጡት ሰዎች ስለ መረጃው እውቀት አላቸው ብዬ ስላመንኩባቸው እና እውቀቱ እንዳላቸው በጥቆማው ወቅት መረጃ ስላገኘሁ ነው፡፡ በተጠኚው አከባቢ ላይ 18 መረጃ አቀባዮችን ስመርጥ 8 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ 10ሩ ደግሞ ንዑሳን መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 5 ሴቶች ሲሆኑ 13ቱ ወንዶች ናቸው፡፡ 3ቱ ሴቶች እድሚያቸው ከ50 ዓመት በላይ ሲሆኑ፤ 2ቱ ከ45 ዓመት በታች ናቸው፡፡ ወንዶቹ ስድስቱ 60 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው፤ ሰባቱ ደግሞ ከ60 ዓመት በታች ሲሆኑ ይህም የተደረገውበዚህ እድሜ ክልሉስጥ የሉ በስርአቱ በቂ እውቀት ያላቸው ሲሆኑ እድሚያቸውም የተወሰነበት ምክኒያት በትላልቅ ሰዎችና በወጣቶች ለስርአቱ ያላቸውን

ጥብቅ መረጃ ለማወቅ ይረዳል በዚህም ላይ አብዛኛውን መረጃ ስለእውቀቱ ጥልቅ እውቀት ካላቸው ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.3. ካልዓይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አሰባሰብ

በዚህ ርእስ ስር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከከለአይ የመረጃ ምንጮች እንዴት እንደተሰበሰቡ የሚገለጽ ክፍል ሲሆን፤ ሂደቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.3.1. ካልዓይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥናቱን የሚደግፉና መረጃ የሚሰጡ ካልዓይ ምንጮች በቀደምት ተመራማሪዎች የተጠኑ ጥናቶች የተጻፉ መጻህፍቶች፣ የታተሙ መጽኄቶችና ያልታተሙ ጽሁፎች ሲሆኑ፤ ከቤተ መጽሀፍት፣ ከመረጃ መረቦችና ከወረዳው የተለያዩ ተቋማት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ መረጃዎቹም ባጠቃላይ ርእሰ ጉዳዩን የሚያጎላምሱ እንዲሁም ስለወረዳው ማህበረሰብ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ መልከዓምድር፣ የአየር ጠባይ፣ የህዝብ ሁኔታ ካርታና ባህላዊ እሴቱን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

### 3.3.2. ቀዳማይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

በፎክሎር ጥናት ትክክለኛና ያልተበረዘ መረጃ የሚገኝበት ነው፡፡ ይህንንም መረጃ ከመስክ ለመሰብሰብ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አሉ እነዚህንም አስመልክቶ ፈቃደ (1991፣90) ሲገልጹ "የመስክ ምርምር በሶስት (3) ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄዱ እንደ ሚችሉ በመግለጽ እነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ምልከታ (observation) ቃለማጠይቅ (interview) እና መጠይቅ (quationare) ናቸው፡፡ በማለት ሲገልጹ MACK (2005፣1) ደግሞ አይነታዊ ምርምር የመረጃ መሰብሰቢያ ዜዴዎች ምልከታ (ovservation)፣ ቃለ-መጠይቅ (intervew) እና አሳታፊ የቡድን ውይይት (focues group discussion) እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በፎክሎር ጥናት ውስጥ የታወቁና መረጃዎቹም በአብዛኛው በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ይሰበሰባሉ በዚህም መሰረት በምልከታ ከዋኙ ማህበረሰብ ማብራራት የማይችላቸውን ለምሳሌ ህጻናት የሚከውኑዋቸውንና በእንሰሳት የሚከወኑ ስርአቶችን ለመመልከትና ተመራማሪው ከርእሰ ጉዳዩ በመነሳት የራሱን ሃሳብ ለመገመት ያስችለዋል

በተጨማሪም ማብራሪያ የሚፈልጉትን ስለ ስርአተ ክዋኔው ይዘት መቼ መከበር እንደ ጀመረና በስርአቱ ላይ የሚከናወኑትን ጉዳዮች ለመረዳትና በምልከታ የተገኙትን መረጃዎች ምንነታቸውን ለማረጋገጥ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በምልከታ ያገኘነውንና በተናጠል ቃለ መጠይቅ  የተሰበሰበውን መረጃ ታማኝነቱን ለማረጋገጥ በተተኳሪ የቡድን ውይይት በድጋሜ ማረጋገጥና መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ባጠቃላይ ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን እና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን በመጠቀም መረጃውን በአላማ ተኮር ከተመረጡ የመረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡

### 3.3.2.1. ምልከታ

ምልከታ ለፎክሎር ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡ ፎክሎር እና ክዋኔ የማይነጣጠሉ ሲሆኑ ፎክሎር  ያለክዋኔ ምሉዕ ሊሆን አይችልም፡፡ የፎክሎር መረጃ ሲሰበሰብ ምልከታን መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ምልከታን በመጠቀም በተፈጥሮአዊ አውዱ ላይ በዋዜማው እና  በጊዜ ኢሬቻው ወቅት በመገኘት የማየውንና የምሰማውን ነገር በስሜት ህዋሳቶቼ በመታገዝ መረጃውን ተፈጥሯዊ ይዘቱን እንደጠበቀ ተሰብስቧል፡፡ ጥናቱ በሚያተኩርበት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ለጥናት በተመረጡት ቦታዎች በመንቀሳቀስ  ከኢሬቻው ስርአተ ከበራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስርአቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

በዋዜማው መስከረም 01/16/2014 በፉርሳ (ከ3፡00- 500)፣ በዬንቦ (5፡30 -7፡30)፣ በዶዴ (8፡00-10፡00) እና በሁሩታ ከተማ (10፡30-12፡30) ሰአት በቀበሌዎቹ በመንቀሳቀስ በልጆች፣ በወጣቶች እና በአዋቂዎች ዘንድ ያለውን ስርአት ለመመልከት ተሞክሯል በድጋሜም 01/16/2015 የመረጃ እጥረት ያለበትን የማጠናከርና የማደራጀት ስራ ተካሂዷል ፡፡ በዚህም መሰረት ልጃገረዶችና ልጆች 6-18 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ ለእንቁጣጣሽ አበባ አየሾይ ጨፍረው ያገኙትን ገንዘብ  በማስቀመጥ በእለቱ መስከረም አስራ ሰባት በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት ከረሜላ ለመግዛት ሲዘጋጁና የሚለብሷቸውን አልባሳት ሲያዘጋጁ በተጨማሪም እናቶች በኢሬቻው ስርአተ ከበራ እለት ጠዋት ተነስተው ለሚያዘጋጁት ፊጫሳ የሚሆኑ የምግብ ዝግጅት ላይ መሳተፍና ቤት ማጽዳት የልጅ አገረዶች ድርሻ መሆኑን ሲያከናውኑ መመልከት ችያለሁ፡፡

**ወጣት ወንዶች፡-** በዋዜማው የተለያዩ ስርአቶችን ያከናውናሉ እነዚህም በእለቱ በከበራው እና በባህላዊ ጨዋታዎቹ ላይ የሚለበሱ አልባሳትን ማዘጋጀት የጉግስ መጫወቻ ፈረሶቻቸውን ማጠብ ውሃ ማጠታትና እርጥብ ሳር እንዲሁም የሚከብዱ ነገሮችን አብዝተው እንዳይበሉ በግቢ ውስጥ ማሰር፣ የፈረስ እቃዎችን ማጌጥና ማጥበቅና ለጉግስ ጨዋታ ማዘጋጀት እንዲሁም በጉግስ ጨወታው ላይ የሚያስፈልጉ ቁስ ጋሻ እና በጦር ምትክ በጉግሱ ወቅት የሚጫወቱበት ቀጫጭን እርጥብ ዘንግ በመቁረጥ ማዘጋጀት ናቸው፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ከመስቀል በአል ጋር በተመሳሳይ ቀን በመዋሉ ለዳመራ የሚሆን እንጨት መቁረጥ የችቦ እንጨት ማዘጋጀትና በእለቱ ከብቶቹን ተከብሮ በቆየ ሳር (kaloo) ሌሊት ለማውጣት እንዲመቻቸው የዳሞቲ ኮርማ ችቦ ያዘጋጃሉ፡፡

**እናቶች**፡- ከሴት ልጆቻቸው ጋር በመሆን እቤታቸውን በማጽዳት በኢሬቻው እለት ጠዋት ለሚያዘጋጁት የፊጫሳ ስርአት ዳቦ ሲጋግሩ፣ የቂንቼ እህል ሲያዘጋጁ ለምግብ የሚሆን ቅቤ ሲያነጥሩና ፊጫሳ ለሚያዘጋጁበት ለጨሌዋ የሚቀቡትን እንዲሁም በኢሬቻው ክዋኔ ወቅት ለአድባሯ የሚቀቡት (ሙዳ) ቅቤ ለማውጣት ወተት ሲንጡ እንደሚውሉ በምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡ የፊጫሳ ስርአት የሴቶች ነው ስለሚባል በቦታው ፍዝ ተመልካች፡፡ በመሆን ስርአቱን በማስታወሻ ደብተር በመመዝገብ ተከታትያለሁ፡፡

**አባቶች፡-** አባቶች በበኩላቸው ስርአቱ በሚከበርበት በዶኒ አድባር በመገናኘት ወደ ቦታው ለሚመጡ የበአሉ ተካፋዮች ስርአተ ከበራው የሚካህድበትን አከባቢ ማስተካከልና ለእንግዶች የሚሆን ቦታ ማመቻቸት በቤታቸውም ለመስቀል እና ለፊጫሳ ስርአት የሚሆን ሰርዶ ሳር፣ ከሴ፣ ጠጅ ሳር፣አሪቲ በማጨድ ለፊጫሳው ለስርአት አንደሚያዘጋጁ በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በክብረ በአሉ ቀን መስከረም 17/2014 ሌሊት ከ9፡30- 10፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ የቀንድ ከብቶቻቸውን ጥጃ ሣይለዩ ለእለቱ ተከብሮ በቆየ ሳር (kaloo) በማውጣት አግጠው በማጥገብ ጠዋት 1፡00- 1፡30 ወደ ጊቢ መልሰው ያስተኛሉ በመቀጠልም እናቶች ፊጫሳውን ካከናወኑ ብኋላ ለወንዶች ቁርስ ለብቻ ይዘጋጃል ምግብ ቀርቦ ሁሉም የቤተሰብ አባል በመመገብ ወደ ኢሬቻው ስርአተ ከበራ ይሄዳሉ፡፡ እኔም በዚህ ስርአት ንቁ ተሳታፊ በመሆን በምግብ ሰአት አብሬ በመመገብና አብሬ ወደ ኤሬቻው ቦታ በመሄድ ለኢሬቻው ስርት የሚሆን ሳርና አዴ አበባ  ሲነቅሉ አብሬ በመንቀል ስርአቱን ንቁ ተሳታፊ በመሆን

በወቅቱ ስርአቱን ካከናወኑ ሰዎች ጋር  በምልከታው ወቅት አብሬ በመሳተፍ ተመልክቻለሁ፡፡

በዶኒ አድባር ስር የኢሬቻውን ስርአት ለማክበር የሚመጣ ሰው ሁሉም ከቤታቸው ይዘው ከሚመጡት የአምልኮ ማስፈጸሚያ ቁስ በተጨማሪ እርጥብ ሳርና አደይ አበባ ከመንገዳቸው በመንቀል ይዘው በመምጣት በአድባሯ ስር የኢሬቻውን ስርአት ከአባገዳዎችና ከአባቶች ኋላ በመሰለፍ ፈረሰኞችም በፈረስ በማጀብ  አድባሩዋን ሁለት ግዜ መሬሆ በማለት ከዞሩ ብኋላ በአድባሯ ስር አበባና ሳሩን በአምስት ቦታ ሲያስቀምጡ ተሳታፊ በመሆን አብሬ አድባሩዋን በመዞር እና እርጥብ ሳር በመያዝ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ስርአቱን ተከታትያለሁ፡፡ ስርአቱንም በመቅረጸ ድምጽ እና በመቅረጸ ምስልና ድምጽ በመቅረጽ አስቀርቻለሁ፡፡

ፈረሰኞቹም የኢሬቻውን ስርአት በፈረስ በማጀብ አብረው አድባሯን ከዞሩ ብኋላ ከፈረስ በመውረድ ኢሬቻውን አስቀምጠው ስርአቱ ሲጠናቀቅና ምርቃቱ ከተጠናቀቀ ወደ ባህላዊ እስፖርት  ሜዳ በመሄድ የፈረስ ጉግስና የሩጫ ጫወታ ስርአቱን በማከነወን የገበጣ ጫወታ፣ የገመድ ጉተታና ኮርቦውን በጦር መውጋት ስርአት ለማከናወን ሲሉ በዝናብ አማካይነት ስርአቱ ሳይከናወን ቢቀርም ይህን ስርአት በ01/17/2015 በድጋሜ ምልከታ በማካሄድ ስርአቱን ተሳታፊ በመሆን መረጃውን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል በሚያሳትፉ ስርአቶች ላይ ተሳታፊ በመሆን የሚነኩትን በመንካት የሚቀምሱት በመቅመስ  የስሜት ህዋሳቶቼን በመጠቀም መረጃውን የሰበሰብኩ ሲሆን ሊያሳትፉኝ በማይችሉ ስርአቶች ለምሳሌ በፈጫሳ ስርአት፣ በሙዳ (አድባሯን ቅቤ መቀባት) እና በምርቃት ጊዜ ኢ-ንቁ ተሳታፊ በመሆን መረጃውን በማስታወሻ ደብተር በመመዝገብ ሰብስቤያለሁ፡፡

በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑ ቁሶች መቅረጸ ድምጽና ምስል፣ መቅረጸ ምስል፣ ማስታወሻ ደብተር እና ብዕር እንዳስፈላጊ ነታቸው በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በስርአቱ ወቅት የማያቸውን አንዳንድ ስርአቶች እንዳይረሳኝ የከዋኙን ስም የሚከውኑትን ስርአትና የሚከወንበትን ሰአት ለመያዝ ማስታወሻደብተሩ ሲጠቅመኝ፣ ስርአተ ክዋኔውንም በቪዲኦ በመቅረጽ እና በፎቶ ለማስቀረት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

### 3.3.2.2. ቃለ-መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ ለጥናቱ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ በተመረጡ ቦታዎች ካሉ መረጃ አቀባዮች ጋ በአካል ፊት ለፊት በመገናኘት ቃለ-መጠይቁን በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ነው፡፡ ለጥናት መረጃ ከማህበረሰብ ሲሰበሰብ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶችን መጠቀም ያስፈልጋል እነዚህንም የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶች አስመልክተው Sapsford and Jupp (2006፤*93)* 'በቃለ-መጠይቁ ወቅት ለሚደረጉ ውይይቶች በማስታወሻ ደብተር ብቻ ከመውሰድ በቴፕ ሪከርድ ጭምር ቢወሰድ መረጃውን በተሟላ መልኩ በርጋታ ወደወረቀት ለማስፈር ይረዳል፡፡"ይላሉ በመሆኑም ቃለ-መጠይቅ በማደርግበት ወቅት ያገኘዋቸውን መረጃዎች በመቅረጸ ድምጽ፣ መቅረጸ ምስልና ማስታወሻ ደብተር ተጠቅሜያለሁ፡፡ ቃለ-መጠይቅ ከመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መካከል አንዱ በመሆኑ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ሆኗል ይህንንም አስመልክተው ያለው (2006፤180) "ጠያቂው በሚያጠናው ችግር ዙሪያ ጠቃሚ መረጃ ያስገኙኛል ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች በፈለገውና ለተጠያቂው ይመቸዋል ብሎ የሚገምተውንና ያመነውን መረጃ የሚጠይቅበት ነው፡፡" ብለው ባቀረቡት መሰረት ለጥናቱ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ይጠቅመኛል ብዬ ባሰብኩት መሰረት የኢሬቻው በአል አከባበር ሂደት ምን እንደ ሚመስል፣ ስርአቱ መቼ መከበር እንደ ጀመረ ማህበረሰቡ በስርአቱ መከበር የሚያገኙት ጥቅም ምን እንደሆነ፣ አድባሯ ዶኒ የሚለውን ስያሜ መች እንዳገኘች፣ በከበራው ወቅት የሚይዟቸው ቁሶች ቅርጽና ይዘት ምን እንደሚያመለክት፣ የቃላት እና የአካል እንቅስቃሴ መደጋገም ያላቸው ትእምርት ምን እደሆነና ወ.ዘ.ተ ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በወቅቱ ስርአተ ከበራው ሲከበር የኮሮና ችግር በመከሰቱ የእርድ ስርአት አልተከናወነም በዚህም የእርድ ስርአትና በርካታሰዎች ለመሳተፍ የተከለከለ በመሆኑ በመረጃ ስብሰባው ወቅት በነጻነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ በማሰብ ነጻ ቃለ መጠይቅ እና ከፊል ነፃ ቃለ መጤቅን ተጠቅሜለሁ በዚህም መረጃ አቀባዮቼ ምንም ሳይጨነቁ ነጻ ሆነው የሚያቁትን መረጃ እንዲሰጡኝ በማሰብ ሲሆን ከርእሰ ጉዳዩ ሲወጡ ለማስታወስ እና በሚፈለገው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ብቻ እንዲወያዩ ለማድረግ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 3.3.2.3.ተተኳሪ ቡድን ውይይት

የቡድን ተኮር ውይይት ስለሚጠናው ጉዳይ መረጃ ያላቸውን ሰዎች በቡድን በማወያየት መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ነው፡፡ የቡድን ተኮር ተወያዮችን ቁጥር መወሰን ያስፈልጋል የቁጥሩንም መጠን በተመለከተ ያለው (2011፡191) እና MACK (2005፡56) ሲገልጹ ቡድን

ተኮር ውይይት የሚካሄደው በችግር ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳ ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ሲሆን የተሳታፊዎች ብዛት የተለመደው ከስምንት (8) እስከ አስር (10) ሰዎች ሲሆን ቢበዛ አስራ ሁለት (12) ነው። በማለት ይገልጻሉ፡፡

በተተኳሪ ቡድኑም የተለያዩ ሰዎች በአንድ ላይ በመሆን ስለ አንድ ጉዳይ እንዲወያዩና መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ አንዱ የሳተውን አንዱ እንዲያስታውስ በማድረግና መረጃውን ለማመሳከር የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ መረጃ አቀባይ ሰዎች ከየቀቤሌዎቹ በመለየት በሶስት ዙር ተተኳሪ ቡድን አካሂጃለው፡፡ የተሳታፊዎችን ብዛት በአንደኛው ዙር ስምንት (8)ሲሆን፤ በሁለተኛው ዙር ስምንት(8) እና በሶስተኛው ዙር ዘጠኝ(9) ሰዎችን  አድርጌ አወያይቻለሁ፡፡ እነዚህን በማደራጀት ለሶስት ጊዜ እንዲወያዩ በማድረግ በምልከታ ጊዜ ግልጽ ያልሆኑልኝን ስርአቶች እና በቃለ-መጠየቅ ወቅት የተለያየ ሃሳብ የተንጸባረቀባቸውን ጉዳዮች በተተኳሪው ቡድን የማጣራት ሂደት በማድረግ ትክክለኛነታቸውን አረጋግጫለሁ፡፡ በተጨማሪም የኢሬቻውን ስርአት አስመልክተው በማህበረሰቡስጥ የሚነገሩና አዲስ የሆኑ መረጃዎችን በዚህ በተተኳሪ ቡድን ውይይት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 3.4. የጥናቱ መረጃ አተናተንና አተረጓጎም ዘዴ

ትንተና ሲባል የተሰበሰቡ መረጃዎች ተገቢውን ፍቺና ትርጉም እንዲይዙ የሚደራጁበት ሂደት ሲሆን ከቀዳማይና ካልዓይ መረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዴት ተተንትነው እንደቀረቡ የሚጠቁም ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ሲሆን፤ በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ቅደም ተከል በመጠበቅ እንደመረጃው ሁኔታ በማደራጀት ትረካዊ ስልትን በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚህም ተጠኚው ማህበረሰብ ስለ ኢሬቻ ስርአተ ከበራ  እና ስለ ዶኒ አድባር መረጃዎችን ግልጽ በሆነ መንገድ እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ለምንና በማን አማካይነት ያከብራሉ (ይከውናሉ) የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡፡ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተገኙ ጥሬ መረጃዎች ቀዳማይ መረጃዎችን ለማጠናከር የገቡ ሲሆኑ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ከተገኘው መረጃ ጋር ያላቸውን ጥምረት ለማሳየት ሞክሯል፡፡

የጥናቱ ትኩረት የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ሲሆን ይህ ስርአት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥረውን አንድነትና ለማህበረሰቡ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ለማሳየትና በአከባቢው የሚነገሩ ቃል ተረኮች በማህበሰቡ ዘንድ የፈጠሩትን አንድነትና ጥምረት ለማሳየት ተግባራዊ ቲዮሪን ተጠቅሟል፡፡ ስነ-ትእምርታዊ ቲዮሪን በመጠቀም በስርአተ ክዋኔው ላይ የሚጠቀሟቸውን ቁሶች ቅርጽና ይዘት እንዲሁም በስርአቱ ላይ ያሉ የነገሮች ድግግሞሽ ትርጉማቸው ምንድነው የሚለውን ለማሳየት የሚረዳ ነው፡፡ የስርአቱን አከዋወን ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ያለውን በቅደም ተከተል ጠብቆ ያለውን ያከዋወን ሂደት ለማስረዳት ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ለመተንተንና ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 3.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ጥናት ለማካሄድ በመጀመሪያ ስለተጠኘው ማህበረሰብ የአኗኗር ዘዬ፣ ባህልና ወግ ልማድ፣ የአካባቢውን መልክዓምድራዊ ሁኔታና የአየር ጠባይ ማወቅ ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብና መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ይረዳል፡፡ እኔም ለጥናት በመረጥኩት ማህበረሰብ አቅራቢያ በማደጌና በስራ አጋጣሚ ማህበረሰቡን በማወቁ ለማህበረሰቡ የእንግድነት ስሜት ሳይሰማኝ ያከባቢውን ማህበረሰብ ባህልና የአኗኗር ሁኔታ ለማወቅ፣ ከመረጃ አቀባዮች ጋር በቀላሉ ለመግባባትና መረጃ አቀባይ ለመምረጥ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮልኛል፡፡

ምልከታ ለማካሄድ በዋዜማው እና በስርአተ ከበራው ወቅት መረጃ ስሰበስብ የገጠሙኝ ችግሮች በቤት ውስጥ እና አድባሩ ጋ የሚከወኑ ስርአቶች በተመሳሳይ ሰአት በመከወናቸው ባንድ ቀን ለመመልከት የሰአት እጥረት ስለገጠመኝ ሁሉንም ስርአቶች ለመመልከት ስል ሰአቱን በመከፋፈልና በመንገድ ሳዐት ሳይባክን ሁሉንም ስርአት ለመመልከት ይዞኝ ካንዱ ቀበሌ ወደሌላው ቀበሌ የሚሄድ ሞተረኛ በመያዝ ተዘዋውሬ ሰርቻለሁ፡፡ 06/01/2014 በአራቱም ቀበሌዎች በመገኘት በዋዜማው የሚከናወኑ የቅድመ ኢሬቻውን ስርአት መከታተል የቻልኩ ሲሆን በድጋሜ 01/16/2015 በየንቦ ቀበሌ ብቻ አንድ ቦታ በአድባሩ አቅራቢያ በመሆን በቤትና በአድባሩ ስር የሚከናወኑትን ቅድመ ዝግጅቶች መመልከት ተችሏል፡፡

ሌላው አስቸጋሪ ሁኔታ የገጠመኝ በወቅቱ የኮሮና በሽታ እንዳዲስ እየተስፋፋ ስለሆነ ተጠንቀቁ ምንም አይነት ሰው በአንድ ቦታ መሰባሰብ የለበትም ማንኛውም ሰው በዚህ

ወቅት ተሰብስቦ ቢገኝ ካንድ አመት እስከ አንድ አመት ከመንፈቅ በእስራት እንደሚያስቀጣና በገንዘብም ካንድ ሺህ እስከ ሁለት ሺህ ብር እንደ ሚያስቀጣ በመነገሩ አብዛኛው ማህበረሰብ በቤቱ የሚያከብረውን ስርአት ካከናወነ ብኋላ በጊዜ ከበራው በአድባሩ ስር የሚከናወኑ ስርአቶችን ለማክበር ሳይሰባሰቡ በመቅረታቸው እኔም በቦታው በመገኘት ይህንንም ችግር በአካባቢው ያሉ እና ባጋጣሚ አዋጁን ያልሰሙ ሰዎች በመምጣታቸው የተወሰኑ ከዋኞች ስርአቱን ሲያከናውኑ ለመመልከት ችያለሁ በተጨማሪም በድጋሜ በ2015ዓ.ም በመገኘት ስርአቱን ለመመልከት የሞከርኩ ሲሆን በእለቱ የኢሬቻውን ስርአት ከበራ ለማክበር የወጣው ማህበረሰብ ስርአቱን የሚመሩት ሽማግሌ አቶ ተሸመ አለሙ በመቅረታቸው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊዋ በአድባሩ ስር የሚከበረው ስርአት ይቅር በማለት ቀጥታ ወደ ባህላዊ እስፖርት መጫወቻ ሜዳው በመሄድ የሰእፖርት ስርአቱን በማስጀመር በአድባሩ ስር የሚካሄደውን ስርአት ሳይከናወን ቀርቱዋል፡፡ ይህንንም ስርአት ለመረዳት ስል በተወሰኑ ከዋኞች የተካሄደውን ስርአት በመመልከትና የእርድ ስርአቱ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ያህል በቀጥታ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ተማልተው ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም በ2014 በአከባቢው ላይ የጣለው ከፍተኛ ዝናብ ባህላዊ ጫወታዎች ገበጣ፣ የገመድ ጉተታ፣ የጦር ውርዋሮና የኮርቦ ውርዋሮ የመሳሰሉት ጨዋታዎች ለማካሄድ አስቸጋሪ በመሆኑ በሰአቱ የፈረስ ጉግስና የሩጫ ጨዋታ ስርአት ብቻ ስመለከት የቀሩትን ባህላዊ ጨዋታዎች ለመመልከትና ሁኔታውን ለማጣራት ባለመቻሌ በ2015 በድጋሜ በመገኘት ባህላዊ እስፖርቶቹን ተከታትዬ አሟልቻለሁ፡፡ ሌላ አስፈላጊ የሆኑና በምልከታ ያልተገኙ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ ወቅት በአከባቢው በመዘዋወር መረጃውን ለመሰብሰብ አስቸጋሪ የሆነብኝ ጉዳይ ባከባቢው ላይ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ስጋት በመፈጠሩ በአከባቢው እንደልብ ለመዘዋወርና መረጃ ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ቢሆንም በአከባቢው ያለውን ስጋት የመንግስት የጸጥታ አካላት በመግበት መውጫ መግቢያ መንገድ ላይ ጥበቃ በማድረግ ወደ አከባቢው እንግዳ ሰው እንዳይገባ በመደረጉ ለጊዜው ከጸጥታ ችግር ጋር ያለው ውጥረት ሲረጋጋ በመጠበቅ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

## 3.6. የመስክ ተሞክሮ

ይህ ጥናት በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ አራት ቀበሌዎች ማለትም በቱሉ የንቦ፣ በፉርሳ፣ በዶዴ እና በወረዳው ዋና ከተማ በሁሩታ ላይ ተካሂዷል፡፡ ይህን ጥናት ለማካሄድ በተመረጠው ቦታ ላይ የአራት ጊዜ የመስክ ጉብኝት ተካሂዷል፡፡ በመጀመሪያው የመስክ ተሞክሮ ለ15 ቀን ከመስከረም 8/2014ዓ/ም እስከ መስከረም 23/2014ዓ/ም ድረስ፤ የሁለተኛው ዙር ከግንቦት 2/2014ዓ/ም እስከ ግንቦት 20/2014ዓ/ም፤ ሶስተኛው ዙር ከሰኔ 1/2014ዓ/ም እስከ ሰኔ 20/2014ዓ/ም፣ አራተኛው የመስክ ጉብኝት የተካሄደው የቀሩ መረጃዎችን ለማሟላት የተካሄደ ሲሆን ይህም ከነሃሴ 21/2014ዓ/ም እስከ 17/01/2015 ድረስ የተደረገ የመስክ ጉብኝት ነው፡፡ ወደመስክ ከመሄዴ በፊት ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑ መቅረጸ ድምጽና ምስል እና ማስታወሻ ደብተር በማሟላት በወረዳው ውስጥ በተለያዩ ቢሮዎች የማውቃቸውን ሰዎች ትብብር በመጠየቅ ስለወረዳው አጠቃላይ መረጃ የማገኝባቸውን ተቋማት በመምረጥ ከመስከረም 8/2014 ዓ/ም እስከ 23/01/2014 ዓ/ም ድረስ የወረዳውን የህዝብ ብዛት፣ መልካምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት ሁኔታ፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና የተለያዩ ባህላዊ እሴቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን መስከረም አስራ ሰባት የሚካሄደውን የኢሬቻ ስርአት በዋዜማውና በእለተ ከበራው ወቅት በመገኘት ምልከታ ተካሂዷል፡፡

የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የሚካሄደው መስከረም17 በመሆኑ በዋዜማው ምልከታ ለማድረግ እንዲ መቸኝ 10/01/2014ዓ/ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰአት በመነሳት በቱሉ የንቦ፣በጉዴልቻ፣ በፉርሳ እና በሁሩታ ከተማ በመገኘት በማቃቸው ግለሰቦችና ለኢሬቻው ስርአት በሚዘጋጁ ሰዎች ቤት በመገኘት ስለምሰራው ጥናት አላማ በማስረዳት በዋዜማው ያለውን ስርአት መመልከት እንደምፈልግ እና በእለቱም የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ በመገኘት መከታተል እንደምፈልግ በማሳወቅ አስፈቀጄ ቀጠሮ በመያዝ በስርአተ ከበራው ተመልሻለሁ በዋዜማውም መስከረም 16/2014 ከጠዋት 2፡00 ሰአት ጀምሮ በየቀበሌዎቹ ለሁለት ለሁለት ሰአት የቆየ ምልከታ ተካሂዷል፡፡

ቀድሜ በወረዳው ውስጥ ካሉ ተቋማት የሰበሰብኩዋቸውን መረጃዎች ለማጠናከር በድጋሚ ከ20/01/2014 ጀምሮ ለሶስት ቀን ከተለያዩ ተቋማት የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በየተቋማቱ በመጠየቅ አሟልቻለሁ፡፡

**ሁለተኛ ዙር፡-** የመስክ ስራ የወጣሁት ግንቦት 2/2014 እስከ ግንቦት 20/2014 ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ ይገፔ ነው፡፡ በወረዳው ከሚገኙ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም ለወረዳው ጸጥታና ደህንነት ቢሮ በማቅረብ ጥናቱ ለሚካሄድባቸው ቀበሌዎች የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ በነጻነት ከቀበሌዎቹ አስተዳዳሪዎች በመገናኘት እና በመተዋወቅ በወቅቱ ከኦነግ ሸኔ ጋር በተያያዘ ካለው ስጋት የማያውቀኝ ሰው በጥርጣሬ እንዳይመለከተኝ ደብዳቤው ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቶልኛል፡፡ ከ02/09/2014ዓ/ም እስከ 08/09/2014 ዓ/ም ለመረጃ አቀባይነት ከተመረጡ መረጃ አቀባይ ጋር ስለጥናቱ አላማ ማስረዳት ስለ ስርአተ ከበራው አካሄድ እንዲያስታውሱ አንዳድ ጥያቄዎችን በማንሳት እንዲያስቡበት በማድረግ መረጃ ለመቀበል ቀጠሮ በመያዝ ከ10/09/2014 ዓ/ም እስከ 20/09/2014 ዓ/ም ድረስ አድባሯ መቼ ዶኒ የሚለውን ስያሜ እንዳገኘች ባከባቢው ሰፍረሮ የነበረው ማህበረሰብ በአድባሯ ስር የኢሬቻውን ስርአት ከመቼ ጀምሮ ማክበር እንደጀመረ፤ በኢሬቻው ክዋኔ ምን ምን ስርአቶች እንደሚከናወኑና በከበራው እለት እናቶች የሚያዘጋጁት ፊጫሳ ከኢሬቻው ስርአተ ከበራ ጋር ምን እንደሚያያይዘው ከስርአተ ከበራው ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ባህላዊ ጫወተወዎች ማለትም ፈረስ ጉግስ፣ ሩጫ፣ ገመድ ጉተታ፣ የጦር ውርዋሮና የገበጣ ጫወታ ከኢሬቻው ስርአተ ከበራ ጋር ምን ያያይዛቸዋል የሚሉትን መረጃዎች በተናጠል ቃለ መጠይቅ ለመሰብሰብ ተሏል፡፡


**ሶስተኛ ዙር**፡- የመስክ ቆይታ ከሰኔ 01/2014 ዓ/ም እስከ ሰኔ 15/2014 ዓ/ም ድረስ የተካሄደ ሲሆን በዚህ ዙር በምልከታ እና በተናጠል ቃለ መጠየቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማጣራት፣ የማጠናከርና ያልተሟሉ መረጃዎችን የማሟላት ስራ የተሰራበት ነው፡፡ በዚህም ወቅት የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በአራቱ ቀበሌዎች ያሉ መረጃ አቀባዮቹን በማሰባሰብ የሶስት ጊዜ የቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዷል በዚህም በቱሉ የንቦ እና በፉርሳ የሚገኙትን እዛው በቀበሌው አዋሳኝ በማሰባሰብ 05/10/2014 ከጠዋት 3፡00ሰአት እስከ 6፡00 ሰአት 8 መረጃ አቀባዮችን በማወያየት መረጃውን የሰበሰብኩ ሲሆን ሁለተኛውን የቡድን ውይይት 8/10/2014ዓ/ም የተደረገ ሲሆን በዚህም በዶዴና በሁሩታ ያሉትን መረጃ አቀባዮች በአንድ ላይ ከቀኑ 4፡00 ሰአት እስከ 6፤00 ሰአት ድረስ ሰምንት(8) ሰዎችን በማወያየት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የመጨረሻው የቡድን ተኮር ውይይት የተካሄደው ቅዳሜ 11/10/2014 ከአራቱም ቀበሌዎች ቁልፍ መረጃ አቀባይ የሆኑትን ወደከተማ ለገበያ በሚመጡበት ቀን የተደረገ ሲሆን በዚህም ከ5፡00ሰአት እስከ 7፡00 ሰአት ድርስ 9 ሰዎችን

በማሳተፍ የተካሄደ ውይይት ነው፡፡ **አራተኛው ዙር ከ**21/12/2014ዓ/ም እስከ 17/01/2015ዓ/ም የተካሄደ የመስክ ቆይታ ሲሆን በዚህ በአራተኛው ዙር የመስክ ቆያታ ለማግኘት አስቸጋሪ የሆኑ የዘፈን መረጃዎችን እና በስርአተ ከበራው ወቅት በ2014 ያልተገኙ መረጃዎች በድጋሚ በመስክ ምልከታ ተሰብስበው የጠሚሉበት እንዲሁም በተናጠልና በቡድን መረጃ ለሰጡኝ ምስጋና በማቅረብ የመስክ ቆያታዬን አጠናቅቄ ቀድሜ በተናጠል ካገኘዋቸው መረጃዎች ጋር በማመሳከር እና ትክክለኛነታቸውን በማጣራት የተለያየ ሃሳብ የያዙትንም ቀጥታ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ባገኘዋቸው መረጃዎች መሰረት በማስተካከልና በማደራጀት የትንተና ስራው ተካሂዷል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች የመረጃ አቀባዮቹን የስራ ሰአት ሳይነኩ በእረፍት ቀናቸው እና በበአል ቀናት የተካሄዱ ናቸው፡፡ በጥናቱም ባጠቃላይ የተጠኝው ማህበረሰብ ቦታ ካርታና አጠቃላይ ዳራ የቀረበበት ነው፡፡

# ምእራፍ አራት፤ ጥናቱ የሚደረግበት አከባቢ መልካ ምድራዊና ማህበረ ባህላዊ ገጽታ

በዚህ ክፍል ስለተጠኘው ማህበሰብ አከባቢ ካርታ ፣ያየር ንብረት፣ ከዋና ከተሞች ያለው እርቀት የማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ማህበረ ባህላዊ ዳራና አጠቃላይ ስለ ወረዳው ዳራ የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡

## 4.1. ካርታዎች




ጥናቱ የሚካሄድበትን ቦታ የሚያሳይ ካርታ

## 4.2.የሎዴ ሄጦሳ ወረዳ አጠቃላይ ዳራ

በዚህ ክፍል የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ስለሆነው ወረዳ አጭር መግለጫ የሚቀርብበት ሲሆን በዚህም፣ የአየር ጠባይና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ባህላዊ የሽምግልና ስርአት፣ ስለሲንቄ ስርአት፣ ጉዲፈቻ፣ ስለ ባህላዊ ምግብና አልባሳት፣ ስለባህላዊ የጋብቻ ስርአት ምን እንደሚመስል በአጭሩ ለመግለጽ ተሞክረሯል፡፡

### 4.2.1. የወረዳው አጭር መግለጫ፣ አየር ጠባይ፣ መልክዐ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በምስራቅ አርሲ ዞን በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ነው፡፡ የወረዳው አዋሳኞች በሰሜን የዶዶታ ወረዳና የስሬ ወረዳ፤ በምስራቅ የዲክሲስ ወረዳ፣ በደቡብና በምእራብ የሄጦሳ ወረዳ ያዋስኑታል፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦች ይገኛሉ እነዚህም የሻያ የተፈጥሮ ደን እና ፀበል፤ የራስ ብሩ ቤት መንግስት የኣባ ጭሪ

ፏፏቴ፣ የእግዜር ድልድይ (በተፈጥሮ በወንዙ ላይ አልፎ ተጋጥሞ የሚገኝ ገደል) ናቸው፡፡ ወረዳው ለመኖሪያ ምቹ ያየር ጸባይ ያላቸው ለሰው ልጆች መኖሪያ የሚሆኑ 19 የገጠር ቀበሌዎችና 3 የከተማ መስተዳድር ቀበሌዎች ይገኙበታል፡፡ ወረዳዉ ከዞኑ ዋና ከተማ ከአሰላ በስተምስራቅ 39 ኪ/ሜ፣ ከአዲስ አበባ 164 ኪ/ሜ፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ከአዳማ ደግሞ 64 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው ሁሩታ፣ አርብ ገበያ እና ሊጋባ የሚባሉ ሶስት ከተሞች በስሩ አካቷል፡፡

ሁሩታ የወረዳው ዋና ከተማ ስትሆን ስያሜውን ያገኘችው ጥንት በስፍራው በሚመላለሱ ነጋዴዎች ከባሌ ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱና ከአዲስ አበባ የሚመለሱ ነጋዴዎች ሲገናኙ ሽፍቶቹ አሉ በማለት ሲጠያየቁ ቀድመው ቦታውን ያለፉት ቁጥቋጦ ውስጥ (huraa kessa jiruu) ከሚለው የኦሮምኛ ቃል በመነሳት ሁሩታ ብለው እንሰየሙት ይናገራሉ ሁለተኛው ስያሜ የተሰጠው ከተማዋ በሁለት ወንዞች የተከበበች በመሆኗ ባከባቢው የሚኖሩት የአርሲ ኦሮሞች ከብቶቻቸውን ሲያሰማሩ አከባቢውን ሁራ (huuraa) በማለት ይጠሩት እንደነበር ይነገራል ከዚህ ቃልም በመነሳት ሁሩታ የሚል ስያሜ እንደሰየሚት ይነገራል፡፡ ከተማዋ የተቆሮቆረችው 1903 ዓ/ም በዐጼ ሚኒሊክ ዘመነ ምግስት ነው፡፡ በአከባቢው የሚገኙ ሰዎች በመሰባሰብ ይገበያዩና ይለዋወጡ እንደ ነበርም (የሁሩታ ከተማ መዘጋጃ ቤት መረጃ ያሳያል፡፡)

የሎዴ ሂጦሳ ወረዳ አየር ጠባይና መልክዐ ምድራዊ ሁኔታን በተመለከተ የወረዳው ግብርና ቢሮ እንደሚያመለክተው የመሬት ስፋት **46,000** ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን ይኸውም 25,940 ሄክታር ለእርሻ አገልግሎት የሚውል መሬት፣ 4704ሄክታር ለግጦሽ የሚውል መሬት፣ 3405 ሄክታር በደን የተሸፈነ መሬት፣ ድንጋያማ እና ለግዜው ጥቅም የማይሰጥ 2570 ሄክታር፣ በውሃ የተሸፈነ 4891ሄክታር፣ ገደላማ እና ወጣ ገባ የሆነው 4000፣ ለተለያየ ግንባታ የሚውሉ 3060ሄክታርመሬት ነው፡፡

የሎዴ ሂጦሳ ወረዳ ከባህር ጠለል በላይ ከ1,700 እስከ 3,060 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን መካከለኛ ከፍታውም 2,900 ሜትር ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ወረዳው የተለያዩ የአየር ጠባይ ባለቤት ሲሆን ከዚህ ውስጥም 5% ቆላ 51% ወይና ደጋ 44% ደጋ ናቸው፡፡ የሙቀት መጠኑም $10^0$c እስካ $25^0$c የሚደርስ የሙቀት መጠን ያለው ሲሆን አመታዊ የዝናብ መጠን በአማካይ ከ800 እስከ1400 ሚሜ ያገኛል፡፡ (የሎዴ ሂጦሳ ወረዳ ግብርና ቢሮ 2014ዓ/ም ሪፖርት ያሳያል)

መልካ ምድራዊ አቀማመጢ ሜዳማ፣ ተራራማ፣ ወጣገባና ሸለቆአማ ሲሆን የአፈር አይነት ቀይ አፈር፣ ጥቁር አፈር እና ቡናማ መልክ ያለው አፈር ይገኝበታል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው እንደወረዳው ግብርና ጽ/ቤት (2214) ህዝቦች ከ86% በላይ በግብርና 14% በንግድና በከተማ ግብርና የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ በወረዳው ውስጥ በስፋት የሚመረቱ ሰብሎች ፍራፍሬዎችና አትክልቶችን ጨምሮ  ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣ኑግ፣ ተልባ ሽንኮራ አገዳ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ማንጎ፣ ሙዝ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ቲማቲምና ድንች በስፋት የሚገኙ ሲሆን ስንዴና ገብስ ምርት ሰፊውን ቦታ ይይዛል፡፡(የሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ግብርና ቢሮ 2014ዓ/ም ሪፖርት ያሳያል)

የወረዳው አየር ጸባይ አብዛኛውን ክፍል የያዘው ወይና ደጋ እና ደጋ በመሆኑ በወረዳው በርካታ እ ንሰሳት ይገኙበታል እነዚህም የዳልጋ ከብት 184300፣ በግ 298820፣ ፍየል 64335፣ ፈረስ10635፣ በቅሎ 2183፣ ዶሮ 297562 በወረዳው እንደሚገኙ (የእንሰሳት ሃብት ጥበቃ ቢሮ 2013 ሪፖርት ) ያመለክታ፡፡

### 4.2.2. የህዝብ ሁኔታ፣ቋንቋና ሀይማኖት

CSC(central Statistic agency) እንደሚያመለክተው የሎዴሄጦሳ ወረዳ  ህዝብ ብዛት ወንድ 78834 ሴት 82052 ሲሆን ባጠቃላይ 160886 ነው፡፡ ከዚህም መካከል በገጠር የሚኖረው ህዝብ ብዛት 130318 (86.4%) የከተማው ህዝብ ብዛት 30568 (13.6%) ሲሆን ከዚህ  85% የሚሆነው ማህበረሰብ በጥምር ግብርና በእርሻና በአርብቶ አደርነት ሲተዳደር 15% ደግሞ በመንግስት ስራና በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡

በወረዳው የሚኖረው ህዝብ የኦሮሚፋ፣ የአማርኛ እና የስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ ኗሪውም ማህበረሰብ የኦሮሞ 50%፣ የአማራ 40%፣ ስልጤ 4%፣ እና የተለያዩ ብሄረሰቦች 6% የሚገመቱ ይገኙበታል፡፡ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው የኦሮሞው 50% እና የአማራው 40% ናቸው፡፡ (የሎዴ ሄጦሳ ማህበራዊ እና ስታቲክስ ኤጀንሲ ሪፖርት2014 ዓ/ም) ሲሆኑ

50%፣ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ፣44% ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮችና የፕሮቴስታንንት እምነት ተከታዮች5%፣ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች1%፣ ናቸው፡፡ 27----

አድባራት 1 ገዳም በድምሩ28 አድባራትና ገዳማት እንዲሁም 85 መስጅድ ይገኝበታል፡፡ እንደ ሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም የቅርስ ጥበቃ (2012)

- በወረዳው የእስልምና የክርስትና የፕሮቶቴስታንት እምነት ተከታይ ህዝቦች የሚኖሩበት ሲሆን፤ ማህበረሰቡ ከእነዚህ ሀይማኖቶች በተጨማሪ ሌሎች ልማዳዊ እምነቶች አሏቸው እነዚህም እምነቶች በቃልቻ/ጠንቋይ/ ፣በአድባር፣ ጨሌ(አቴቴ) እና ቦረንትቻ መንፈስ ማመን የመሳሰሉ እምነቶችም ባከባቢው ይገኛሉ፡፡

- **ጠንቋይ (ቃልቻ) የዛር መንፈስ (ውቃቢ) ባላቸው ሰዎች ማመን**

በማህበረሰቡ ውስጥ ሰዎች የተለያየ ችግር ሲገጥማቸው፤ ጤና ሲያጡ /ሲያማቸው/፣አዝመራ ሲጠፋባቸው ከብት ሲሰረቅባቸው ወደ ጠንቋይ በመሄድ በሽታቸውንና የገጠማቸውን ችግር መፍትሄው ምን እንደሆነ ለማወቅ ወደ ጠንቋይ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ጠንቋዩንም በመጠየቅ የተለያየ አምልኳዊ ስርአቶችን ይፈጽማሉ በዚህም ምድራዊ ፈጣሪ ነው በማለት ያምናሉ ጠንቋዩ አድርጉ የሚላቸውን ያደርጋሉ፣ አምጡ የሚላቸውንም ይሰጣሉ፡፡ ከሰማይ በታች ያለውን ሁሉን የሚያውቅ አርገው ይወስዳሉ ከፈጣሪም በታች ጠባቂያቸው እንደሆነ አድርገው ያስቡታል፡፡ ጠንቋዮች አብዛኛውን ጊዜ የዛር መንፈስ ያለባአው ሰዎች ናቸው፡፡ በአሁን ሰአት አልፎ እልፎ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ስርአቶች አስተምህሮ ማህበረሰቡ በሙተው ጠንቋይ የሚከተለው ሰው ብዛት እየቀነሰ ነው፡፡

- **በአድባር፣ ጨሌ(አቴቴ) እና ቦረንትቻ መንፈስ ማመን**

አብዛኛው ማህበረሰብ በግብርና ህይወቱስጥ የሚኖር በመሆኑ የኢኮኖሚው ዋልታ የሆኑትን እና አርሰው የሚያበሉትን እንሰሳቶቹን፣ ልጆቹን እና የራሱን ጤና ጠባቂ በማድረግ ለአድባር ፣ለጨሌ(አቴቴ) እና ቦረንትቻ ትልቅ ቦታ በመስጠት ያመልካሉ፡፡ አቴቴ በአመቱስት ለዘመን መለወጫ፣አዲስ ምርት ወደቤት ሲገባ እና ሰኔ ዘር ከቤት ሲወጣ የፈጫሳ ስርአት ያደርጋሉ፡፡ አድባር ዝናብ ግዜውን አሳልፎ ሲዘገይ እና ባመቱስት በግንቦት እና በጥቅምት ወር ስርአተ ከበራ በማድረግ ለልጆች፣ ለከብቶች እና የእኛን ጤና ይሰጠናል ይጠብቀናል በማለት የሚያምኑበት ስርአት ነው፡፡ የቦረንትቻ ስርአት በግንቦት ወር መጨረሻና በሰኔ ወር መግቢያ ላይ በግለሰብ ደረጃ በማዘጋጀት ለእንሰሳቶቹ እና ለልጆቹ ጤና እንዲሰጥላቸው ይለማመናሉ፡፡ ያከባቢው ማህበረሰብ በነዚህ ሶስት መናፈፍስቶች ትልቅ እምነት እንዳላቸው (ባህልና ቱርዝም ቢሮ የባህል እሴት ስራ ዘርፍ የሆኑት ወ/ሮ መርሻ ይገልጣሉ)

## 4.4. የወረዳው መልካም ባህላዊ እሴቶች

ማህበረሰቡ ጠብቆ ካቆያቸው መልካም ባህላዊ እሴቶች መካከል የተወሰኑትን ለማቅረብ ተሞክሯል እነዚህም እሴቶች ባከባቢው ማህበረሰብ የሚታወቁ እና የሚከበሩ ስርአቶች ናቸው፡፡ እነዚህም የየሽምግልና (Jaarsuma)፣ ሲንቄ (እናቶች የሚይዧት ዘንግ)፣ ባህላዊ ሰርግ፣ የባህላዊ ለቅሶ ስርአት፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ የምግብ አዘገጀጀት፣ የጉዲፈቻ እና ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት የመሳሰሉ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወኑና ያከባቢውን ማህበረሰብ አብሮ የመኖር የረጅም ጊዜ ልምድ የሚያሳዩ መልካም እሴቶች ናቸው፡፡

### 4.4.1. ሰላምን ከማረጋገጥ አንጻር ያሉ መልካም እሴቶች

- የሽምግልና ስርአት(jaarsuma)

በአከባቢው ላይ አልፎ አልፎ የተለያዩ ግጭቶች ሊከሰቱ ይችላሉ እነዚህም ግጭቶች በብዛት የሚከሰቱት በእርሻ መሬት፣ በግጦሽ ሳር ወሰን አለመስማማት፣ የእንሰሳት ሌብነት፣ አንዱ ተክሎ የተንከባከበውን ደን ሌላው ሲቆርጥበት እና ወዘተ… በመሳሰሉ ጉዳዮች ግጭቶች ይነሳሉ፡፡ የሰው ልጅ ህይወት እስከ መጥፋት ሊደርስ ይችላል፡፡ በዚህም ትላልቅ አባቶች ና ያገር ሽማግሌዎች ፈጥነው ማሃል በመግባት ነገሩን የሚያረጋጉበትና የቀድሞውን ሰላም የሚመልሱበት ስርአት ነው፡፡ እንደ ሎዴ ሔጦሳ ወረዳ የሽማግልና ስርአት የሚካሄደው በቤተክርስቲያን ፤በመስጅድ እና በትልልቅ ዛፍ ሥር ነው፡ የእርቅ ስርአት በሓይማኖታዊ ተቋማት ሲካሄዱ የሚታረቁት አካላት ውሸት አይደባልቁም እውነታውን ያወጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን በተጨማሪመሪም በዛፍ ስር ሲሆን ማህበረሰቡ በዛፍ ስር የፈጣሪ መንፈስ አለ ለእርቁ ስርአት መሳካት ጥሩ ቦታነው በማለት ያምናሉ በተጨማሪም የእርቁ ስርአት ቢቆይ እንኳን አስታራቂ ሽማግሌዎቹንም ሆነ ታራቂዎቹን ከጸሃይ ሃሩር የሚከላከል ቦታ በመሆኑ ነው፡፡

የሽምግልና(jaarsuma) ስርአት በዚህ አይነት በድብቅ የተከናወኑ የስርቆት እና የነብስ ማጥፋት ወንጀሎችን የሚያውጣጡበት ስርአት አላቸው ይንም የተጠረጠረውን ሰው በማስማል እና የገደለውን እራሱን ካላጋለጠ በመርገም ነው፡፡ ከማሃለዎቹ መካከል በድብቅ ወንጀል ሰው ገሏል ተብሎ ከተጠረጠረ ጦር በማስነከስ አላደረኩትም ሲል እንዲምል ይደረጋል ሌላው የሳር(የስንደዶ) ገመድ በመግመድ እና መረት ላይ ችካል በመቸከል ገመዱን በችካሉ ላይ እንዲ ጠመጥም በማድረግ እኔ አድርጌ ደብቄ ከሆነ በኔ እንዲሁም

በዘሬ ላይ ችግር ይጠምጠም ብሎ እንዲምል ይደረጋል እንዲሁም መርፌ፣ ወስፌ እና ቅዱሳት መጻህፍት በማስያዝ በማሃላ ነገሩን ያውጣጣሉ፡፡

ባጋጣሚ በተነሳ ጸብ ሰው የገደለ እና ገሎ ከደበቀ በእርግማኑ እና በማሃላው አውጣጭኝ የታወቀ ከሆነ ባከባቢው የሽምግልና ባህል መሰረት እንዳይገዳደሉ ሁኔታው ተጠንቶ ሽማግሌዎቹ ለሟች ወገን ጉማ (የነብስ ዋጋ) ለምኖ እንዲከፍል ለገዳይ የቀን ቀጠሮ ይሰጠዋል ለተወሰነ ጊዜ በገበያ ቦታ በሃይማኖታዊ ክብረ በአል እንዲሁም ከየዘመዶቹ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሳይገባ እየዞረ በእጁ የሰው ነብስ እዳለፈና ሽማግሌዎች ለጉማ የሚሆን ገንዘብ ወይም ከብት እንዲከፍል እንደተወሰነበት እየተናገረ ለምኖ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ በዚህም አይነት ለምኖ ከከፈለ እና ከታረቀ ብኋላ ቀድሞ በሟች ቤተሰብ አቅራቢያ የሚኖር ከሆነ ቤቱን አፍርሶ ከሚኖርበት አካባቢ እንዲርቅ እና ሰፈሩን እንዲየይር ይደረጋል፡፡ የባህላዊ ሽምግልና ስርአቱ ማህበረሰቡ ከለመደው አከባቢ ማህበራዊ ህይወት መገለል እና መገፋት እንዳይደርስበት ሲል ሰላሙን ጠብቆ ይኖራል፡፡ በዚህም ሰላምን በማስፈን ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

**ሲንቄ** (Siinqee) **ስርአት**

ሲንቄ ማለት ቀጭን ዘንግ በሰው ቁመት ተቆርጦ ቅባት በመቀባት በጭስ ላይ በመስቀል እንድትቀላ በማድረግ የምትዘጋጅ ዘንግ ስትሆን የተስተካከለ እና ምንም አይነት ጉጥ ያሌላት ናት፡፡ ሲንቄ እናቶች ለክብር የሚይዟት ስትሆን ወንዶችም ሆኑ ያላገቡ ሴቶች እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም፡፡ በሲንቄ ከብት አይሰማራም፣ የተጫነች አሕያ አይነዳም ፈረስ አይመታባትም፣ ውሻም ቢመጣ ውሻላይ አትወረወርም፣ ለወገብ ማጥኛም አይደገፏትም ህግን ለማስከበር ብቻ የምትያዝ የክብር እቃ ናት፡፡ በመንገድ ላይ ሲንቄ የያዘች እናት ብትመጣ ቅድሚያ ይሰጣታል በመልካም ቢሆን ቀድማ እንድትሻገር የሚደረገው ሲንቄ የያዘች እናት ናት፡፡ እንደ ሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ሲንቄ ለሴቶች የክብራቸው ማስጠበቂያ ምልክትናት፡፡

የሲነቄ ስርት አጀማመርን በተመለከተ gammachuu እና sisayi (2019) መጽሃፋቸው ሲያብራሩ የሲንቄ ስርአት ተጀመረ የሚባለው በአኮ መኖዬ (የሴቶች የበላይነት በነበረበት ጊዜ) ሲሆን በሴቶች እጅ የነበረውን ስልጣን ለወንዶች አሳልፈው ሲሰጡ የሲንቄ ስርአትን እና የቀናፋ ስርአትን መልሰው እንደወሰዱ ይነገራል፡፡ በሲንቄ የተለያዩ ስርአቶች የሚከናወኑ ሲሆን በዋናነት የሴቶች መብት የሚጠበቅበት ስርአት ነው፡፡

እንደ አርሲ አሮሞ አዋቂው (hayyuu) አለንጋ ይዞ ሲፈርድ አባ ቦኩው (የገዳ ስርአት የሚፈጸምበት ዱላ) በቦኩ ሲፈርድ እናቶችም በሲንቄ አማካይነት ፍርድ ያስተላልፋሉ፡፡ ሲንቄ እንደቦታው ከተለያዩ ቁሳቁሶች ጋር የሚያዝ ሲሆን ለምሳሌ ወደ መልካ ሲኬድ ከሰርዶ ሳር ጋር ይያዛል ይህም ኢሬሳ ይባላል፡፡ ሲንቄን እናቶች ሁልጊዜም በቀኝ እጅ የሚይዙት ሲሆን በግራ እጃቸውም ጮጮ፣ እርጥብ ልምጭ፣ እርጥብ ሳር በእጃቸው ይይዛሉ በአቴቴ ፊጫሳ ጊዜም ሲንቄውን በመያዝ ጨሌ ባንገታቸው ያጠልቃሉ በእጇም ከሲንቄው ጋር ኢሬሳ (እርጥብ ሰርዶ ሳር) ትይዛለች፡፡ ሲንቄ በርካታ ጠቀሜታ እንዳሉት ይጠቀሳል ለምሳሌ በሁለት በጎሳዎች መሃል የተነሳን ግጭት ወደ ጦርነትና ትልቅ ችግር ከመፈጠሩ በፊት እናቶች ሲንቄ ይዘው ይገላግላሉ፡፡ ጦርነት ቢነሳም እንኳን በጦርነቱ መሃል እናቶች ሲንቄ ይሰው እልል እያሉ እና ዲልጎ የሚባለውን ዘፈን እንደሚከተለው እየጨፈሩ መሃል በመግበት ያረጋጋሉ፡፡

| | |
|---|---|
| 'Ani waraana hin qabu; | እኔ ጦር የለኝም |
| Siinqee tiyya sootii qabadhe; | ቆንጆዋን ዘንጌን ይዤ |
| Ani humnaa hinqabuu; | እኔ ጉልበትም የለኝም |
| Waaqa kiyya motii kadhadhee; | ፈጣሪዬ ንጉሱን ለምኜ |
| Waan rakadhee hin qabuu; | የቸገረኝ ነገር የለም |
| Maaf dhaba Kan jilo qabdu,' | ለምን አጣለሁ የጂሎአለ፡፡ |

ዘፈን እየዘፈኑ በጦርነቱ መሃል በመግባት ከመስፋፋቱና ከባድ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ጦርነቱ እንዲረጋጋና እንዲቆም ያደርጋሉ፡፡ ሲንቄ የያዙ እናቶች የሃገር ወሰን ጥሶ የመጣ ጠላት ችግር ሲፈጥር ወንዶቹን በመሰብሰብ መርቀው አገራቸውን ተዋግተው እንዲታደጉም ያደራሉ፡፡

- **ቀናፋ (Qanafaa)፡-** ቀናፋ (Qanafaa) ማለት እንደ ኦሮሞ ባህል ሴቶች በግንባራቸው ላይ የሚያስሩት ጌጥና መከበሪያቸው ነው፡፡ አንድ እናት ሴት ከወለደች ለአራት ወር እና ወንድ ከወለደች ለአምስት ወር በግንባሯ ላይ በማሰር መብቷን ታስከብራለች፡፡ ቀናፋ በግንባሯ ያሰረች ሴት ክብር ያላት ስትሆን አትመታም ክፉ ነገር አይነገሯትም ይህን የተላለፈ ባል እንኳን ቢኖር እናቶች ሲንቄ በመያዝ ያጠፋውን ወንድ ይቀጡታል የበደላትንም ሚስቱን እንዲክሳት ይደረጋል ሲንቄ ለያዙትንም እናቶች አርዶ እንዲያበላ ይፈረድበታል፡፡

## 4.5. የዝምድና መፍጠሪያ መንገዶች

በአከባቢው ማህበረሰብ  የተያዩ የዝምድና መፍጠሪያ ስርአቶች ሲኖሩ እነዚህም ስርአቶች ባብዘኛው ታዋቂ የሆኑት ጉዲፈቻ፣ ጋብቻ ፣ክርስትና ጡት መጣባትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- **ጉዲፈቻ** (Guddifachaa)፡-ጉዲፈቻ ስርአት ማለት ልጅ መውለድ ያልቻሉ መሀን ሰዎች ልጅ ካላቸው ወስደው እንደ ራሳቸው የሚያሳድጉበት ሂደት ሲሆን አልፎ አልፎም ሴት ብቻ ሲወልዱ ወንድ ልጅ ሲፈልጉ ይወስዳሉ እነዲሁም ወንድ ወልደው ሴት ልጅ ሲፈልጉ በጉዲፈቻ ወስደው የሚያሳድጉበት ስርአት ነው፡፡ ጉዲፈቻ መውሰድ የሚፈልጉ ሰዎች አራት እና ከዚያ በላይ ልጆች ያላቸውን ሰዎች እንዲሰጧቸው ሲፈልጉ ባከባቢው ሚስጥር ጠባቂ የሆነ ሽማግሌ በመምረጥ ወደ ልጁ ወላጆች ቤት በመላክ ከልጆቻቸው መሃል በስም በመጥቀስ ልጃቸውን ሊያሳድጹ እንደሚፈልጉ እና እንድሰጧቸው ይፈልጋሉ በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ሽማግሌ ሁኔታውን ካጣራ ብኋላ መልሱን ይዞ ጉዲፈቻ መውሰድ ወደሚፈልጉት ሰዎች በመመለስ መልሱን ያደርሳል የልጁ ወላጆች ፍቃደኛ ከሆኑ  ለልጁ ወላጆች ጊደር፣ ቅቤ ስጦታ በመያዝ ለወላጆቹና ለልጁ አዲስ ልብስ በማልበስ አባገዳዎችን እና የጎሳ ሃላፊዎችን በመጥራት በ“ጫጩ ከለቻ” በመያዝ ወደ ጉዲፈቻው ልጅ ቤተሰብ በመሄድ ከአባገዳዎችና ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ጉዳዩን ካነጋገሩና ከጨረሱ ብሁዋላ ጉዲፈቻ የሚወስዱት ሰዎች የሚወስዱትን ልጅ እንደራሳቸው ልጅ ተንከባክበው ሊያሳድጉ በ“ጫጩ ከለቻ” ቃል ይገባሉ፡፡ ወላጆቹም “በጫጩ ከለቻ” ቃል በመግባትና የቀሩት ልጆች ይበቁናል በማለት ልጁ የኛነው በማለት ሁለተኛ ላይፈልጉት ልጁን አንስተው ፊታቸውን አዙረው ሳያዩ ጉዲፈቻ ለሚወስዱት ይሰጣሉ፡፡

ጉዲፈቻ የሚወሰዱት ያመጡትን ልብስ በማልበስ ጊደሯን መርቀው በመስጠት ሁለቱንም የልጁን ወላጆችና ጉዲፈቻ የሚወስዱትን ልጅ ቅቤ በመቀባትና ማር በማጉረስ ፍቅራቹን ያጽናላቹ ያላቹን ልጆች ይባርክላቹ በማለት ጉዲፈቻ የሚወስዱትንም ልጃቹ የተባረከ ለናንተም ያይናቹ ማረፊያ ጠዋሪ ቀባሪ ያድርግላቹ በማለት መርቀው ሲያበቁ ልጁን ይዘው ወደቤታቸው ይሄዳሉ ከዚያም የሚፈልጉትን ስም በማውጣት በራሳቸው ስም እንዲጠራ ያደርጋሉ ለልጁም አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ ያሳድጋሉ ሲያረጁም ያላቸውን ንብረት በሽማግሌ ፊት ያወርሱታል ልጅም ያሳደጉትን እድሜያቸው ሲደክም

ይጠራል ይንከባከባል፡፡ ጉዲፈቻ የወሰዱት ሌላ ልጆች ካላቸው ንብረት እንደሁሉም ልጆች አብሮ እኩል ተካፍሎ እንዲወርስ ይደረጋል ከልጆቹም ወንድምና እህት ሆኖ ይኖራል፡፡

## ባህላዊ የጋብቻ ስርአት

እንደ ሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት የባህል እሴት ልማት ባለሙያ በወረዳዉ ባህላዊ የሰርግ ስርአት ነባርና በሁሉም አካባቢ ማህበረሰብ ተመሳሳይ የሆነ ሂደት ያላቸው እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳውስት የተለያዩ የጋብቻ ስርአት ይገኛል እነዚህ ም, **ወሊን ኬና** (walii kennaa)፣ **ከዳ** (kadhaa) **ወል ገራ** (wal gara)፣**ዳላ** (dhaala),**ሜምቤቶ** (me nbeetoo) **ኢራ ዳባ** (irra-dhaaba) **ኢራ ጪብሳ**( Irra-ciibsa,) **አሴና** (Aseen naa) **ወሊን ገሉ** (waliin galuu) በመባል ይታወቃሉ፡፡

1. **ወሊን ኬና (walii-kennaa)፡-** ይህ የጋብቻ አይነት የሚካሄደው የልጁና የልጂቷ ቤተሰብ በመስማማት ልጅህን ለልጄ ስጠኝ ዝምድናህን ፈልጋለው በማለትና በመስማማት ልጆቻቸውን በማጋባት ዝምድና የሚፈጥሩበት መንገድ ነው፡፡ ይህም ስርአት የሚካሄደው ከሁለቱ ተጋቢዎች እውቅና ውጪ የሚካሄድ እና ልጆቹም ለአቅመ አዳም እንደደረሱ ቤተሰብ ያላቸውን እና ቃል የተግባቡበትን የሚያገቡበት ስርአት ነው፡፡

2. **ኢረ ጪብሳ (Irra-ciibsa)፡-** ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ በድንገት ለትደር በሚፈልጋት ልጅ ቤተሰብ ግቢ ሽማግሌዎችና ጓደኞቹን በመያዝ በልጂቱ ቤተሰብ ግቢ በመግባትና በመቀመጥ ለትዳር የምንፈልጋትን ልጅ ስጡን ዝምድናቹን እንፈልጋለን በማለት በግቢው ይቆያሉ በዚህም ፍቃደኛ ሆነው እስኪሰጡዋቸው ድረስ በግቢ ውስጥ በመዋልና በማደር ሲጠብቁ ሽማግሌዎች ነገሩን በመጨረስ የልጂቱ ቤተሰብ ልጂቱን እድታገባ ፈቅደው በመስጠት ልጂቱን ይዘው ወደልጁ ቤተሰብ ይሄዳሉ፡፡

3. **ከዳ (kadhaa)፡-** የከዳ ጋብቻ አይነት የሚጋቡትን እና የተጋቢዎችን ቤተሰብ እንዲሁም የስጋ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች የማይሳተፉበት ስርአት ነው፡፡ ላቅመ አዳም የደረሰው ወጣት የሚፈልጋትን ልጅ አገረድ በማየት ለቤተሰብ እንዲ ለምኑልት ወይም ቤተሰቦቹ ከመረጠለት ልጂቷን በገበያም ሆነ በተለያየ ቦታ ከጓደኛው ጋር በመሄድ እንዲያያት ተደርጎ ፍቀደኛ ከሆነ የልጁ ቤተሰብ ለጋብቻ የሚጠይቅ ወረቀትና ኢሬሳ(እርጥብ ሳር) ለጋብቻ ወደ ተፈለገችው ልጃ ገረድ ቤተሰብ በመላክ ለጋብቻ ይጠይቃሉ በዚህም ግዜ የልጂቱ ቤተሰብ ከወዳጅ ዘመድ ጋር በመመክር እንዲሁም የልጁን ማንነት በማጥናት ለጋብቻው ፍቃደኛ ከሆኑ በሽማግሌ ጉዳዩን በመጨረስ እና የጋብቻውን ስርአት በመቁረጥ ሁለቱ እንዲጋቡ የሚደረግበት የጋብቻ አይት ነው፡፡

4. **ወል ገራ** (Wal-garaa):-ይህ የጋብቻ አይነት ላቅመ አዳም የደረሰ ወጣት ካንድ እናትና አባት የምትወለደውን እህቱን ለሚያገባት ልጅ ወንድም በመስጠት በልዋጭ የሚያገባበት ስርአት ነው፡፡

5. **ዳላ** (dhaala)፡- ስርአቱን ጠብቃ በቤተሰብ የተዳረች ልጅ አገረድ ለባሏ ታማኝ ሆና ልጆች ወልዳ እያለች ባሏ ባጋጣሚ ቢያርፍባት (ቢሞት) ለልጆቹ ባዳ የሆነ አግብታ ልጆቹ እንዳይበደሉና የአባታቸውን ንብረት ባዳ እንዳይበላው የልጆቹን ቅርስ እንዲጠብቅና ልጆቹን ተንከባክቦ እንዲያሳድግ የሟች ባሏን ወንድም በማግባት ልጆቹን በጋራ እንዲንከባከቡና እንዲያሳድጉ በዳላ እንድታገባ ይደረጋል በዚህም ልጆቹ ባነታቸው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ያድጋሉ እንዲሁም የሚወለዱት የወንድም አማች ልጆች በመሆናቸው ሁሉንም በእኩል አይን እያዩ በማሳደግ ለቁም ነገር እንዲበቁ ያደርጋሉ፡፡

6. **አሴና**(Aseennaa):- አሴና የጋብቻ ስርአት የሚካሄደው ሴቶች የጋብቻ ወቅቷ ሲያልፍባት (ቆሞ ቀር) ስትሆንና የሚያገባት ስታጣ ባከባቢው የምትፈልገውን ወንድ በማየት እርጥብ ዘንግ ቆርጣ ከማለቢያ ጋር በመያዝ ወደልጁ ቤተሰብ በመሄድ የልጁ እናት ቤት በመግባት የቤቱ እኩሌታ ምሰሶ ስር ቁጭ በማለት ገብቼ አልወጣም ተቀምጬ አልነሳም ትላለች በዚህም ጊዜ የልጁ ቤተሰብ ባከባቢው ትላልቅ ሽማግሌዎችን በመጥራት ሽማግሌዎቹ ልጅቷን ለምን እንደ መጣች በመጠየቅ ከዚያ በፊት ለትዳር በሌላ ሰው መለመን አለመለመኗን አግብታ መፍታት አለመፍታቷን በማጣራት በሚስጥር ከነድንግልናዋ መሆኗን ሽማግሌዎቹ ከመረመሯት ብኋላ የፈለገችውን ልጅ በመጠየቅ አስገድደው እንዲያገባት ያደርጋሉ ነገር ግን የተለመነች ከሆነች፣አግብታ የፈታች ከሆነችና ድንድል ካልሆነች የልጁ ቤተሰብ ለልጂቷ ሙሉ ልብስ በማልበስ ወደቤተሰቦቿ ይመልሷታል፡፡

7. **ወሊን ገሉ** (Waliin- galuu):- ሁለት ለአቅመ አዳም የረሱ ወንድና ሴት በራሳቸው ፍላጎት (ስምምነት) ሁሉንም በመጨረስ ሴቷ ወደ ልጁ ቤት በመግባት የሚጋቡበት ስርአት ሲሆን በዚህም አይነት አብረው መኖር ከጀመረሩ ብኋላ ወደልጂቷ ቤተሰብ በመላክ ጋብቻቸውን በማስተዋወቅ ስራ የሚሰሩበት የጋብቻ ስርአት ነው፡፡

8. **ሜምቤቶ** (Menbeeto)፡- አንድ ሴት በገበራ አግብታ ስትኖር ባጋጣሚ ልጅ ወልዳም ይሁን ሳትወልድ ብትሞት የሟች ባለቤቱን እህት ወይም እህት ካሌላት የእኅት ልጅ ወይም የቅርብ ዘመድ የሆነችውን በማግባት እንድትኖር ይደረጋል በዚህም የሟቿን ልጆች ዘመድ ያልሆነች ሴት የሟቿን ልጆች እንዳት ጎዳ ሲሆን በዘመድ ሲያድጉ እንክብካቤ ያገኛሉ

ተብሎ ይታሰባል፡፡ የዚህ አይነት ሚስቱ ስትሞት የሚስቱን እህት ወይም የቅርብ ዘመድ ሲያገባ ሜምቤቶ በመባል ይታወቃል

## ባህላዊ የለቅሶ ስርአት

እንደ ሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ባህል ታዋቂ ሰው ሲሞት የራሱ የሆነ ያለቃቀስ ስርአት አለው፡፡ ይህም ስርአት ግለሰቡ በህመም ውስጥ ካለና እንደማይተርፍ ከተረዱ እንደሚከተለው ሀይማኖት የቅርብ ጓደኛና የንስሃ አባት በመቅረብ ያለውን ቃለ ኑዛዜ በመቀበል በሚስጥር ይይዛሉ ከዚህን ጊዜ ብኋላ ታማሚው እየባሰበት ከሄደ ወዳጅ ዘመድ እንደማይተርፍ ከተረዱ ለቀብር ስርአት የሚሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ ይህም ለእርድ የሚሆን ከብት መግዛት ለእንጀራ የሚሆን እህል ማስፈጨት በርበሬና ሽሮ ያከባቢው እድር ከሚሰጠው በተጨማሪ ማዘጋጀት የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ያካሂዳሉ፡፡ ቀኑም ደርሶ ታማሚው ነፍሱ ከስጋው ከተለየ የሟች ቤተሰብ በራሱ ለወዳጅ ዘመድ መርዶ ነጋሪ መላክ ወይም ስልክ በመደወል ያረዳሉ ከዚህን ብኋላ ለቀብር ስርአቱ ወንድም፣ እህት፣ ልጅ፣ እናተና አባት ሊሆን ይችላል መርዶውን እንደሰሙ ሽንጎ በመታገዝ እንጀራና አረቄ በመያዝ በጎሮቤትና በጓደኛ ታጅበው የማስለቀሻ ፈረስ ቀሚስ በማልበስ ወደለቅሶው ቤት በመምጣት የሟቹን አልባሳት፣ ፎቶና የግል እቃዎች በመያዝ ህርማቸውን የሚያወጡ ሲሆን ለአስከሬኑም ፍታት ተካሂዶ እንዳለቀ ወደ ቀብር ቦታው ሲሄድ በተለያየ ሙሾና ፉከራ በማጀብ ቀብሩ ቦታ ሲደርሱ ሁሉም ቆመው በማልቀስና ህርማቸውን በማውጣት ግብአተ መሬቱ ካበቃ ብኋላ የሟች ጓደኛ በቀባሪው ማህበረሰብ ፊት በመቆም የሟቹን የህይወት ታሪክ በማንበብ ያሳለፈውን የትምህርት የጀግንነት እና የሰራቸውን ጀብድ በማንበብ ህዝቡን ያስተምራል ከዚህን ብኋላ አባቶች ካህናት ሃይማኖታዊ ምክር በመስጠት ለቤተሰቡና ለወዳጅ ዘመድ መጽናናትን ተመኝተው እግዚአብሄር ያጽናችሁ በማለት አሳርገው በሰላም ግቡ ሲሉ ሁሉም ለቀባሪ የመጣውን ንፍሮ (እንባ አድርቅ) በመብላት ወደ ለቅሶው ቤት ይመለሳሉ፡፡ በሟቹ ቤተሰብ የተዘጋጀውን የእንግዳ መሸኛ በመመገብ ቀባሪው ይበተናል በድጋሜም በሶስተኛው ቀን (ሰልስት) ጠዋት አስራ ሁለት ሰአት በመውጣት አልቅሰው ከሟች ቤተሰብ ጋር በመሆን የተለያዩ ጫወታዎችን በማንሳት በሀዘኑ ቤት በመሰባሰብና በመጫወት የሟች ቤተሰብ ከሃዘን እንዲ ወጣ (እንዲጽናና) ያደርጋሉ፡፡

## ባህላዊ አልባሳት እና መዋቢያ

አልባሳት ሰዎች ጸሀይንና ብርድን ከአካላቸው ለመከላከልና እርቃናቸውን ለመሸፈን የሚለብሱት ሲሆን ይህም አልባሳት እንደየ አካባቢው አየር ጸባይ፣ ባህል እና እምነት

የተለያዩ ናቸው፡፡ ባህላዊ አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ባህል ሲገልጹ በተጨማሪም ጾታን፣ የስራ ሁኔታን፣ ማህበራዊ ደረጃና እድሜን የሚገልጹ ናቸው፡፡ እንደ ሎዴ ሄጣሳ ወረዳ ታዋቂ የሆኑት ባህላዊ አልባሳትን በተመለከተ የወረዳው ባ/ቱ/ጽ/ቤት የባህል ዘርፍ ባለሙያ የሆኑት ሲገልጹ ሴቶች በክብረ በአል እና በሰርግ ጊዜ የሚለብሱት አልባሳት የአከባቢውን ማህበረሰብ ባህል የሚገልጹ አልባሳት ቡራ ቡሬ ሽንሽን ቀሚስ በቀይ ወይም በሰማያዊ ሻማ ውስጥልብስ፣ ከሱሬ ጋር ይለበሳል፣ ቀይ ወይም ጥቁር ጥለት ያለውን ነጠላ መቀነት ይጠቀማሉ በቀሚሱላም ሹራብ ኮት የሚደርቡ ሲሆን ተረገዝ ያለውን ጫማ ከነጭ ካልሲ ጋር ይጫሙታል ከላይም ቀይ ወይም ጥቁር ጥለት ያለው ነጠላ (naxalaa kula) የሚደረብ ሲሆን ጸጉራቸውን በጥቁር ሻሽ በማሰር የሚለበስ ነው፡፡ ይህ አለባበስ ከተለያዩ ጌጣጌጦች ጋር የሚለበስ ሲሆን እነዚህም ጌጣጌጦች ባንገት የሚጠለቅ ጨሌ፣ እጅ አንባር፣ በእጅ ጣት የሚጠለቅ የብር ቀለበትና ቀናፋ (በግንባር ላይ የሚደረግ ቀይ ጠፍጣፋ ጨሌ) በማድረግ ያጌጣሉ፡፡ እናቶች በክብረ በአላትና በሰርግ ጊዜ የሚያዞትሩት ሲሆን ወንዶች በድሮ ጊዜ ተነፋነፍ ሱሬ እና ኮት ከባርሜጣ ጋር የሚጠለቅ አለባበስ ሲሆን በተጨማሪም ከላይ ጋቢ በመደረብ በእጃቸው ዘንግ ወይም ከዘራ በመያዝ የሚያጌጡበት አለባበስ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ የመረጃ ትንተናና ትርጓሜ

በዚህ ምዕራፍ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአት አጀማመር፣ የስርአቱ አከዋወን፣ በቅድመ፣ በጊዜና በድህረ ኢሬቻው ምን ይመስላል? የስርአቱ መከበር ላከባቢው ማህበረሰብ ያለውን ጠቀሜታ ግልጽ በሆነ መንገድ መረጃው ትርጉም በሚሰጥ መንገድ የክዋኔውን ቅደም ተከተል ጠብቀው ተደራጅተው ከጽንሰ ሃሳብና ከመተንተኛ ትውሮች ጋር በመጣመር ተተንትኖ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## 5.1. በዶኒ አድባር የኢሬቻ ስርአተ ከበራ አጀማመርና የአድባሩ ስያሜ፡፡

ይህ ቦታ ዶኒ የሚለውን ስያሜ ከማግኘቱና የምስጋናው ኢሬቻ መከበር ከመጀመሩ በፊት ጥንት ባከባቢው ይኖሩና በዶኒ አድባር ስር ስርአተ አምልኮ ይፈጽሙ የነበሩት ሃዲያዎች ናቸው፡፡ ሃዲያዎች በአከባቢው ሲኖሩ በዶኒ ተራራ ጎን ትላልቅ ድንጋይ ባለበት አከባቢ የከብት በረት በድንጋይ ክበው እንደሰሩና በቦታውም ከአንድ ሺህ (1000) አመት በፊት ጀምሮ ሰፍረው ሲኖሩና ስርአተ አምልኮውንም ሲፈፅሙ የነበሩት ሀዲያዎች ናቸው፡፡ በዚህ ቦታ ስርአተ አምልኮው በእርግጠኝነት መቼ እንደተጀመረ አይታወቅም፡፡ በቦታውም ሀዲያዎች የተለያዩ ስርአተ ከበራዎችን ሲፈጽሙ እንደነበር መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ በዶኒ አድባር ስር የተለያዩ ሃይማኖታዊ ስርአቶችን ሲፈጽሙ እንደኖሩ የሚጠቁሙ ቁሶች የነበሩ እንደ ማለቢያ፣ ቅል፣ የሸክላ ማሰሮ የመሳሰሉ የመስዋዕት ማቅረቢያ ቁሶች በቦታው ተገኝተዋል ሲሉ አቶ ደዲሹ ቱርኬ በቀን (10/09/2014በተደረገ ቃለመጠይቅ) ሲገልጹ በተጨማሪም አቶ ተሸመ አለሙና አቶ ዲንቁ ሰቦታ (በቀን 20/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ)

> በጋራ በመሆን በቦታው አርሲ ኦሮሞ እንዴት እንደተተካ ሲገልጹ ጥንት አርሲ አሮሞዎች ወደ አከባቢው ባደረጉት መስፋፋት ሃዲያዎች ካከባቢው ለቀው ወተዋል በቦታውም አርሲ ኦሮሞዎች ሰፍረው መኖር ጀምረዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ አርሲ አሮሞ ባከባቢው መኖር ከጀመረ ብሁዋላ ባከባቢው አስከፊ ድርቅ ተከስቶ በርካታ እንሰሳት በማለቃቸውና አስከፊ ረሃብ በመከሰቱ በህዝቡ ዘንድ ሃዘንና ግራ መጋባት ተፈጥሯል፡፡ በወቅቱ የነበሩ ትላልቅ አባቶች መስዋዕት እናቅርብና ፈጣሪን (ዋቃን) እንለምን በማለት በአከባቢው ታዋቂ የሆኑ አባቶች **አቶ መንጃ ቦቄ** ነጭ ግመል **አቶ ዲዶ ገዳ** ደግሞ ነጭ ኮርማ በማምጣት ለፈጣሪ መስዋዕት ለማቅረብ ይህን

ከዶኒ ተራራ በስተ ደቡብ ያለውን ቦታ የመሬት እኩሌታ ነው በማለት ቀደም ብለው ሃዲያዎች ስርአተ አምልኮ ሲፈጽሙበት የነበረው ቦታ ላይ ግመልና ኮርማውን በማረድ ለፈጣሪ መስዕዋት አቅርበው በመለመን በእለቱ ዝናብ ዘንቦላቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ዶኒ የሚለውን ስያሜ የሰጡት አርሲ አሮሞዎች ባከባቢው ከሰፈሩ ብኋላ ነው፡፡ ባከባቢው በመጣው ድርቅ የተነሳ ትላልቅ አባቶች በአንድነት አድባሩ ስር በመውጣት ክብ ተቀምጠው ፈጣሪን (dooyrii taa`ani waqaa kadhatuu) በመለመን ፈጣሪ ሰምቷቸው እንደዘነበላቸው ሲገልጹ ከዚህም በመነሳት ዶሪ የሚለውን ስያሜ እንደሰየሙት ይገልጻሉ፡፡ “ዶሪ” የሚለውን ቃል ሲተረጎም የመሬት እኩሌታ፤ ክብ ቦታ፣ ክብ ተቀምጦ ፈጣሪን መለመን በማለት ይገልጹታል ዶሪ ከሚለውስያሜም በተጨማሪ “ዶኒ” በማለት ይጠሩታል ትርጉሙም ከማእበል የሚያሻግር ጀልባ በማለት እንደሰየሙት ይገልጻሉ፡፡

አባቶች ባከባቢው ላይ ከመጣባቸው ድርቅ ለመዳን ሲሉ ባንድነት በመለመን ለአድባሩ መስዋእት ካቀረቧቸው የግመሉን ደምና ፈርስ በድንጋዩ ላይ የቀባቡት ሲሆን በዚያ በተቀባበት ቦታ የፅድ ዛፍ በቅሎበታል በፅዱም መሃል አንድ የወይራ ዛፍ በቅሎ ይገኛል ፡፡ በማለት (አቶ ከፊያለው ፋንታ በቀን 05/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ይህንንም የጽድ አድባር በቦታው በመገኘት የዛፉ የአበቃቀል ሁኔታ በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በዶኒ አድባር ስር ስርአተ አምልኮ መከበር የተጀመረው በሃዲያዎች ሲሆን መቼ ማክበር እንደጀመሩና እነሱ በምን ምክንያት እንደጀመሩት በውል ባይታወቅም ከአከባቢው ከለቀቁና አርሲ ኦሮሞዎች ባከባቢው ከሰፈሩ ወዲህ በአከባቢው በተከሰተ ድርቅ የተነሳ በአቶ መንጃ ቦቄና በአቶ ዲዶ ገዳ አማካኝነት የኢሬቻው ስርአተ ከበራ እንደተጀመረ በርካታ መረጃ አቀባዮች ሲገልጹ የኢሬቻው ስርአትም መስከረም አስራ ሰባት እንዲከበር ስርአቱን ያስጀመሩት አባቶች በመወሰናቸው በአከባቢው ያለው ማህበረሰብ በመስማማት ቀኑን ጠብቆ በየዓመቱ በአድባሩ ስር በመሰባሰብ ስርአተ ከበራውን በድምቀት ያከብራሉ፡፡ ሲሉ አቶ አብዶ ሮባ (በቀን 18/12/2014 የተገኘ ቃለመጠይቅ)፡፡

**ሁለተኛው ቃል ተረክ ዶኒ የሚለውን ስያሜ አስመልክቶ የሚነገረው፡-** ባንድ ወቅት አስከፊ ወረርሽኝ በሽታ በአከባቢው ተከስቶ ብዙ ሰው በወረርሽኙ ህይወቱን በማጣቱ አባቶች እስኪ ፈጣሪያችንን እንለምን በማለት ተሰባስበው ወደዚህ በድንጋይ ወደ ተከበበች ቦታ

በመምጣት እዛች ድንጋያማ ቦታ ላይ ፈጣሪን (ዋቃን) በመለመን ከመጣብን ወረርሽኝ (በሽታ) ድነናል፡፡ ከወረርሽኝ በሽታ የዳኑበትን ወቅት ለማሰብ በያመቱ መስከረም አስራ ሰባት በአመት አንድ ጊዜ በዶኒ አድባር ስር በመውጣት ምስጋና ሲያቀርቡ የኖሩ ሲሆን በያመቱ ምስጋናችንን ካላቀረብን ወረርሽኝ በሽታ በድባሜ እንዳይነሳባቸው ያከብራሉ፡፡ ያከባቢው ማህበረሰብ እዚህ ቦታ ላይ በያመቱ ሲወጡ ፈጣሪ በቦታው ላይ አድሮ ካደረገላቸው ቸርነት በመነሳት ቦታውን ዶኒ(doonii) በመለት ይጠሩታል ትርጉምም ፈጣሪ በቸርነቱ አቅፎ ከመጣብን ወረርሽኝ በሰላም ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረን ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ማህበረሰቡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ አደጋ ሲከሰትና ባከባቢው በሚኖሩ ጎሳዎች መካከል ግጭት ሲቀሰቀስ፣ ጦርነት ሲነሳ፣ ልጅ ያልወለደና ማሃን የሆነ፣ ከብቶች አልራባ ሲሉ እንዲሁም የሚያስጨንቅ ችግር ሲከሰትብን ለዶኒ አድባር በግልና በጋራ በመሆን ስዕለት በመሳል በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ቀን ስዕለታችንን ይዘን በኢሬቻው ቀን ለአድባሩ እናቀርባለን ሲሉ (አቶ ጣፋ ቱፋ 12/09/2014ና አቶ ዲንቁ ሰቦቃ 16/09/2014 ቀን የተደረገ ቃለመጠይቅ ይገልጣሉ)፡፡

አቶ ተሸመ በቀለ (በቀን 19/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ) በአሁኑ ወቅት የአድባሩ ሃላፊ፤ መራቂና የመስዋት ከብት ባራኪ (አራጅ) ሽማግሌ የሆኑ በዶኒ አድባር ላይ ስላላቸው ሃላፊነት እንዴት እንደተቀበሉ ሲገልጹ ጥንት ቅድመ ሃያታችን አቶ ባልቻ ያደቴ መሃን ሆኖ ልጅ በማጣቱ ስዕለት ተስሎ ልጆች ወልዷል ስዕለቱንም ለረጅም ዘመን በተደጋጋሚ ነጭ ኮርማ በማምጣት ሲያርዱና ለአድባሩ መስዋዕት ሲያቀርቡ የቆዩ በመሆናቸው በአከባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ክብር በማግኘታቸው ለአድባሩ የመስዋዕት ከብት እንዲባርኩ መርጧቸዋል፡፡ የተሰጣቸው ሃላፊነት ከልጅ ልጅ በመተላለፍ እኔም ካባቴ ተረክቤ አሁን የመስዋዕት ከብት የምባርከው እኔ ነኝ በማለት ይገልጻሉ፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ እኔ ባልኖር እንኳን የአቶ ባልቻ ያደቴ የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ብቻ በመተካት እንዲመርቅና የቀረበውን የመስዋዕት ከብት እንዲ ባርክ ይደረጋል ሲሉ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

የዶኒ አድባር ስር በሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ሃይማኖት፣ ብሄር፣ ጎሳና ጾታ ሳይለይ ሁሉም በአንድነት የሚሳተፍበት ስርአተ ከበራ ነው፡፡ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ የተጀመረው የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሀይማኖት በአከባቢው ከመስፋፋቱ በፊት ሲሆን በተለያዩ ወቅቶች በሰፈራ ወቅት የሰፈረው

ማህበረሰብ በሂደት ወደ ስርአቱ በመደባለቅ ከወቅት ወደወቅት ላሸጋገራቸው ፈጣሪ በአመት አንድ ጊዚ የምስጋና ኢሬቻ ያቀርባሉ፡፡

## 5.2. የኢሬቻ በዓል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ

በወረዳው ከሚከበሩ የምስጋና ኢሬቻ ስርአቶች መካከል ይህ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ወቅቱን ጠብቆ በዓመት አንድ ጊዜ መስከረም አስራ ሰባት የሚከበር የምስጋና ስርአተ ከበራ ነው፡፡ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የራሱ የሆነ የአከዋወን ሂደት ያለው ሲሆን ሂደቱም ስርአቱን ጠብቆ በቅድመ፣ በጊዜና በድህረ ክዋኔ ተከፋፍሎ የሚቀርብ ስርአተ ከበራ ነው፡፡

### 5.2.1. ለኢሬቻው ስርአተ ከበራ የሚከናወኑ ቅድመ ዝግጅቶች

የአከባቢው ማህበረሰብ ከኢሬቻው ስርአተ ከበራ ቀን ቀደም ብለው የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶች የሚያከናውኑ ሲሆን እነዚህም ቅድመ ዝግጅቶች በአከባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንደማህበራዊ ደረጃቸው የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ዝግጅቶች በልጃገረዶች፣ በወጣት ወንዶች፣ በእናቶችና በአባወራዎች ዘንድ የሚከናወኑ ስርአቶች ናቸው፡፡ ቅድመ ዝግጅቱም ከዘመን መለወጫ (ከእንቁጣጣሽ) ክብረበአል ጀምሮ ለአስራ ስድስት ቀን የሚከናወን ቅድመ ዝግጅት ነው፡፡በዋዜማው የሚከናወኑ ቅድመ ዝግጅቶች እንደየግለሰቡ ዝግጅት ቢለያይም በጾታና እድሜ የተለያዩ ቅድመ እግጅቶች ይከናወናሉ ቅድመዝግጅቶቹም በጾታና በእድሜ ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

- **የልጃገረዶች ቅድመ ዝግጅት፡-** ዕድሜያቸው ከ6-18 ያሉ ልጆችና ልጅ አገረዶች

ለዘመን መለወጫ (ለእንቁጣጣሽ) አበባ አየሽ ወይ ጨፍረው ያገኙትን ገንዘብ በማስቀመጥ በኢሬቻው ቀን ከረሜላ ገዝተው ይገዛሉ፡፡ በዋዜማውም የባህል ልብስ ያላት የባህል ልብሷን ወይም የክት ልብስ በማጠብ ያዘጋጃሉ መስከረም አስራ ስድስት ጸጉራቸውን በመሰራት በስርአተ ከበራው ላይ አምረውና አጊጠው ለመቅረብ ይዘጋጃሉ፡፡ ይህንንም በማስመልከት ወ/ሪት አበባ ንጉሴ (በቀን 12/10/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ) ላይ እንደገለጹልኝ፡፡

> አበባአየሽ ወይ በመጨፈር ያገኘነውን ገንዘብ በአንድ ሰው እጅ በማስቀመጥ የኢሬቻው በአል ሲደርስ ከረሜላ በመግዛት እንዘጋጃለን አዳዲስ ልብሶቻችንን

በማውጣትና የቆሸሸውን በማጠብ እናዘጋጃለን በዋዜማውም ጸጉራችንን በመሰራት፤ ቤት በማጽዳትና የባአል ምግብ በማዘጋጀት ቤተሰብን በመርዳት ዋዜማውን እናሳልፋለን በማለት ያብራራሉ፡፡

የዚህ ሃሳብ ይዘት የሚያመለክተው ልጅ አገረዶች በኢርቻው ዋዜማ የራሳቸውን አልባሳት ሲያዘጋጁ ጸጉራቸውን ሲሰሩና በተለያዩ ለኢሬቻው ስርአት በሚዘጋጅ የምግብ ዝግጅት ላይ በመሳተፍ በቤት ውስጥ እናት የምትሰራውን ስራ እንደሚረዱ የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም በቤት ውስጥ እናቶች ለኢሬቻ በአል በሚያዘጋጇቸው የምግብ ዝግጅት ላይ በመሳተፍ እናቶቻቸውን የሚያግዙ ሲሆን ከሚሳተፉባቸው ስራዎች መካከል በዋናነት ቤት ማጽዳት፣ የቂንጬ እህል መከካትና ማዘጋጀት፣ ወተት በመናጥ ለሙዳና ፈጫሳ የሚሆን ቅቤ ማዘጋጀትና ወዘተ ስራዎች ላይ በመሳተፍ ዋዜማውን ያሳልፋሉ፡፡

- **የወጣት ወንዶች ቅድመ ዝግጅት፡-** ወጣት ወንዶች በዋዜማው የተለያዩ ስርአቶችን

የሚያከናውኑ ሲሆን ከእነዚህ ክንውኖች መካከል የፈረስ ጉግስ የሚጫወቱ ወጣቶች ለጉግስ ጫወታ የሚሆን የፈረስ እቃዎችን ማስተካከል፤የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮች የፈረሱን እቃዎች ማስጌጥ፤ ጋሻና ዳቢያቸውን መወልወል፤ በጦር ምትክ ቀጫጭን እርጥብ ዘንግ መቁረጥ፤ ለጉግስ ጫወታ የሚሆነውን ድንጉላ ፈረስ በዋዜማው ማጠብ፤ ማሰር፣ ጥሬ እህል እንዳይበላና ሳርም በብዛት እንዳይበላ ትንሽ ትንሽ እንዲበላና በሆዱ ያለውን ፋንድያ እንዲያወጣ ማድረግ በጉግስ ጫወታው እለትም ውሃ አለማጠጣት ለጉገስ ጫወታ ማዘጋጀት ናቸው፡፡ ይህንንም በማስመልከት አቶ አበራ ደምሴ (በቀን 12/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ) ሲገልጹ

> በጉግስ ጫወታ ላይ የሚሳተፈውን ሰንጋ ፈረስ ለወር ተጠብቆ በቆየ ሳር (marga kallo) ውስጥ በማሰር በደንብ መቀለብና መንከባከብ አልፎ አልፎ በመጋለብ ማለማመድና ሳይለቀቅ በእንክብካቤ ተይዞ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ለሚካሄደው የጉግስ ጫወታ ሊደርስ አራት ቀን ሲቀረው ሆዱን ሊከብዱት የሚችሉ መኖዎችን በመቀነስ ትንሽ ትንሽ መስጠትና ፈረሱን ማጠብ በዋዜማው ጥሬ እህል አለመስጠትና በቤት አስሮ በማዋል በደህና ሜዳ ላይ እንዲጋልብና ላቡ እዲወጣለት በማድረግ ሰውነቱ እንዲቀለው ማድረግ ሲሆን በኢሬቻው እለትም ለሚካሄደው የጉግስ ጫወታ የፈረስ እቃዎችንና ጋሻዎችን በማዘጋጀት በእለቱ ሰንጋውን ፈረስ ባጌጠ እቃ ጭነን በጉግስ ጫወታ ላይ እንሳተፋለን ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው አንድ ሰው በጉግስ ጨዋታው ላይ ለመሳተፍ ቀድሞ የፈረስ እቃዎቹን እንደሚያስጌጥ ሰንጋ ፈረሱንም ለጉግስ ጨዋታው ለማዘጋጀት ከስርአተ ከበራው ለወር ያክል አስሮ የሚንከባከበው አልፎ አልፎ በመጋለብ የፈረሱ ሰውነት እንዲፍታታ የሚያደርጉት በስርአተ ከበራው ቀን ቀድመው ፈረሱን እንደሚያጥቡና በዋዜማውም የሚከብድ መኖ እንደማይሰጥና ሰውነቱ ቀሎት እንደልቡ ትንፋሹን ውጦ እንዲሮጥና በውድድሩ ላይ የተሻለ ፍጥነት እንዲኖረው ያደርገዋል የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡

ወጣት ወንዶች በኢሬቻው ዋዜማ ለከንፈር ወዳጃቸው የፍቅር መግለጫ የሚሰጡትን ሎሚ ገዝተው የሚያዘጋጁ ሲሆን በተጨማሪም መስከረም 16 ለሚከበረው የደመራ በአል የሚሆን እንጨት መቁረጥ፣ችቦ መስራትና ሌሊት የቀንድ ከብቶቻቸውን ተከብሮ ወደ ቆየ ግጦሽ ለሊቱን ሲያሰማሩ የሚያበሩት ዳሞቲ ኮርማ (daammoti kormaa) ችቦ በማዘጋጀት ሌሊት ችቦውን እያበሩ ከብቶቻቸውን ወደ ግጦሽ ያወጣሉ፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች የክት ልብሳቸውን በማዘጋጀት በእለቱ በክት ልብሳቸው አምረው ይቀርባሉ፡፡

- **ፎሌዎች፡-** በማህበረሰቡ ውስጥ እንደወታደር የሚታዩና ማንኛውንም የተደበቀ ነገር

የሚያጋልጡ ናቸው፡፡ ፎሌዎች እንደ ወታደርና እንደ መረጃ አስተላላፊ (free press) ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን በራሳቸው ህግ የሚመሩና ባከባቢው ጥፋት ያጠፉን ሰው በዘፈናቸው ውስጥ ከጥፍቱ እንዲመለስ ማስጠንቀቅ አልመለስ ካለ ባደባባይ መስደብና መርገም ይችላሉ፡፡ የፎሌዎች ተግባር ሁሉም ላከባቢው ህግና ስርአት ተገዝቶ እንዲኖር ያደርጉታል፡፡ በተለያዩ ስርአተ ከበራ ላይ በመሰባሰብ በዘፈን ይጫወታሉ በማለት ደጀን ደምሴ (በቀን 20/10/2014 የተደረገ ቃለመጠይቅ)፡፡ በዚህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የፎሌ ቡድን አባል የሆኑ ወጣቶች በቅድመ ኢሬቻው የተለያዩ ዝግጅቶችን ያከናውናሉ እነዚህም ዝግጅቶች በዋዜማው ቀደም ብለው ዳቤ(የጭላዳ ዝንጀሮ ጸጉር የተሰራ ቆብ) በመወልወልና ቅባት በመቀባት ማበጠር ሲሆን በተጨማሪም በእለቱ የሚጫወቱበትን ዱላቸውን ከተሰቀለበት በማውጣት ይወለውላሉ፡፡

- **የእናቶች ቅድመ ዝግጅት፡-** እናቶች ለኢሬቻው ስርአት የተለያዩ ዝግጅቶችን

የሚያከናውኑ ሲሆን ከነዚህም ዝግጅቶች መካከል ለፈጫሳና ለኢሬቻው ስርአት የሚያስፈልግ ምግብ ማዘጋጀት ለምሳሌ፡- ለቂንጩ የሚሆን ገብስ ወይም ስንዴ መከካት፣ ዳቦ መጋገር፣ ለሙዳ ቅቤ፣ማዘጋጀት፣ለምግብ የሚሆን ቅቤ ማንጠር ፣የክት ልብስና የጨሌ ጥብቆ በማጠብ ይዘጋጃሉ፡፡ በኢሬቻው ቀን ጠዋት በመነሳት አቴቴ(ጨሌ) ፈጫሳ ብለው ሲያበቁ ቁርስ በማዘጋጀት ለግጦሽ ከብቶች ያሰማሩ ወንዶች ሲመለሱ ለብቻቸው ገንፎ ወይም ቂንጩ ተዘጋጅቶ ቁርስ ከተበላ ብኋላ ወደ ኢሬቻው ስርአት ለመሄድ ሁሉም ይዘጋጃል፡፡ በክብረ በአሉም እለት ጨሌ ፈጫሳ የማያዘጋጁ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ እናቶች አዲስ የክት ላብሳቸውን ለብሰው ይሄዳሉ፡፡ ለወንዶች ገንፎ ወይም ቂንጩ ለብቻ ቁርስ የሚዘጋጀው ለፈጫሳ የተዘጋጀ ቂንጩ ለወንዶች ስለማይቀርብ ነው በማለት (ወ/ሮ ከበቡሽ ዘለቀ 14/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ) ይገልጻሉ፡፡ ቁርስ ቀርቦ ከተበላ ብኋላ ፈጫሳ ያዘጋጁ እናቶች ጨሌ ጥብቆ (የጨሌ ልብስ) እንደለበሱ ጨሌቸውን ካንገታቸው ሳያወልቁ ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ወደ ዶኒ አድባር በመሄድ የኢሬቻውን ስርአት ለማክበር ይዘጋጃሉ፡፡ ያከባቢው ማህበረሰብ ከዶኒ አድባር በረከት ለማግኘት ቤት ያፈራውን ማንኛውንም ምግብ እንደ ጨኮ፣ በሶ፣ ዳቦ፣ገብስ ቆሎ፣ እሸት በቆሎ፣ ጠላ፣ እንጀራ በዋዜማው በማዘጋጀት ወደ ኢርቻው ስርአት ይዘው ይሄዳሉ፡፡

- **የአባወራዎች ቅድመ ዝግጅት፡-** የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ቀን ከመድረሱ

በፊት ቀደም ብለው በእድር ገንዘብ በማዋጣት ለመስዋዕትና ለእንግዳ መሸኛ የሚሆን ከብት ይገዛሉ፡፡ በዋዜማውም ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ቦታ ማዘጋጀትና ለምግብ ማብሰያ የሚሆን እንጨት በማሰባሰብ እንደሚያዘጋጁ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ ጎልማሳ የሆኑ አባወራዎች የሆኑ አባወራዎች ከወጣቶችጋ ባንድነት በጉግስ ጫወታው ለመሳተፍ የፈረስ እቃ ማስተካከል እና ለደመራ በአል የሚያስፈልግ እርጥብ እንጨት መቁረጥ፣ ጉዝጓዝ ማጨድ፣ለደመራና ዳሞቲ ኮርማ የሚሆን የችቦ እንጨት ማዘጋጀት ሲሆን በእለቱም በሌሊት በመነሳት ከወጣት ወንድ ወነዶች ጋር በመሆን ዳሞቲ ኮርማ (ሌሊት የቀንድ ከብቶች ወደ ግጦሽ ሲወጡ የሚበራ ጭቦ) በመለኮስ የቀንድ ከብቶቻቸውን ለእለቱ ተጠብቆ በቆየ ግጦሽ ሳር (kaloo) ሌሊቱን በማውጣት አግጠው ካጠገቡ ብኋላ ወደ ጊቢ በመመለስ አስተኝተው የተዘጋጀላቸውን ቁርስ ይመገባሉ፡፡ በርካታ ስርአቶች የሚካሄዱት

በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሲሆን ባብዛኛው በእስልምና ተከታዮች ዘንድ አይከናወኑም እነዚህም ልጅ አገረዶች ለዘመን መለወጫ በሚጨፍሩት አበባ አየሆይ ጭፈራ፤ በዳመራ ስርአት፤ ለደመራ ስርአት በሚደረጉ ዝግጅቶች እና የቀንድ ከብቶችን በለሊት ወደ ግጦሽ ማውጣት፤ የፎሌዎች ዝግጅትና ተግባር የመሳሰሉ ስርአቶች ላይ የእስልምና ሃማኖት የማይሳተፉ ሲሆን በሌላው ተግባራት ላይ ሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በእኩልነት ይሳተፋሉ፡፡

## 5.3. የጊዜ ኢሬቻ ስርአተ ከበራ

በዚህ ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ ብሄር፣ ሃይማኖት፣ጾታና እድሜ ሳይለዩ በአንድነት በየአመቱ መስከረም 17 በዶኒ አድባር ስር በመውጣት የሚያከብሩት የምስጋና በአል ነው፡፡ ይህ ስርአተ ከበራ ከ**Reynolds and Erikson (2017፡2)** (Chwe፡ 2003; Clawson፡ 2004; Collins፡1981,)….ወዘተ በመጥቀስ "ስርአተ ከበራዎች አስደሳች የሆነ ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ምድብ ነው። የአምልኮ ሥርዓቶች ማህበራዊ ትስስርን ይጨምራሉ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚይዙ ሲሆን የስርአተ አምልኮው ተካፋዮች ስለ አለም ያላቸውን ግንዛቤ የሚያደራጁበት መዋቅር ይፈጥርላቸዋል" በማለት ያሰፈረውን ሃሰብ የሚያጠናክር ስርአተ ከበራ ነው፡፡ በዚህ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የሚሳተፉ ሁሉም ታዳሚዎች ስለ አከባቢውና ስለ ስርአተ ከበራው ብሎም ስለ አለም ተመሳሳይ ሃሳብ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

የአከባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ትንሽ ሳይል በአንድነት በየቤቱ ለከበራው የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ካጠናቀቀ ብኋላ በየቤቱ ቁርሱን በልቶ ወደ ኢሬቻው ማክበሪያ ቦታ በመውጣት የኢሬቻውን ስርአተ ከበራ በድምቀት ያከብራሉ፡፡ በእለቱም በዶኒ አድባር የኢሬቻ ሰርአት በማክበሪያ ቦታው ቀደም ብለው የሚገኙት ልጅ አገረዶችና ወጣት ወንዶች ሲሆኑ ልጅ አገረዶች ለእንቁጣጣሽ አበባ አየሆይ ጨፍረው ባገኙት ገንዘብ የገዙትን ከረሜላ አድባሩ ስር በመሰባሰብ ይከፋፈላሉ፡፡ ወጣት ወንዶች ፈረሶቻቸውን በመያዝ በአድባሩ አቅራቢያ በመሆንና በመጠባበቅ ሁሉም ሲሰባሰብ የኢሬቻው ስርአተ ከበራ በአባቶች መሪነት ይጀመራል፡፡

በእለቱ ጠዋት ፊጫሳ ያዘጋጀች እናት ለፊጫሳ የለበሰችውን የጨሌ ጥብቆና ጨሌውን ካንገቷ ሳታወልቅ በማለቢያ ወተት፣ የሙዳ ቅቤ፣ በቀኝ እጇ ሲንቄና ጋዲ በመያዝ ከባለቤቷ ጋር በመሆን ከመንገዳቸው ለምለም ሰርዶ ሳርና አዴ አበባ ነቅለው ወደ ዶኒ

አድባር ያመራሉ፡፡ ማህበረሰቡም ትላልቅ ያገር ሽማግሌዎች፣ እናቶች፣ ፎሌዎች፣ ወጣቶችና ልጆች ባንድነት በቦታው በመሰባሰብ ስርአተ ከበራውን በዶኒ አድባር ስር በአባቶች መሪነት የኢሬቻውን ስርአት በምርቃት ያስጀምራሉ፡፡ የኢርቻው ስርአተ ከበራ በምርቃት መክፈት በተመለከተ በቡድት ተኮር ውይይት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ቀደም ባሉት አመታት የኢሬቻውን ስርአት በምርቃት የሚያስጀምሩት ጥንት የኢሬቻውን ስርአት በአድባሩ ስር ያስጀመሩ አባት ለጆች ወይም የቅርብ ዘመድ የሆኑ በቦታው ተተክተው ሲመርቁ ቆይተዋል በዚያንጊዜ ስርአቱን ያስጀመሩት 1ኛ የአቶ መንጃ ቦቄ 2ኛ ዲዶ ገዳ ሲሆኑ አቶ ባልቻ ያደቴ ስእለት በመሳልና የመስዋእት ከብት በማረድ አድባሩን ሲጠብቁና ሲያገለግሉ በመቆየታቸው ከነ ዲዶ ገዳ ዘር በመቀጠል ሶስተኛ ሽማግሌ በመሆን እንዲመርቁና የመስዋእት ከብት እንዲባርኩ በህዝቡ ተመርጠዋል በማለት (8/10/2014ዓ/ም በተደረገ የቡድን ተኮር ወይይት የተገኘ መረጃ)፡፡

በአሁኑ ወቅት በዶኒ አድባር በሚካሄደው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የአቶ መንጃ ቦቄ ዘር የቅርብ ዘመድ የሆኑ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በመሆናቸው ሽሪአ ከለከለን በማለት በኢሬቻው ስርአት ላይ መሳተፍ ስላቆሙና የዲዶ ገዳ ቤተሰብ በስራ ምክንያት ከአከባቢው በመልቀቃቸው በኢሬቻው ስርአት ላይ በእነሱ ምትክ ባከባቢው ባህል መሰረት የታላቅ ጎሳ አባል የሆነ ሽማግሌ ስርአቱን በምርቃት እንዲያስጀምር የተደረገ ሲሆን በዚህም መሰረት በስርአተ ከበራው ላይ የሚመርቀው ከየገላንና ገላን ኮራ ጂዳ ጎሳ የሆኑ ሽማግሌዎች በቦታው በመተካት ሲመርቁ ሶስተኛው የባልቻ ያደቴ የልጅ ልጅ ልጅ የሆኑና በአሁን ሰአት የአድባሩ ሃላፊና የመስዋት ከብት የሚባርኩ አቶ ተሾመ በቀለ በመመረቅ ስርአቱን ያስጀምራሉ፡፡

በዶኒ አድባር በሚካሄደው የኢሬቻ ስርአት ላይ ትላልቅ አባቶችና እናቶች በቦታው ከተገናኙ ብኋላ ሁሉም ባንድነት እናቶችና ያገር ሽማግሌዋችን በማስቀደም አባወራዎችና እማ ወራዎች፣ ወጣት ወንዶችና ፎልዎች ባንድነት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው በመከታተል ስርአቱን ሲያከብሩ ልጃ አገረዶች በነጻነት ደስ ባላቸው ቦታ በመሰለፍ አድባሩን ከምእራብ ወደ ምስራቅ ሶስት ጊዜ “ሆያ መሬሆ” በማለት ይዞራሉ፡፡ መሬ ሆ የሚለው የምስጋና ዘፈን ካበቃ ብሁዋላ ወንዶች በቀኝ ሴቶች በግራ ቆመው በተራ ወንዶች እግዚኦ ሲሉ ሴቶች አቤት ሴቶቹም በተራቸው እግዚኦ ሲሉ ወንዶች አቤት በማለትና

በመቀባበል ፈጣሪ አንተ ስማን እያሉ ካመሰገኑ ብኋላ የያዙትን ሰርዶ ሳርና አዴ አበባ በአምስት ቦታ በማስቀመጥ የኢሬቻውን ስርአት ያከናውናሉ፡፡ ይህን ስርአት በማስመልከት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ይህ ቦታ ለአከባቢያችንና ለሃገራችን ይቅርታ የምንለምንበት ቦታ ነው፡፡ በዚህ ቦታም የሰውልጅ- ከፈጣሪው፣ ሰው- ከተፈጥሮ፣ ምድር- ከሰማይ የሚታረቅበት ቦታ ነው፡፡ ዶኒ ብለን ስንነግረው ከችግር ለሚታደገን ፈጣሪ (waqaa) የምስጋና ኢሬቻ እናቀርባለን፡፡ በስረአቱም ምስጋና ለማቅረብ የሚመጣ ማንኛውም ሰው በሆዱ ቂም መያዝ (gommii qabachu) የለበትም የተጣላም ካለ የምስጋና ኢሬቻ ከመጀመሩ በፊት የተጣላ እንዲታረቅ ይደረጋል አልታረቅም ያለ የኢሬቻውን ስርአት ለማክበር ከወጣው ህዝብ ተለይተው እንዲወጡ ይደረጋል በማለት ይገልጻሉ፡፡(አቶ ደምሴ በሂ በቀን 20/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ)

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ማህበረሰቡ በቦታው ላይ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት የተጣላ የሚታረቅበትና ሰላም የሚወርድበት ቦታ ነው፡፡ ዶኒ አድባር የሰላምና የእርቅ ቦታ በመሆኑ በሆድ ቂም ቋጥሮ ቦታው ላይ መሄድ ከፈጣሪ ያጣላል የዶኒ አምላክ ጥሎን ይሄዳል፤ ቂም በሆዱ የያዘውን ይቀስፈዋል ተብሎ ስለሚታሰብ በዶኒ አድባር ስር የተጣላም ሆነ በሆዳቸው ቂም የያዙ ሰዎች ካሉ ከመታረቃቸው በፊት በአድባሩ ስር በሚከበር የትኛውም ስርአት ከማህበረሰቡ ጋር ተደባልቀው እንዲያከብሩ የሚፈቀድላቸው ሲታረቁና ሰላም ሲያወርዱ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም አቶ ከተማ ደምሴ በቀን21/09/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ)

> የስርአቱን አከዋወን በተመለከተ ሲያብራሩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ የምያከብረው ህዝብ ከተሰበሰበ ብኋላ አድባሩን ሶስት ጊዜ የሚዞሩት ነገር በሶስት ይጸናል ብለው ስለሚያምኑ አድባሩን ሶስቴ ይዞራሉ፡፡ ፊታቸውን ወደምስራቅ ማዞራቸው ምስራቅ የብርሃን መውጫ በመሆኗ መጪውን ብርሃናማ ወቅት በማሰብ ነው፡፡ እንዲሁም ሰርዶ ሳርና አደይ አበባውን በአምስት ቦታ ማስቀመጣቸው ሉባ፣ ቆንዳላ፣ ፎሌ፣ ደበሌ፣ ኢቲ መኮ የሚባሉትን አምስቱን የገዳ ክፍሎች የሚወክል ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

አብዛኛው ማህበረሰብ በዶኒ አድባር ስር በመውጣት አድባራችንን ለምነን ከተለያዩ ከተፈጥሮዊና በሰው ልጅ ጥፋት ከሚከሰቱ ችግሮች ዶኒ እንደሚጠብቃቸውና ዶኒ ለሁሉም

የበላይ ጠባቂ እንደሆነ አብዛኛው መረጃ አቀባች ይገልጻሉ ይህንንም ሃሳብ በማስመልከት በቡድን ተኮር ውይይት ላይ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ዶኒ አድባር ትልቅ ታሪክ ያለው አድባር የነገሩትን የሚሰማ ነው፡፡ ዝናብ ከወቅቱ ሲዘገይ በአድባሩ ስር በመሰባሰብ ስንለምን ይዘንብልናል ከወረርሽኝ በሽታ ይጠብቀናል፣ በዙሪያችን የርስ በርስ ጦርነት ሲነሳ ወተን እግዚኦ ከክፉ ነገር ሰውረን በማለት ባከባቢው ከመጡ ጦርነቶች አድኖናል፡፡ ለምሳሌ ድሮ አባቶቻችን ሲነድሩን የጣሊያን ጦርነት ዙሪያችንን ሲዞረን እዚህ ሳይበርስ ዶኒ ይዞልናል ሲሉ የሰማን ሲሆን በደርግ ጊዜም ቢሆን የተነሳውን የርስ በርስ ጦርነት ያዝልን ብለን በመለመን ቅርብ ቦታ ደርሶ ዶኒ መከታችን በመሆኑ ጦርነቱን ባለበት አብርዶልናል፡፡ ዶኒ አከባቢያችንን ባርኮልን በበረከት እንኖራለን ያሳጣን ነገር የለም ከብቶቻችን ይራቡልናል ዘርተን እናመርታለን ልጆቻችን በጤና ያድጉልናል በቸርነት ስላደረገልን ምስጋናችንን ለምለም ሰርዶ ሳርና አዴ አበባ ይዘን በአድባሩ ስር ለፈጣሪ(ለዋቃ) ምስጋና እናቀርብለታለን በማለት ይገልጻሉ፡፡ (አቶ ዲንቂ ሰቦቃና ተሸመ በቀለ 2/10/2014 በተደረገ ቡድን ተኮር ውይይት)

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ዶኒ አድባር ያከባቢውን ማህበረሰብ፣ የቤት እንሰሳቱንና አዝመራውን ከክፉ ነገር እንደሚጠብቅ እና ባርኮ በደስታ የሚያኖራቸው በዶኒ አድባር አማካይነት ዋቃ እንደሆነ የሚገልጽ ሃሳብ ነው፡፡ ሲሆን በዶኒ አድባር ላይ አድሮ ይህን ላደረገላቸው ፈጣሪ (ዋቃ) ለምለም ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ በመያዝ በየአመቱ መስከረም አስራ ሰባት ዶኒ አድባር ስር በመውጣት የምስጋና ኢሬቻ እንደሚያቀርቡ የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡

በዚህ በዶኒ አድባር ስር መስከረም አስራ ሰባት የሚከወነው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ወቅቱን ጠብቆ በያመቱ የሚካሄድ ሲሆን በስርአተ ከበራው እለት የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎች የሚካሄድበት ስርአት ነው፡፡ የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚወጡ ሰዎች በየዓመቱ በ መስከረም ወር ከጭጋጋማው ክረምት በሰላም ወደ ብርሃናማው ጸደይ ላስተላለፋቸው ለአንድ ፈጣሪ (waqaa tokkichaaf) የሚያከብሩት የምስጋና ኢሬቻ ነው፡፡

### 5.3.1. የኢሬቻ ስርአት አከዋወን

በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ወደ ዶኒ አድባር ለማክበር ሲመጡ ከመንገዳቸው ቀንበጥ ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ በመንቀል ይዘው በአድባሩ አቅራቢያ በመሰባሰብ ማህበራዊ ደረጃቸውን ጠብቀው ትላልቅ ያገር ሽማግሌዎች፣ እናቶች አውሊያ (ውቃቢ ያላቸው ግለሰቦች፣ ቃሉዎች ባንድነት ከፊት ሲቀድሙ አባወራዎችና እናቶች፣ ወጣቶችና ፎሌዎችን በማስከተል በቅደም ተከተል በመከታተል ስርአቱን ያከብራሉ፡፡ በዚህ ስርአት ላይ ልጅ አገረዶችና ልጆች ደስ ባላቸው ቦታ በመሆን የምርቃት ስርአቱን ይከታተላሉ፡፡ በስርአቱ ላይ ምርቃት የሚመርቁትና የኢሬቻውን ስርአት የሚመሩት ሽማግሌዎች የሚውጡት ከገላንና ገላን ኮራ ጂዳ ጎሳ የሚመረጡ ሲሆን በሶስተኛነት ከላይ እንደተጠቀሰው አቶ ተሾመ በቀለ ቢጋራ በመሆን ለማክበር የመጣውን ህዝብ በመመረቅና የኢሬ ቻውን ስርአት በማስጀመር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ እንዲከናወን ከምርቃት በመጀመር ይመራ ሉ፡፡ ይህ ሃሳብ ከFrank (2004፡6) ሥርአተ ከበራ ልዩ ተግባር ሲሆን ስርአቱን የሚመሩ (የሚያ ስፈጽሙ) ሰዎች ይፈልጋል፡፡ ከሚለው ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡

ከገላንና ከገላን ኮራ ጂዳ ጎሳ የተመረጡ ሽማግሌዎች በቦታው የተሰበሰበውን ህዝብ ስርአተ ከበራው ከመጀመሩ በፊት በመመረቅ ስርአቱን የሚያስጀምሩ ሲሆን በምርቃቱ ላይ የተሰበሰበው ህዝብ በአንድነት አሜን አሜን በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ በቦታው የሚቀርብ ምርቃት

Waaqni nagaan nubulche nagaan nu haa oolchu

በሰላም ያሳደረን አምላክ በሰላም ያውለን

Biyya keenya biyya amaanaa nuuf haa godhu

ሃገራችንን የሰላም ሃገር ያድርግልን

Kan biyya Ormaatti dhageenu nurraa haa qabu

በሰው ሃገር የምንሰማውን በዛው ይያዝልን

Tulluun doonni tun waajjin deemte Lola dhageenu kana waaqni bishaan hagodhu

ዶኒ አድባር አብራ ዘምታ የምንሰማውን ግጭት ፈጣሪ ውሃ ያድርግልን

Goota keenyaa daangaa biyyaa kabachiisuf deemee waaqni nagaan hadeebisuu

ሃገሩን ለመጠበቅ የሄደውን ጀግና ፈጣሪ በሰላም ወደ ቤቱ ይመልስልን

Akkuma kalleesaa dhageenuutti doonniin biyyaa nagaa nuhagodhu

ትናንት እንደምንሰማው ዶኒ ሃገራችንን ሰላም ያድርግልን

Mangistii kenyaa sirreerati nuhaabulchuu

መንግስታችንን በዙፋኑ ያቆይልን

Biyyaa kenyaa biyyaa nagaa nuhaagodhuu

ሃገራችንን የሰላም ሃገር ያድርግልን

Biyyii yoo jirraate jirranaa kannaaf

ሃገር ሲኖር ነውና የምንኖረው ስለዚህ

Biyyaa kenyaa nagaan nuhajirraachisuu

ሃገራችንን በሰላም ያኑርልን

Akkuma guuttuu taanne doonniin guuttuu nuhaatasiftu

ዶኒ እንዲሁ ሙሉ እንደሆንን ለቀጣዩም ሙሉ ያድርገን

Doonniin fayyaa keenyaa nuhaakennuu

ዶኒ ጤናችንን ይስጠን

Waaqni waggaa moofaa irraa gara waggaa haarraatti nudabarse

ካሮጌው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን ያሸጋገረን ፈጣሪ

Ammaas ifaatti nuhaabasuu

አሁንም ወደ ብርሃናማው ያሸጋግረን

Azmaraa ijaan arginnee kana moo firritti jijjiiree Nama nyaatu nuhaa godhu

ይህን በአይናችን የምናየውን አዝመራ ወደ ፍሬ ቀይሮ የምንመገብ ያድርገን

Nama bulleesa dirreeti haabulchu

ትላልቅ ሰዎችን ባከባቢው ያቆይልን

Labata nu jalattii haa guddisuu

ታዳጊውን በስራችን ያሳድግልን

Ummaan ummaa haabektu

ተፈጥሮ ተፈጥሮን ትወቅ

Saffuun saffuu haa beektuu

ሁሉም ስርአቱን ይወቅ

Malkaan tuulluutti halallabduu

መልካው ለጋራው ያመልክት

Tuulluun immo malkaatti haa lalabduu

ጋራው ደግሞ ለመልካው ያመልክት

Boru lubbuun Bara kana Bara nagaa haa godhuu

ለነገ ሰላማችን ይህ ዘመን ነውና ዘመኑን ሰላም ያድርግልን

Bara kana jalaa nagaan nuhaabasuu

ከዘመንዘመን በሰላም ያሸጋግረን

Ummaan nuhaabattu

ፈጣሪ በፍጥረቱ ይጠብቀን

Doonniin nuhaabattu

ዶኒ ይጠብቀን

Kan bitan dhuffe mirgaatti nuhabasuu

በግራ የመጣውን በቀኝ ይመልሰው

Nabi alaahu masalii!! ነቢ አላሁ መሰሊ! በማለት ምርቃታቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ በዚህ ምርቃት የተላለፈው መልእክት ፈጣሪ ህዝቡን እንዲጠብቅ በሃገር ላይ የመጣውን ጦርንት እንዲያጠፋላቸውና ለህዝቡም ሆነ ለእንሰሳቱ ጤና እንዲሰጣቸው ካሮጌው ዘመን ወዳዲሱ በሰላም እንዳስተላለፋቸው ከክረምቱ ወራት ደግሞ ፈጣሪ በሰላም ወደ ብርሃናማው የጸደይ ወራት እንዲያስተላልፋቸው ምኞታቸውን የገለጹበት ምርቃት ሲሆን በተጨማሪም በሃገርና በነሱ ክፉ የሚያስበውን ዶኒ እንደስራው እንዲሰጠው ተራራው፣ ሸለቆው፣ ምድርና ሰማይ ተስማምተው ሃገራቸው ሰላም እንዲሆን ምኞታቸውን የገለጹበት ስርአት ምርቃት ነው፡፡ የምርቃት ስርአቱ ሲጠናቀቅ ሁሉም የበአሉ ከዋኝ ባንድነት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ሆ ያ መሬ ሆ በማለት የምስጋና ዘፈን በመቀባበል እያዜሙ አድባሩን ከምራብ ወደ ምስራቅ ሶስት ጊዜ አድባሩን ይዞራሉ፡፡ የሚቀርበውም የምስጋና ዘፈን እንደሚከተለው ነው፡፡

a/ hoo, yaa maaree hoo! ------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ hoo, yaa maaree hoo! ------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ yaa waaq, si kadhanna, yaa mareehoo!---ፈጣሪ ሆይ እንለምንሃለን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! -----------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Ati nuu dhagahi yaa mare hoo!-----------አንተ ስማን መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ---------------------ሆ ያ መሬ ሆ!

a/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------ሆ ያ መሬ ሆ!

b/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ abaabbon birraa daraaradha yaamaree hoo! ------አደይ አበባ አበባነው ያ መሬሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ namni wallaaladha yaa mere hoo! ---ሰው ስህተተኛ ነው ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Gumguma ganna nagaan nu baafte ,yaa mare hoo!----ከጭጋጋማው ክረምት በሰላም አወጣኸን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! --------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Galata kee jennaa yaa mare hoo! ----------------ተመስገን እንልሃለን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ---------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ kunoo irresaa kee siif irreeffannaa,yaa mare hoo! ------ይኸው ኢሬሳኸን ላንተ እንሰጣለን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! --------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ maaree hoo! -------------------- መሬ ሆ

b/ maaree hoo! ------------------- መሬ ሆ

a/ maaree hoo! -------------------- መሬ ሆ

b/ maaree hoo-------------------- መሬ ሆ

a/ yaa waaqa wa maraa umte, yaa mare, hoo! ------ፈጣሪ ሆይ ፈጠርከን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ---------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ uumte nu badhaaftee yaa mare hoo! --------------ፈጥረኸ አትጣለን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ sigalatefana, yaa maaree hoo! ---------------------እናመሰግንሃለን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, yaa maaree hoo! ----------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ fayyaa fi nagaan nu tiksi yaa maaree hoo! --በሰላምና በጤኛ ጠብቀንያ መሬ ሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! ----------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Tokkumman nu jirraachisii Yaa maaree hoo!--አንድነታችንን አጠናክርልን ያ መሬሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! -----------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Arfaasaa fi birraan, wal maree, yaa mare hoo!----በልግና ጻደይ ዞረልን ያ መሬ ሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! ------------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ doni baneet siif ireeffaana yaa mare hoo!---ዶኒ ወተን ኢሬሳ እንሰጥሃለን ያ መሬሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! -------------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ Irreessaan sitti marmaarre, yaa mare hoo! ----------ኢሬሳው ከቦሃል ያ መሬ ሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! -------------------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

a/ kan dhibame, nuu maari, yaa mare hoo---የታመሙትን ማርልን ሆ ያ መሬ ሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo! ------------------------ሆ ያ መሬ ሆ

b/ kan hidhame nuuf hiiki maaree hoo! ------በስር ያሉት ፍታልን ሆ ያ መሬ ሆ

b/ hoo, Yaa maaree hoo!----------- ሆ ያ መሬ ሆ

a/ maaree hoo! ---------------------- መሬ ሆ

b/ maaree hoo! ---------------------- መሬ ሆ

a/ maaree hoo! ---------------------- መሬ ሆ

b/ maaree hoo! ---------------------- መሬ ሆ

በማለት የሚያዜሙ ሲሆን ይህ የምስጋና ዘፈን ሁለት አይነት ይዘት ያለው ነው፡፡ አንደኛ ፈጣሪ ዘመኑን በሰላም አዙሮ ከወቅት ወደ ወቅት በሰላም ስላሸጋገራቸው ለዋቃ የሚያቀርቡት ምስጋና ሲሆን ሁለተኛው ሃሳብ ተስፋን የሚያሳይ ነው፡፡ የምስጋናው ዘፈን ላይ የሚቀርበው የተስፋ ዘፈን ሃገራቸውን እንዲጠብቅላቸው፣ በሰላም እንዲያኖራቸው፤ ህዝቡን ከህዝቡ ህዝቡን ከፈጣሪው ቃል ለቃል አግባብቶ በአንድነት እንዲያኖራቸው፤ የታመመውን እን ዲምርላቸው፤ የታሰሩትን እንዲያስፈታላቸው፣ አዝመራውን ወደ ፍሬ እንዲቀይርላቸውና ከተለ ያዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ሀገራቸውን ጠብቆ ሰላም እነዲያደርጋቸው የሚያቀርቡት የልመና ዘፈን ነው፡፡ በአጠቃላይ ላለፈው ምስጋና የሚያቀርቡበትና ለወደፊቱም መልካም ነገር እንዲገጥማቸው ፈጣሪን የሚለምኑበት ዘፈን ነው፡፡

የአከባቢው ማህበረሰብ በቢራ (በጸደይ) ወቅት በመልካ ወይም በአድባር በመውጣት ስር በመውጣት ላለፈው ምሰጋና ለወደፊቱም በቸርነቱ የሚያስፈልጋቸውን እንዲሰጣቸው ለፈጠራቸው (ለዋቃ) የልመና ጸሎትና ተማጥኖ የሚያቀርብበት ስርአት ነው፡፡ በዚህ በሎዴ ሂጦሳ ወረዳ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የምስጋና ኢሬቻ ሲሆን በኢሬቻው ስርአት ላይ ከዋኙ ማህበረሰብ አድባሩን መሬሆ በማለት ሶስት ጊዜ ከዞሩ ብኋላ ወንዶች በቀኝ ሴቶች

በግራ በመቆም ሁሉም በአንድነት ላለፈው ይቅር እንዲላቸው ለወደፊቱም በቸርነቱ እንዲጠብቃቸው ለፈጣሪ (ለዋቃ) የልመና ጥሪያቸውን እግዚኦ በማለት እንደሚከተለው ወንዶች በቀኝ ሴቶች በጋራ በመቆም ተቀባብለው ያሰማሉ፡፡

ወንዶች---------እግዚኦ (5)

ሴቶች ----------አቤት (5)

ሴቶች ----------እግዚኦ (5)

ወንዶች----------አቤት (5) በማለትና በመቀባበል በአድበሩ ስር ፈጣሪን ይለምናሉ፡፡ መጀመሪያ ወንዶቹ ሁሉም በአንድነት እግዚኦ ሲሉ ሴቶች በመቀበል አቤት የሚሉ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር ወንዶች አምስት እግዚኦታ ሲያቀርቡ ሴቶቹም አምስት ጊዜ አቤት በማለትና በመቀባበል ፈጣሪን ይለምናሉ፡፡ በሁለተኛው ዙር ሴቶቹ እግዚኦ ሲሉ ወንዶች አቤት በማለትና በመቀባበል በሁለት ዙር አስር እግዚኦታና አስር ጊዜ አቤት በማለት ፈጣሪን(ዋቃን) ምህረት ይለማመናሉ፡፡

በእግዚኦታው ስርአት ላይ ወንዶች በቀኝ ሴቶች በግራ ሆነው ፊታቸውን ወደ ምስራቅ የሚመልሱት ምስራቅ የፀሀይ መውጫ ብርሃን የሚታይበት በመሆኑ ወደ ብርሃናማው ወራት በሰላም አስተላልፈን የሚል መልክት የያዘ ሲሆን ሴቶችና ወንዶች ተለያይተው በመቀባበል እግዚኦ የሚሉት ፈጣሪ ሆይ ስንጠራህ አንተ አቤት በለን ሀገራችንን ከክፉ ነገር ጠብቅልን ጥፋታችንን ሳታይብን ስንጠራህ አቤት በለን ከከፉ ነገር ሁሉ ጠብቀን ለማለት ነው፡፡ ሲሉ (አቶ ከፌያለው ፋንታ በቀን 18/09/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ) ይገልጻሉ

ፎቶ ግራፍ አንድ፡- ወንዶች በቀኝ ሴቶች በግራ ቆመው እግዚኦ ሲሉ የሚያሳይ ምስል፡፡



ምንጭ፡- ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘ ምስል፡፡

#### 5.3.1.1. ለኢሬቻው ስርአት ሳርና አበባ አመራረጥና ኢሬቻ አቀራረብ

ምድር በጋውን ወራት በጸሀይና በሙቀት አሳልፋ በክረምቱ ዝናብ በውስጧ የያዘችውን በማብቀል ክረምቱን በአረንጓዴ ተቀይራ በጸደይ ወራት ወደ አበባ ቀይራ በሙቀት በመብሰል አዝእርቱና እጽዋቱ ወደ ፍሬ የሚቀየርበት፤ የቤት እንሰሳት በወቅቱ የሚራቡበትና የወተት ምርት በብዛት የሚሰጡበት ወቅት ነው፡፡ ወቅቱ ተስፋ የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ወቅት ያከባቢው ማህበረሰብ በአድባሩ ስር በመውጣት ከጭጋጋማው የክረምት ወራት አሳልፎ ወደ ሞቃታማው የጸደይ ወራት በሰላም ጠብቆ ላሻጋገራቸው ፈጣሪ ላለፈው ምስጋና ለወደፊቱም በቸርነቱ ከክፉ ነገር ሁሉ እንዲጠብቃቸው ለምለም ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ በመያዝ የምስጋና ኢሬቻ የሚያቀርቡበት ስርአተ ከበራ ነው፡፡

ፈጣሪ በቸርነቱ ከፈጠራቸው እጽወቶች መካከል ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ ለፈጣሪ የሚቀርብ የምስጋና ስጦታ ሲሆን በኢሬቻ ስርአት ላይ ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርቡ ሲሆን ከመንገድ ለምለም ሰርዶ ሳር እና አደይ አበባ በመንቀል በአድባሩ ስር ኢሬቻ በማድረግ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ ለኢሬቻ ስርአት የሚቀርበው ሰርዶ ሳር እና አደይ አበባ የቤት እንሰሳት ያልነኩትና ያልተበጠሰ ንጹህ መሆን አለበት፡፡

በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚሳተፍ ሁሉም ሰው ንጹህና ያልተበጠሰ ለምለም ሰርዶ ሳር እና አደይ አበባ በመንቀል ይዘው በአድበሩ ስር የኢሬቻ ስርአት ይፈጽማሉ በስርአቱም ትላልቅ ሽማግሌዎችና እናቶች በመጀመሪያ ሳርና አደይ አበባውን በማስቀመጥ የኢሬቻውን ስርአት ሲያከናውኑ ከነሱ በመቀጠል ሁሉም የበአሉ ተሳታፊ ማህበራዊ ደረጃቸውን ጠብቀው በቅደም ተከተል የኢሬቻውን ስርአት ያከናውናሉ፡፡ ሰርዶ ሳርና አደይ አበባውን በመከፋፈል በአምስት ቦታ ላይ በማስቀመጥና አድባሩን በመሳለም የኢሬቻውን ስርአት ያከናውናሉ፡፡ ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ የተመረጠበትን ምክንያት በማስመልከት (አቶ ደምሴ በሂ በቀን 11/09/2014 ዓ/ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ) እንደሚከተለው ይገልጹ፡፡

ሰርዶ ሳር ስሩ በአፈሩስጥ ተስፋፍቶ የሚገኝ ባለብዙ አንጓ ሲሆን ሳሩ የሰውን ዘር መብዛት የሚወክልና የጎሳን መስፋት የሚያሳይ ነው፡፡ አዴ አበባ በአመቱስጥ በጸደይ ወር የሚበቅል ተስፋን የሚያሳይ ከጭጋጋማው የክረምት ወራት ወደ ብርሃናማው የጸይ ወራት በሰላም ለመሸጋገር ተስፋ በማድረግና አበባ ሆኖ ያለውን አዝመራ ወደ ፍሬ እንደሚቀይርላቸውና የታዳጊ ወጣቶችን የሃገር መረከብ ተስፋ በማድረግ የሚቀርብ የምስጋና ስጦታ በማለት ያብራራሉ፡፡

ይህ ሃሳብ የሚያሳየን ሰርዶ ሳርና አደይ አበባ እንደአከባቢው ማህበረሰብ ትርጉም አዘል ሲሆን ሰርዶ ሳር የጎሳን መስፋፋት ሲያሳይ ሰርዶ ሳር በባህሪው ለስላሳና ገር መሆኑ ለፈጣሪ ታዛዥ መሆንን ያሳያል አደይ አበባ ተስፋ ነው፡፡ ተስፋ አንደኛ በወቅቱ ያለው አዝመራ አበባ በመሆኑ ከአበባ ወደፍሬ ቀይርልን የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ተስፋ ለጋ የሆኑ ልጆችን አሳድጎ መልካም ደረጃ ላይ እንዲያደርስላቸው ተስፋ በማድረግ እነደሆነም (በቀን 05/10/2014 በቡድን ተኮር ውይይት ላይ ይገልጻሉነው)፡፡

ሰርዶ ሳርና አደይ አበባውን ከአድባሩ አጠገብ በአምስት ቦታ ኢሬቻውን በማስቀመጥና አድባሩን በመሳለም ስርአቱን ይፈጽማሉ ይህንንም ሃሳብ በማስመልከት በቡድን ውይይት ላይ አቶ በቀለ ታደሰ በቀን 2/10/2014 በተደረገ የቡድን ውይይት) "ሰርዶ ሳርና አደይ አበባውን በአምስት ቦታ በማስቀመጥ የኢሬቻውን ስርአት የሚያከናውኑት አምስት በገዳ ስርአት የሚገኙትን አምስቱን የገዳ ደረጃዎች የሚወክል ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው በኢሬቻው ስርአት ውስጥ ሰርዶ ሳርና አዴ አበባው በአምስት ቦታ መቀመጡ በኦሮሞ ገዳ ስርአት ውስጥ አምስቱን የገዳ ደረጃዎች የሚወክል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ፡2 ሰርዶ ሳርና አደይ አበባውን ኢሬቻ ሲያስቀምጡ የሚያሳይ



ምንጭ፡-ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘ ምስል

### 5.3.1.2. ፈረሰኞች በኢሬቻው ስርአት ላይ ያላቸው ተሳትፎ

በኢሬቻው ስርአት ላይ ከሚሳተፉ በተለየያዩ የፈረስ ማህበሩስጥ የታቀፉ ሲሆኑ ሁሉም ወደ አድባሩ ከመምጣታቸው በፊት በየቤታቸው ጠዋት ተነስተው ወደ ከበራው ቦታ ከመሄዳቸው በፊት ቁርስ በልተው ፈረሶቻቸውን ባማሩና በተዋቡ እቃዎች ከጫኑ ብኋላ ያላገባ ወጣት ከሆነ እናቱ ባለትዳር ከሆነም ባለቤቱ የሙዳ ቅቤ በማውጣት ፈጣሪ ይጠብቅህ አሸንፈህ በድል ተመለስ የዶኒ አምላክ ይከተልህ በማለት መርቃ ፈረሰኛውን ግንባሩን ሙዳ በማለት (ቅቤ መቀባት) ፈረሱንም ግንባሩን፣ ደረቱንና ከጅራቱ ከፍ ብላ ሙዳ በማለት ትሸኛለች፡፡ ፈረሰኞች በአድባሩ ስር በመሰባሰብ ህዝቡ የኢሬቻውን ስርአት አከናውኖ እስኪጨርስ ፈረሰኛውም በአድባሩ ዙሪያ ከበው በመቆም ይጠባበቃሉ ህዝቡም የኢሬቻውን ስርአት ሲያጠናቅ ፈረሰኛውም በተራው አድባሩን ሆያ መሬ ሆ በማለት ሶስት ጊዜ በመዞርና ስርአቱን በማጀብ ከፈረሶቻቸው ወርደው የያዙትን ሳርና አበባ እንደ አባቶች በአምስት ቦታ በማስቀመጥና አድባሩን በመሳም የኢሬቻውን ስርአት ያከብራሉ፡፡ ሳርና አበባ በመያዝ ለፈጣሪ (ዋቃ) ኢሬቻ በማቅረብና ፈጣሪን ካመሰገኑ ብኋላ አባቶች ሂዱ ተጫወቱ ፈጣሪ የደስታ ጫወታ ያድርግላቹ ዶኒ ይከተላቸሁ በማለት መርቀው ሲሸኟቸው ወደ ጉግስ መጫወቻው ሜዳ በመሄድ በፈረስ ጉግስ ውድድር ይጫወታሉ፡፡

### 5.3.1. የመስዋዕት አቀራረብ

Zegeye (2017፡16) (Orent፡1969) (Yiheew፡2002) እና Yeshambel፡2009)ን በመጥቀስ ስርአተ ከበራ ጠንካራ አካባቢያዊ እውቀት የሆነ፤ በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው፣ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ዋጋ ሰጥቶ የሚያዘጋጀው ሲሆን ምስጋና፣ መስዋዕት

እና ስጦታ የመሳሰሉ ስርአቶች የሚቀርቡበት ነው፡፡ በማለት የገለጸውን ሃሳብ የሚያጠናክር ስርአተ ከበራ ነው፡፡ ይህ በዶኒ የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የአከባቢው ማህበረሰብ ገንዘብ በማዋጣትና በስዕለት የሚገኘውን ገንዘብ ባንድ ላይ በመያዝ እንደተገኘው ገንዘብ ኮርማ በሬ ወይም ወጠጤ በግ በመግዛት መስዋእት የሚያቀርቡ ሲሆን በእለት ለመስዋእት የሚቀርበው ከብት መልክ ነጭ ነው፡፡ ከጠፋም እንዳማራጭ ዳለቻ ወይም ቡሌ መልክ ያለው ኮርማ ወይም ወጠቴ በግ ለመስዋዕት ይቀርባል፡፡ ይህንን ለመስዋእት የሚቀርቡትን እንሰሳት በልክ በተመለከተ አቶ ንጉሴ ተሊላ በቀን 12/09/2014 እና አቶ ተሸመ በቀለ (በቀን 18/09/2014 ዓ/ም በተደረገ ቃለመጠይቅ ሲገልጹ

> በጸደይ ወራት ለመስዋዕት የሚቀርበው ከብት ነጭ መልክ ያለው ነው ከጠፋም እንዳማራጭ ዳለቻ ወይም ቡሌ ከብት ይቀርባል እንጂ ከዚህ መልክ ውጪ ያላቸው እንሰሳት በጸደይ ወር ለአዳባር መስዋእት አይቀርቡም፡፡ ነጭ ዳለቻ ወይም ቡሌ ከብት ወቅቱንም የሚያሳዩ ብርሃንን የሚያሳዩ በመሆናቸው ነው ለመስዋእት የሚቀርቡት በማለት ያብራራሉ

የመስዋዕቱን ከብት መባረክና መስዋዕቱን ለአድባሩ የማቅረብ ሃላፊነት የተሰጠው ለባልቻ ያደቴ ዝርያ ሲሆን ይህን በማስመልከት የልጅ ልጅ ልጅ የሆኑ በአሁኑ ሰአት የመስዋእት ከብት እርድ የሚፈጽሙ አቶ ተሸመ በቀለ (በቀን 18/09/2014 ዓ/ም በተደረገ ቃለመጠይቅ)

> ጥንት ቅም ሃያታችን ልጅ በማጣቱ ለዶኒ ተስሎ ልጅ ስላገኘ ብዙ ጊዜ ነጭ ኮርማ በማምጣት ለአድበሩ መስዋዕት በማቅረብ የመጣውን እንግዳ በማብላት እንግዶችን ያስተናግ ነበር በዚህም ወቅት ላድባሩ ባለው ክብር ያከባቢው ማህበረሰብ አድባሩን እንዲ ጠብቅና ለአድባሩ ሃላፊ ሆኖ የመስዋዕት ከብት እንዲባርክ፣ አድባሩን እንዲጠብቅና የኢሬቻውን ስርአት በምርቃት እንዲያስጀምር ሃላፊነት ተሰቶታል፡፡ ቅም ሃያታችን አቶ ባልቻ ያደቴ የተሰጠውን ሃላፊነት ልጆቹ ተቀብለው እንዲያስቀጥሉ በመደረጉ አሁን ካባቴ ተቀብዬ ስርአቱን ፈጽማለሁ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በዶኒ አድባር ስር በሚካሄደው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የመስዋዕት ከብት የሚባርከው ሰው ባይኖር እንኳን ወንድም ወይም የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው በቦታው ተተክቶ

እንዲባርክ እና መስዋዕቱን እንዲያቀርብ ይደረጋል እንጂ ሌላ ሰው በቦታው ተተክቶ መስዋዕት ማቅረብ አይችልም፡፡

የመስዋዕት ከብት የሚታረደው ሳርና አደይ አበባ ተቀምጦ ይዘው የኢሬቻው ስርአት ከተካሄደና ከተጠናቀቀ ብኋላ የመስዋዕት ከብት ቀርቦ ሁለት ትላልቅ ሽማግሌዎች ከታላቅ ጎሳ በመውጣት ህዝቡን መርቀው ሶስተኛ የመስዋእት ከብት የሚባርኩት ሽማግሌ አቶ ተሽመ በቀለ ቢለቸውን ይዘው በመቅረብ እንደ ሚከተለው ምርቃታቸውን ያቀርባሉ፡፡

Waqni nagaan nubulche nagaan nuhaa olchu--በሰላም ያሳደረን አምላክ በሰላም ያውለን

Kenaa abdari qaltan kanaa waqni isin ira hafudhatu--ያቀረባችሁትን መስዋእት ፈጣሪ ይቀበላችሁ

Saawaan keesan haa horan ------------------ ላሞቻችሁ ይራቡላችሁ

Kuno isinis bilchaataa donif dhiyesitani-----ይሄው እናንተም የበሰለውን ለዶኒ እንዳቀረባችሁ

Donnin dheedhii bakka isiniif haa buusu------ዶኒ የማይበላሸውን ጥሬ በቦታው ይተካላቹ

Saddeet sagaliin isiniif haa guutu---------------ስምንቱን በዘጠኝ ይተካላቹ

Guutuun guutuu isiniif haa ta'u---------------- ሙሉ ሙሉ ይሁንላችሁ

Sa'aa namaan nagaa isiniif haa hata'u------ላሞችና ሰዉ ሁሉም ሰላም ይሁን

Kan guute keessa isin oolchee haa bulchu----በሞላ ቤት አውሎ ያሳድራቹ

Kunno ababoo arginu kana fiirritti nuhaajijjiru----የምናየውን አበባ ወደ ፍሬ ይቀይርልን

Waan qotattan isiniif haa barkatu----------------ያዘመራችሁት ይበርክት

Sa'aa tikseen isiniif haa horu-------------------የምታሰማሯቸው ላሞች ይራቡላችሁ

Qotiyyoo qanbaratti------------------------------በሬውን በቀንበር

Dhaltii okoleetti-----------------------------------ላሞቹን በማለቢያቸው

Fardaa collee koraatti ----------------------ጮሌውን ፈረስ በኮርቻው

Waatii manatti hatursisu ---------------------ጥጆችን በቤት ያቆይልን

Rooba gannaa nagaan isin baasee ------ከክረምቱ ዝናብ በሰላም አሳልፎ

Gara birraatti nagan isini haadabarsu --- ወደ ጸደይ ወራት በሰላም ያሸጋግራችሁ

Fageenyaa dhihaatee----------------------------የራቀውን ያቅርብላችሁ

Dhiheenyaa awwaatee--------------------------የቅርቡ አቤት ይበላችሁ

Ala qabatee-----------------------------------------የውጪውን ይዞ

Abdaariin nagaa isiniif haa kennu -------------አድባራችን ሰላማችንን ይስጠን

Nabi qabatee firaa tiskee isiniif haa eegu------ያባቶቻችን አምላክ ወገኖቻችንን ይጠብቅልን

Taba kessan Kan gamachuuf jaalalaa isiinif hata'u---ጫወታችሁ የደስታና የፍቅር ጫወታ ያድርግችሁ

Waqni donni Fardaf Nama garmmamaf bahe nuhaa eguu---የዶኒ አምላክ ለጉግስ ጫወታ የወጣውን ሰውና ፈረስ ይጠብቅልን፡፡

Waqni gamachun isiinni adebisu -- ፈጣሪ በደስታ ይመልሳችሁ

Baka anaa wallaleti waqni haguttu -- ባጎደልኩ ፈጣሪ ይሙላ፡፡

የዚህ ምርቃት ይዘት የሚያመለክተን በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ አዋተው ለመስዋዕት ከብት የገዙትንና በስዕለትም ሆነ በአከባቢ መዋጮ ምግብና መጠጥ ያመጡትን ሰዎች ዶኒ በቤታቸው በረከት እንዲሰጣቸው የእንሰሳቱንና የማህበረሰቡን ጤና እንዲጠብቅ ሃገራቸውን በበረከት እንዲባርክላቸውና እንዲጠብቅላቸው መንግስታቸውን በዙፋን እንዲያቆይላቸው የሚጫወቱ ወጣቶች በፍቅርና በደስታ እንዲጫወቱ እንዲሁም ከክፉ ነገር እንዲጠብቃቸው ምኞትን የያዘ  ምርቃት ነው፡፡ በቦታው የመመረቅ ስልጣን የተሰጣቸው አባቶች ከታላቅ ጎሳ የተመረጡ ሽማግሌዎች ሲሆኑ እነዚህም በአከባቢው የሚመርቁት ሽማግሌዎች ከገላን ፣ከገላን ኮራ ጂዳ፣ ጎሳ የመጡ ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ የታላቅ ጎሳ አባል ወጣት ቢሆን እንኳዋን በስርአቱ ላይ ካለ የታናሽ ጎሳ በእድሜ ትልቅ ስለሆነ እንዲመርቅ አይፈቀድም በዚህም መሰረት የታላቅ ጎሳ አባል የሆነ ሰው ከሌለ እንደ ቅደም ተከተላቸው በመውረድ የታናሽ ጎሳ አባል በመውረድ በምትኩ እንዲመርቁ ይደረጋል መዚህም መሰረት ገላን፣ ገላን ኮራ ጂዳ፣ ጉምቢቹ፣ ጉለሌ፣ ጂዳና የሜታ ጎሳ አባል የሆኑ እንዲሁ ታላቅ ጎሳ ባሌለበት ቦታ በመተካት ካሌለ ታናሽ በመተካት ይመርቃሉ፡፡ በእለቱም ለመስዋእት የቀረበውን የእርድ ከብት ወጣቶች በመተባበር ወደቀኝ ሲጥሉ  የሚባርኩት ሰው ዶኒ መስዋእታችንን ተቀበለን ሃገራችንን ሰላም አድርግልን በማለት ሲባርክ መጀመሪያ የሚፈሰውን ደም የሚባርከው ሰው ባለቤት የሆነችው በእቃ በመቅዳት ደምና ቅቤ ይዘው አድባሩን ሙዳ በማለት ደሙን በአድባሩ ላይ ቀብተው የተረፈውን አድባሩ ስር ያፈሱታል፡፡

የታረደው ከብት የስጋው ብልት ወቶ ካለቀ ብኋላ ከየብልቱ ላይ በመቁረጥ በበረምጣድ በመጥበስና በማሳረር ጥብስ (ciincaa) በማድረግ ለሁሉም ሲሸት ከመጣው ጸበልና ጻዲቅ ጨምረው በአድባሩ ስር በአንድ ቦታ በማስቀመጥ መስዋዕቱን እናቅባለን ከሁሉም ብልት የሚቆረጥብት ምክኒያት ሁሉም ነገራችን የፈጣሪ ነውና ሁሉንም ነገራችንን ላንተ ሰጠናል አንተ ጠብቅልን እሱ ፈጣሪ እንዲጠብቅ ልን ነው በማለት (በቀን 18/09/2014 ዓ/ም አቶ ተሸመ በቀለ እና ወ/ሮ ፀሀይ ሰንበታ በተደረገ ቃለመጠይቅ ያብራራሉ)፡፡

አድባሩን ቅቤ ሙዳ ማለትና የደም መስዋዕት ለፈጣሪ የሚያቀርቡት ስርአት በምእራፍ አራት ላይ አካባቢያዊ ዳራ ላይ እንደተጠቀሰው ያከባቢው ማህበረሰብ ከፊል አርብቶ አደር መሆኑ የራሳቸውንና የቤት እንሰሳቶቹን ጤና እንዲጠብቅላቸው ለአድባሩ ሙዳ በማለትና የደም መስዋዕት በማቅረብ ፈጣሪን የሚለማመኑበት ስርአት ሲሆን ይህ ተግባር ካከባቢው ማህበረሰብ ህይወት ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡

### 5.3.3. ለዶኒ አድባር የሚቀርቡ ስእለቶች

ስእለት ማለት አንድ ሰው በህይወቱ ውስጥ እንዲሳካለት የሚፈልገውን ነገር የበላይ አካል ለሆነው ፈጣሪው ወይም ከፈጣሪ ጋር ያገናኙኛል ለሚላቸው መናፍስትና ልእለ ሰብ ቃል በመግባት ካደረክልኝ ለክብርህ መገለጫ ይህን ይገኔ ቀርባለሁ በማለት የሚሳሉትና ይዘው የሚቀርቡት ስጦታ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ ያለው ማህበረሰብ እንዲሳካላቸው የሚፈልጉትን ለማግኘት ለዶኒ አድባር ስዕለት ይሳላሉ፡፡ የአከባቢው ማህበረሰብ ለዶኒ አድባር በመሳል ይዘው የሚቀርቡም በትዳር ቆይተው ልጅ ያጡ ልጅ ለማግኘት፣ ጥጃ አላድግ ያላቸው እንዲያድጉላቸው፣የዘሩትን አዝመራ ባርኮ ፍሬ እንዲተፋበትና ልጆቻቸውን ባርኮ በትምህርት ጥሩ ደረጃ እንዲደርሱላቸው በማሰብ የተለያዩ ስእለቶችን ይሳላሉ፡፡

ማህበረሰቡ በጋራ በመሆን ለዶኒ አድባር ስእለት የሚያቀርብ ሲሆን ይህ ስእለት በአከባቢው ላይ አስፈሪ የሆነ የርስ በርስ ጦርነት፣ ድርቅና ወረርሽኝ በሽታ ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ካለ በጋራ በመውጣት በሰላም ሀገራችንን ሰላም አድርግልን አንተ ጠብቅልን ክፉ ነገር አታሳየን በማለት ለዶኒ አድባር በመሳል የሚያቀርቡት ስእለት ነው፡፡ የሚቀርቡ ስእለቶች የሙዳ ቅቤ፣ ገንዘብ (ተቆጣሪ ብር)፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ የኦሮሚያ ባንዲራ፣ ዕጣን፣ሻማ፣ ወጠጤ በግ፣ ኮርማ በሬ፣ አውራ ዶሮ፣ ድፎ ዳቦ፣ ጠላ፣

ጩኮ፣ ቆሪ ገንፎ፣ ቡና፣ እሸት በቆሎና ባቄላ የመሳሰሉ በእለቱ ተዘጋጅተው ለምግብነት የሚውሉና በአድባሩ የሚጨስ እጣን እና በአድባሩ ላይ የሚሰቀል ባንዲራ የመሳሰሉና ገንዘብ በቦታው ይቀርባሉ፡፡ በስእለት መልክ በኢሬቻው ቀን ይቀርባሉ፡፡ በዶኒ አድባር የሚቀርብ ስዕለት አይነትን በተመለከተ ሲገልጹ በቦታው የሚቀርበው ስዕለት አራት አይነት ነው፡፡ በማለት አቶ ደጀን በቀለ (በቀን26/12/2014 ዓ/ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ) እንደሚከተለው ይገልጻሉ

> በመጀመሪያ ደረጃ የሚበራና የሚጨስ እዛው በአድባሩ ስር ሻማውንም በማብራትና ሰንደልና እጣኑን በማጨስ ስዕለታቸውን የሚያቀርቡ ሲሆን ባንዲራ ከመጣ ባንዲራውን እዛው በአድባሩ ላይ እንዲውለበለብ ይሰቅሉታል፡፡ በሁለተኛነት ደረጃ የሚቀርበው ምግብ ሲሆን ካናቱላይ ለአድባሩ በመስጠት የቀረበውን ከመጣው ሰው ጋር በመከፋፈል ይመገባሉ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የገንዘብ ስዕለት የሚገባ ሲሆን ገንዘቡን አንድ ሰውጋ ባደራ በማስቀመጥ ለቀጣይ መስዋዕት የሚሆን ከብት መግዣ ያደርጋሉ፡፡ አራተኛው ስዕለት የከብት ሲሆን መልኩ ለአድባር መስዋዕት የማይሆንና የእነስት ጾታ ያላት ከብት ከሆነች ተሽጦ ለመስዋዕት የሚሆን ከብት ተገዝቶ እንዲቀርብ ይደረጋል በማለት ስርአቱን ይገልጻሉ፡፡

ይህ ሃሳብ የሚያመለክተው ለአድባሩ በስዕለት አማካይነት የሚቀርቡት ስጦታዎች አራት አይነት እንደሆኑና እነሱም ለአድባሩ የሚጨሱ፣ ባንዲራ፣ የከብትና የገንዘብ ስጦታ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

### 5.3.5. ለኢሬቻው ስርአተ ከበራ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ምግብ

የአከባቢው ማህበረሰብ በእድር ገንዘብ በማዋጣት የመስዋእት ከብት በመግዛት ቀርቦ ከታረደ ብኋላ ስጋውን በመክተፍ በበረምጣድ ተጠብሶ ለሁሉም እንዲሸት በማድረግ ለማክበር የመጣውን እንግዳ በተዘጋጀለት ቦታ በማስቀመጥ ሁሉም ይመገባል በተጨማሪም በስእለት የመጣውን ምግብ ባለቤቱ ለመጥው እንግዳ የቻለለትን ያክል በማደል ያበላል፡፡ በዚህ ቦታ ላይ በዋናነት ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ምግብ በአከባቢው ማህበረሰብ በእድር ተዋቶ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን ወጠቴ በግም ሆነ ኮርማ በሬ በማረድ እንጀራና ጠላ በማዋጣት ኢሬቻውን ለማክበር የመጣውን እንግዳ ያበላሉ፡፡ በዚህም እለት በእርድ ላይ ሁሉም እንደ ሃይማኖቱ ሙስሊሙ በሙስሊሙ ቦታ ክርስቲያኑም በክርስቲያኑ ቦታ

በመሆን የስጋ ምግቦችን ይመገባሉ እንጂ ሁሉም ባንድነት ሙስሊሙና ክርስቲያኑ አይመገብም፡፡

በስርአተ ከበራው ወቅት ያከባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት ይዘው የሚመጡ ሲሆን ሽማግሌዎች ከባረኩና እንዲመገቡ ከፈቀዱ ብኋላ በቦታው የተዘጋጀውን ምግብና ከዶኒ አድባር በረከት ለማግኘት አዘጋጅተው ያመጡትን ምግብ ካለበት ቦታ በመጀመር የደረሰለትን ያህል ትልቅ ትንሽ ሴት ወንድ ሳይሉ ለሁሉም ሰው በማደል ለከበራው የመጣ ሁሉም የደረሰውን ምግብ በመቋደስ ስርአተ ከበራውን ያከብራል፡፡

በዚህ በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ ስእለት ተስለው የደረሰላቸው ሰዎችና አዲስ የብላጊ አዝመራ ሲደርስ ከኛ በፊት አድባራችን ይቅመስ በማለት ከእሸት ቦቆሎ ጀምሮ የተለያየ ቤት ያፈራውን ምግብ በቦታው ይዘው በመምጣትና ላድባሩ ሰተው የቀረውን ባባቶች በማስባረክና በማስመረቅ ለመጣው እንግዳ በማከፋፈል አዝመራቸውን ያስባርካሉ፡፡

ፎቶ ግራፍ፡- ሶስት እናቶች በእለቱ ያለውን ምግብ በአይነት በአድባሩ አቅራቢያ በሚገኝ ቤት ሲያቀራርቡ የሚያሳይ



ምንጭ፡-ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘ ምስል

### 5.3.3. የወጣቶች ጨዋታ

በአከባቢው የሚኖሩ ወጣቶች ካባቶች ጋር በመሆን የኢሬቻውን ስርአት ካባቶች በመከተል ከፈጸሙ ብኋላ በዶኒ ሜዳ በመሰባሰብ የኢሬቻውን ክብረ በአል ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ቀኑን በደስታ የሚያሳልፉበትና ከሩቅ ዘመድ የሚገናኙበት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር የተለያዩ ጨዋታዎች ላይ በመሳተፍ ተደስተው ይውላሉ፡፡

በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ወጣቶች ነጻነት አግኝተው ከጓደኞቻቸው ጋር የሚጫወቱበትና የሚቦርቁበት ሲሆን በእለቱም ልጅ አገረደች፣ ወጣት ወንዶችና ፎሌዎች በየግላቸው ክብ በመፍጠር የተለያዩ ወቅቱን የሚመለከቱ ዘፈኖችን በመዝፈን ይጨፍራሉ፡፡

ወጣቶች የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎች ላይ በመወዳደርና አሸናፊውን በመሸለም ቀኑን ተደስተው የሚያሳልፉ ሲሆን በእለቱም የሚተላለፉ ባህላዊ ጫወታዎች የማህበረሰቡን ጥንታዊ ባህልና አኗኗር የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ወጣቶች የሚሳተፉባቸው እነዚህ ባህላዊ ጨዋታዎች የፈረስ ጉግስ (garmaamaa fardaa)፣ የጦር ውርዋሮ (darbanaa ebboo) ገመድ ጉተታ፣ የእሩጫ ውድድርና የገበጣ ጫወታ (Taba sadiqaa) በመጫወት ቀኑን ያሳልፋሉ፡፡ በእለቱ ከነዚህ ወድድሮች መካከል አባቶች ቀለል ባሉ ጨዋታዎች ላይ በመሳተፍ እየተዝናኑ ቀኑን ያሳልፉሉ፡፡ ወጣቶች በሚሳተፉበት ጨወታዎች ላይ አባቶችም በመደባለቅ አብረው የጦር ውርዋሮ ላይ በመወዳደር እለቱን ያሳልፋሉ

- **የልጅ አገረዶች ዘፈን**፡- ልጅ አገረዶች በኢሬቻው ቀን በመሰባሰብ ለዘመን መለወጫ

እንኳን አደረሳችሁ በማለት አበባየሆይ ጨፍረው ባገኙት ገንዘብ ከረሜላ ገዝተው በመከፋፈልና ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ ዘፈኖችን በመዝፈን ረገዳ ይጨፍራሉ፡፡ የልጅ አገረዶችን ጭፈራ አስመልክተው አቶ ከፊያለው ፋንታ ወ/ሮ ከበቡሽ ዘለቀ (በቀን 20/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ ሲገልጹ

> ድሮ ልጅ አገረዶች እድሜያቸው ከ14-24 ያሉ ልጅ አገረዶች በአሁኑ ደግሞ እድሜያቸው ከ6-18 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣት ልጅ አገረዶች ለዘመን መለወጫ አበባየሆይ በመጨፈር በሚያገኙትን ገንዘብ በድሮ የሀር ክር አሁን ደግሞ ከረሜላ በመግዛት የኢሬቻው ቀን የሚከፋፈሉ ሲሆን የደረሳቸውን ከረሜላም ለከንፈር ወዳጃቸው (wadaajja) በማካፈልና ከከንፈር ወዳጃቸውም በምትኩ ሎሚ በመቀበል አብረው በመዝፈንና በመጨፈር ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው በመጫወት እለቱን በነጻነት ተደስተው ያሳልፋሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

ልጅ አገረዶች በእለቱ ከቤተሰብ ቁጥጥር ነጻ ሆነው ከጓደኞቻቸው ጋር በነጻነት የሚጫወቱበት ቀን ነው፡፡ በኢሬቻው ቀን ልጅ አገረዶች የክት ልብሳቸውን በመልበስ በነጻነት ከከንፈር ወዳጃቸውና ከሴት ጓደኞቻቸው ጋር በመጫወት የሚያሳልፉ ሲሆን

በእለቱም ከወላጅ ቁጥጥር ነጻ በመሆን ከወጣት ወንዶች ጋር በመደባለቅ ረደዳ እየጨፈሩ እየተዝናኑ ይውላሉ፡፡

- **የወጣት ወንዶች ጭፈራ፡-** ወጣቶች በእለቱ በተለያዩ ጨዋታዎች ላይ ይሳተፋሉ በመሰባሰብም የተለያዩ ግጥሞችን እየደረደሩና ካዎ እያሉ በዱላቸው በመማከት ይጫወታሉ፡፡ ከሴቶቹም በመደባለቅ የሚወዱትንና የከንፈር ወዳጅ የሆነችውን ልጅ አገረድ ከልጆቹ መካከል ነጥሎ በመውሰድ ለብቻ ይዞ በመቀመጥ የገዛላትን ሎሚ ይሰጣታል እሷም በምትኩ ለከንፈር ወዳጇ እሷም በምትኩ ከኩዮቿ የተከካፈለችውን ከረሜላ በመስጠት ያላትን ፍላጎት ትገልጽለታለች፡፡

በኢሬቻው ክብረ በአል ቀን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በነጻነት የሚጫወቱበት የወደፊት የትዳር አጋራቸውን የሚመርጡበት ቀን ነው፡፡ ወጣቶች ቀኑን ከቤተሰብ ቁጥጥር ነጻ በመሆን የሚጫወቱ ሲሆን በእለቱ አንድን ልጅ አገረድ ያለፍላጎቷ ማስገደድ አይችሉም ያንዱን ከንፈር ወዳጅም ሌላው መንካትም ሆነ የከንፈር ወዳጅ እንድትሆነው ማስገደድ አይቻልም ሴትን ልጅ ያለፍላጎቷ ማስገደድ ባከባቢው ነውርና አጸያፊ ተግባር በመሆኑ የሌላ ሰው ከንፈር ወዳጅ የሆነችን ሴት ማንም ሰው ያለ ፍላጎቷ አያስገድዳትም ይህን ተላልፎ የሚገኝ ሰው ቢኖር ከጓደኞቹ ያጋጨዋል እንዲሁም ከጓደኞቹና መገለል ይደርስብኛል በማለት የአከባቢውን ባህል አክብረውና ጠብቀው ይኖራሉ፡፡

በእለቱ ሁሉም ወጣቶች በነጻነት የተለያዩ ወቅቱን የሚያሳዩ ዘፈኖችን አንድላይ በመሆን የሚጫወቱ ሲሆን በጨዋታውም ሁሉም ዱላቸውን በመጠቀም የሚጫወቱት የዱላ ጨዋታ ነው፡፡

a/ Kaawoo yaa ayyaana waggaa wagaadhan nugahii.(2) **ካዎ** አውዳመት ላመት አመቱ አድርሰን

b/ Kaawoo yaa ayyaana waggaa wagaadhan nugahii.(2) **ካዎ** አውዳመት ላመት አመቱ አድርሰን

a/ Sagaalee sagaalee ድምጽ ድምጽ

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Sagaalee qeenxittii ድምጽ ቄንጥ ነው

b/ Kaawooካዎ

a/ Gadii qabii dhahii ወደታች ይዘህ ምታው

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Akka abbaa keetittii እንዳባትህ

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Tumaalecha coomsi ወጠጤውን አስባ

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Yoqalachuu feetee ለማረድ ከፈለክ

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Sagalee gowwomsi በቃላት አተለው

b/ Kaawooካዎ

a/ Yo taphachuu feetee መጫወት ከፈለክ

b/ Kaawooካዎ

a/ Dargaggeessaa birraa የጸደይ ወጣት

b/ Kaawoo nu wal bira jirraa  ካዎ ይኸው አብረን ነው ያለነው

a/ Yaa fura masqalaa የመስቀል ሳር

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Fura laga keessaa የወን ላይ ሳር

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Furri jabbi nyaatee ሳሩን ጥጆች በሉት

b/ Kaawoo ካዎ

a/ Fira koo maal taatee ዘመዴ ምኖነሃል

b/ Kaawoo yaa ayyaana waggaa waggaadhan nugahi(2) ካዎ አውዳመታችን ላመት አመቱ አድርሰን፡፡ በማለት የሚጫወቱ ሲሆን በእለቱም ቀኑን ያሳልፈሉ፡፡

➢ **የጋራ ጭፈራ፡-** ወጣቶች በየግላቸው ሲጫወቱ ቆይተው በመጨረሻ ወንድና ሴቶቹ በአንድላይ በመደባለቅ ክብ ፈጥረው የተለያየ የፍቅር ዘፈን በመቀባበል እየዘፈኑ ባንድላይ ረገዳ ይጨፍራሉ፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ እለት የተለያዩ ዘፈኖች በጋራ በመሆን በደስታ ሲጫወቱና ሲዝናኑ የሚውሉ ሲሆን በእለቱ አንድላይ በመሆን የሚጫወቷቸው አብዛኞቹ ዘፈኖች ስለ ተቃራኒ ጾታ ፍቅር የሚገልጹ ግጥሞች ሲሆኑ ከዚህም መካከል፡፡

Maasa gurgudda lagarraa erguman qootee galfadhee

አፋፍ ላይ በሰፊው አዝምሬ ባስገባ

Maalan barbadaa kanbira ergumman shagge ko argadhee

ሌላ ምን ፈልጋለሁ የልቤን ሰው ካገኘው

- ✓ Baaqeelli asheete gamaa (2)

  የማዶው ባቄላ ቢያሸት(2)

Siifan dukanaa jaagama seexana naseete namaa

ላንቺ ስል በጨለማ ብዞር ሴጣን አይደለሁም ሰው ነኝ

Haadha mashiinii yaa Daassee shurubbaa bubbeen daddaaqse

የኔዋን ቆንጆ ሹሩባዋን ነፈስ በታተነው

- ✓ Haadha mashiinii yaa lookoo siifan gurgurree jorroo koo

  የኔ ቆንጆ ላንቺ ስል ጆሮውን በሬዬን ሸጥኩት

- ✓ Yaadafaqaa dobbidhaa (2)

  ዶቢ አረፋ ነው(2)

Namni shaggee too tuqee qorichi isaa Uleedha

የኔዋን ቆንጆ የነካ መዳኒቱ ቦንብ ነው

- ✓ dheedanniis yaadheedanii gaarati oll offi burree

  ከጋጡም ይጋጡ ወደላይ ወደ ጋራው ንዳቸው እነቡሬን

beekanis yaa beekanni daaran sibaasa surree

ቢያቁም ይወቁ ሱሬ አለብስሻለሁ

- ✓ shaggiyyoo biraan rafee akkuma raffen dirriirfadhee

  ቆንጆዬጋር ተኝቼ እንደተኛው እግሬን ብዘረጋው

osoon dallawa cabsee akkuma saree sibiriirfadhee

አጥር ዘልዬ እንደ ውሻ እግርሽ ስር የምለማመጥሽ

- ✓ kan roobee addeelleedha finfiine maa rasa rasaa

  አዴሌ ቢዘንብ ፊንፊኔ ለምን ይረሰርሳል

kan waljalate nuhii ormii maa odduusaa nasa nasaa

የተዋደድን እኛ ሌላው ለምን ወሬውን ያሞቃል

- ✓ yaa intala magaallee maqaa kee baruufan dukkana jooreti

  አንቺ ጸይም ልጅ ስምሽን ለማወቅ በጨለማ ዞሬ ነው

osoon sifudhadhee bade warra kee afurtama kiseeti

ይገርሽም ብጠፋ ወላጆችሽን አርባ ሺ ከሼ ነው

afurtmnis biruma ofi kan ormaa hin taatu tiyyumma

አርባ ሺውም ብር ነው የማንም አትሆኚ አንቺ የኔው ነሽ

- ✓ xilaa maaltu qabataa itiyee malee itiyee malee

  ጥላን ማን ይይዛል ከመቤቴ በቀር

addan baana maaf jettaa maaltu addaan nu baasa yoo biyee malee

ለምን እንለያያለን ትያለሽ ማን ያለያየናል ከጨካኙ ከሞት በቀር

- ✓ hadaamitu dheeraadhaa hundarraa hadaamittuu dheeradhaa

  ቁልቋል ነው እረጅም ከሁሉም በላይ

as kootu ni ragannaa hundurraa wadaajjitu seenaa dha

ወዲህ ነይ ረገዳ እን ጨፍር ከሁሉም በላይ የከንፈር ወዳጅ ትዝታ ነው

➢ **የፎልዎች ጭፈራ፡-** ፎሌ ማለት በኦሮሞው ማህበረሰብ ዘንድ እንደወታደር የሚቆጠሩና የአከባቢውን ባህል የሚያስጠብቁ ጠላት በአከባቢው ላይ ችግር እንዳያደርሱ ይከላከላሉ፡፡ ፎሌ በአከባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ክብር ያላቸው ሲሆኑ የአከባቢውን ባህል ተላልፈው ጥፋት ያጠፉ ሰዎች ሲኖሩ ፎሌዎች በራሳቸው ህግ በመቅጣት ስርአቱን የሚያስተካክሉ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ፎሌዎች የጠየቁትን ነገር ያሚሉላቸዋል፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ ፎሌዎች በኢሬቻው ክብረ በአል ላይ በመገኘት የተለያዩ የፎሌ ጫወታዎች ሲጫወቱና በስርአተ ከበራው ላይ ምንም አይነት ችግር እንዳይፈጠር ከመንግስት ጸጥታ ሀላፊዎች ጋር በመቀናጀት ሰላም ያስከብራሉ፡፡ ፎሌዎች በእለቱ በመሰባሰብ የሚጨፍሩት በማህበረሰቡ ውስጥ (sigabaa) ባሏ የሞተባትና የፈታች ሴት ጋ በድብቅ የሚገባ የአከባቢ ነወሪ ካገኙ በመያዝና ስሙን እየጠሩ የስድብ ዘፈን በመዝፈንና የለበሰውን ልብስ ከላዩ አውልቀው በሰው ፊት እርቃኑን እንዲቆምና ሰው እንዲስቅበት ያደርጋሉ፡፡ ሲገባ ተብሎ የተያዘው ሰው ጥፋት ማጥፋቱን ለፎሌዎች በማመን የሚቀጡትን በመቀበል ቃል ገብቶ ፎሌዎች ቀን በመቅጠር ደግሶ በቤቱ ያበላል፡፡ የፎሌ አባል ሆኖ ያጠፋ ሰው እንደጥፋቱ አይነት የተለያየ መቀጮ የሚቀጣ ሲሆን እንደጥፋቱ አይነት ከፍ ሲል ከብት አርዶ ድግስ ደግሶ ፎሌዎችን በቤቱ እንዲያበላ ቀን ቆርጠው ወስነውበት ይሄዳሉ፡፡ ጥፋቱ ቀለል ሲልና በምክር እንዲታለፍ ሲወሰን ነጭ ውሃ ያልነካው አዲስ ጋቢ ገዝቶ ለቡድኑ ይሰጣል ቡድኑም ጋቢውን ቀዳደው በዱላቸው ላይ በማሰር ሆ ይላሉ

በተጨማሪም በአከባቢው ላይ ሌባና አስቸጋሪ ባህሪ ያላቸውን ወጣቶች በዘፈናቸው ውስጥ በመንቀፍ ላከባቢው ህግ ተገዢ በመሆን አደብ ገዝተው እና ባህሉን ጠብቀው እንዲኖ ያደርጋሉ በማለት መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡

### 5.3.5.1. በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚካሄዱ ባህላዊ ውድድሮች

ወጣቶች በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት የተለያዩ የማህበረሰቡን ነባር ባህል የሚያሳዩ ባህላዊ ጨዋታዎች ላይ በመወዳደር ይሳተፋሉ፡፡ በባህላዊ ጨዋታዎቹ ወጣቶች ሲወዳደሩና ሲጫወቱ የሚውሉ ሲሆን የአከባቢው ማህበረሰብ ለዘመናት አዳብሮ ያቆየውን ባህል፣ ወግና ልማድ የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ስርአት አብዛኞቹ ወጣቶች በመሳተፍ እለቱን በደስታ ያሳልፋሉ፡፡ በቀኑም ወጣቶች የሚሳተፉባቸው ባህላዊ ጨዋታዎች ከgamaachu እና siisaayi (2011: 292) ላይ ከገለጸው ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊና ይህን ሃሳብ ያረጋገጠ ጥናት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ጥንታዊ ባህሉን ጠብቆ የኖረና በቀጣይነት በትውልዱ ውስጥ ማንነቱን በባህላዊ ጨዋታዎቹ አማካይነት እያሰረጸ ነባር ባህሉ ሳይበረዝና ሳይጠፋ ቀጣይነት እንዲኖረው ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረካታል፡፡

ስርአተ ከበራው ተካሂዶ ከጠጠናቀቀ ብሁዋላ ሁሉም ባንድነት ውድድራዊ ጨዋታው ወደሚካሄድበት ሜዳ በመሄድ በመወዳደርና በስፖርቱ ላይ የማይወዳደሩ ታዳሚ በመሆን ተወዳዳሪዎችን በማበረታታት ያደምቃሉ፡፡ በእለቱም በወጣቶች መካከል የሚካሄዱ ውድድሮች ፈረስ ጉግስ፣ገመድ ጉተታና ሩጫ ሲሆኑ በእድሜ ሳይወሰን ሁሉም የሚሳተፍባቸው ውድድሮች ደግሞ የገበጣ ጨዋታና ኮርቦ ውርዋሮ ውድድሮች ናቸው፡፡ ልጅ አገረዶች በእለቱ ከጭፈራው መልስ በሩጫ ውድድር ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ሃሳብ Thomas (1997፡300) ፌስቲቫሎች በተለምዶ የውድድራዊ ጫወታ ሥርዓቶችን የሚያካትቱ ሲሆኑ ጨዋታዎቹም በልማድ የሚገለጹና እንደ ውድድር በልዩ ህጎች የተደነገጉ ናቸው፡፡ የሚለውን ሃሳብ የሚያጠናክር ስርአት ነው፡፡

- **የፈረስ ጉግስ ጨዋታ**(Tabaa garmaama fardaa)፡- በምእራፍ አራት አከባቢያዊ ዳራ ላ እንደተጠቀሰው አከባቢው ደጋና ወይና ደባ በመሆኑም በአከባቢው በራካታ የፈረስ እርባታ የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ይህ የፈረስ ውድድር ስርአትም ከዚሁ ጋር ተደጋጋፊነት ይኖረዋል፡፡ በአከባቢው ማህበረሰቡ ፈረስን ለረጅም ዘመናት በቤቱስጥ በማርባት ሲገለገልበት የኖረ ሲሆን ከነዚህ ግልጋሎቶች ውስጥ ለመጓጓዣነት፣

ለጭነት፣ለእርሻና በክፎ ጊዜም የጦር አጋር በማድረግ እንዲሁም ሽሽቶማመለጫ በመሆን የሚገለገልበት የቤት እንሰሳ ነው፡፡ አባቶች በገዳ ስርአት ውስጥ ወጣቶችን ፈረስ ጉግስና የተለያዩ እስፖርቶችን ያሰለጥኑም እንደነበርጨዋታዎች ከgamaachu እና siisaayi (2011) ይገልጻሉ፡፡ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ በዶኒ አድባር ስር በሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚካሄደው የፈረስ ጉግስ ጫወታም ከጥንት ጀምሮ ከሃያት ቅድሚሃያቶቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡

በዚህ በዶኒ ምዳ ላይ በባህላዊ የፈረስ ጉግስ ጨዋታ ላይ ከተለያዩ ወረዳዎች የተውጣጡ ፈረሰኞችና የፈረስ ማህበርተኞች በመሰባሰብ በውድድር የሚሳተፉ ሲሆን ፈረሰኞቹ የተለያየ ቀለም ባለው ክሮች ባጌጡ የፈረስ እቃዎች በመጫን በጉግስ ጨዋታው ላይ ይሳተፋሉ፡፡ የፈረስ ጉግስ ጨዋታው ላይ በመሳተፍ ከብዙ ሰው ጋር በመገናኘት እርስ በርስ ጓደኝነት እንዲመሰርቱና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ እንዲወያዩ መድረክ የሚከፍት ሲሆን በዚሁ ስርአተ ከበራ አማካኝት የተራራቁ ሰዎች እንዲቀራረቡና ስላከባቢያቸው እንዲወያዩ ያደርጋቸዋል፡፡

የፈረስ ጉግስ ጨዋታ የሚካሄደው በዋናነት በፈረስ ማህበርተኞች መካከል ሲሆን ፈረሰኞችን በአስር በአስር እየከፋፈሉ በማወዳደር ከአንድ እስከ ሶስት የወጡትን በመመልመልና አሸናፊዎቹን መልሰው በማወዳደር መጨረሻ ከዐንድ እስከ ሶስት ደረጃ የያዙ አሸናፊ የሆኑትን በመምረጥ የተለያዩ ሽልማቶችን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ይሸልማል፡፡

ፎቶ ግራፍ3 በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ጉግስ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል፡፡



ምንጭ17/01/2014 በስርአተ ከበራው ላይ በረዳት መስከኛ የተነሳ ምስል

➢ **የሩጫ ውድድር** (Dorgomi figicho)፡- እሩጫ የሰው ልጅ የአካል ቅልጥፍናውን በመጠቀም ፈጥኖ ለመድረስ፣ አብሮ ለመያዝና እሮጦ ለማምለጥ የሚጠቀምበት ሲሆን በአከባቢው ማህበረሰብ በኢሬቻው ስርአተ ከደራ ላይ ጥንታዊ ባህሉን ከሚያሳዩ እስፖርቶች መካከል በየጾታቸው በመከፈል እሩጫ ይወዳደራሉ በዚህ ውድድርም ከባህልና ቱሪዝም እንዲሁም ከወጣቶችና እስፖርት ቢሮ የተለያዩ የማበረታቻ ሽልማት ይሸልማሉ፡፡ ማህበረሰቡ እስፖራታዊ ውድድሮቹን እንደ ባህል በመያዝ ከጥንት ጀምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ አሁን ባለበት ደርሷል፡፡ እንደ ባህል በመለመዱም ካከባቢው በርካታ አትሌቶች መውጣት ችለዋል፡፡ በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚሳተፉትን ግለሰቦች እርስ በርስ ከማስተዋወቅም ባለፈ ጓደኝነት እንዲመሰርቱና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ አንድነት እንዲፈጠር እንዲሁም በዚህ ስርአተ ከበራ ላይ በሚተላለፉ እስፖርተኞች ጠንካራ በባህሉ የሚኮራ ትውልድ በማፍራት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ፎቶ ግራፍ አራት፡- በኢሬቻው ስርአት ላይ ልጅ አገረዶች በሩጫ ሲወዳደሩ የሚያሳይ



17/01/2015 በስርአተ ከበራው ወቅት በመስከኛው የተወሰደ ምስል

➢ ***የገመድ ጉተታ ውድድር*** (Wadaroo harekisu)፡- የገመድ ጉተታ እስፖርት ላይ የሚወዳደሩ በርካታ ሰዎች በቡድን እኩል በመከፈል መስመር አበጅተው በገመዱ በመጓተት የተሰመረውን መስመር ያሳለፈ ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡ በዚህ የገመድ ጉተታ ጨዋታ ላይ የሚሳተፉት ወንዶች ብቻ ሲሆኑ ይህ ጨዋታ የአካል ጥንካሬ የሚሰጥ ጨዋታ ነው፡፡

ፎቶግራፍአምስት፡-ወንዶች በገመድ ጉተታ ሲወዳደሩ የሚያሳይ ምስል



ቀን 17/01/2015 በስርአተ ከበራው ላይ በረዳት መስከኛ የተነሳ ምስል

➢ **የኮርቦ ውርዋሮ፡-** ኮርቦ በቀጫጭን እንጨት በክብ ጠቅለው በመስራት በሜዳው ላይ አንድ ሰው ሲያንከባልል ሌላው በያዘው ጦር የምትንከባለለውን ኮርቦ ቀድሞ በጦሩ ወግቶ መጣል ሲሆን በጨዋታው ህግ አሸናፊ የሚሆነው ሰው በወረወረው ጦር ኮርቦዋን ውስጥ በመውጋት የምትከባለለውን ኮርቦ የጣለ ሰው ነው፡፡ ይህ ጫወታ ጥንት አባቶች የቤት እንሳቶቻቸውን ለግጦሽ ይዘው በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የሚያስጨግራቸውን የዱር አራዊት ለመከላከል ጦርን ይጠቀሙ እንደነበርና ይህም ባህል ሆኖ በጫወታ እንደመጣ በርካታ መረጃ አቀባዮች ይጠቅሳሉ፡፡ በጦር ውርዋሮው ጨዋታ ላይ ወንዶች በመወዳደር እንደሌላው ጨዋታ ሁሉ ይዝናኑበታል፡፡ የኮርቦ ውርዋሮ ጨዋታን ወጣቶች ሲጫወቱ ለአላማቸው ትኩረት እንዴት መስጠት እንዳለባቸው የሚማሩበት ነው፡፡ በዚህ ቀን ማህበረሰቡ ባህላዊ ጨዋታዎች ላይ በመሳተፍና በመወዳደር እራሳቸውን በማዝናናት ቀኑን በደስታ የሚያሳልፉበት እና ከጊዜያዊ የስራ ተጽኖ፣ ሃሳብና ከተለያዩ ወቅታዊ ችግሮችን በመርሳት የሚዝናኑባቸውና የሚደሰቱባቸው ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ ስድስት፡- በጦር ኮርቦ ሲወጉ የሚያሳይ ምስል፡፡



17/01/2015 በስርተ ከበራው ላይ በተመራማሪው የተነሳ ምስል

➢ **የገበጣ ጨዋታ** (Taba sadiqaa)፡- የገበጣ ጨወታ መሬት ላይ በሁለት መስመር ስድስት ስድስት ጉድጉድ በአጠቃላይ አስራ ሁለት ጉድጓድ በማጎድዶድና በያንዳዱ ጉድገዋድ ውስጥ አራት አራት ጠጠር በመጨመር በሁለት ሰዎች መካከል የሚካሄድ ጨዋታ ነው፡፡ የገበጣ ጨዋታ የሂሳብ ስሌት የሚጠይቅ ሲሆን ጥንት ቅድሚያ ሀያቶቻችን የቤት እንሰሳቶቻቸውን በማሰማራት በሚውሉበት ቦታ ከሚዝናኑበት ጨዋታ መካከል አንዱ ነው፡፡ የገበጣ ጨዋታ በሂሳብ ስሌት ጎበዝ እና በፍጥነት የማሰብን ክህሎት ይጨምራል፡፡ የገበጣውን ጨዋታ በማስመልከት አቶ ኡሴን ቱሮ (በቀን10/09/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ) ሲገልጹ "የገበጣ ጫወታ ሁለት አይነት ነው፡፡ እሱም ላሜ ወለደችና ኪሳራ የሚባለው ነው፡፡ ላሞቹ እንዲረቡለት የሚፈልግ ላሜ ወለደች ይጫወታል ኪሳራ የታየው ሰው ደግሞ ኪሳራ ይጫወታል በማለት ያብራራሉ" ይህ ሃሳብ የሚያሳየን የገበጣ ጨዋታ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች አብዛኞቹ አርብቶ አደር መሆናቸው ጨዋታቸውንም ከእንሰሳት እርባታ ጋር እንዲሁም እንሰሳትን አርብቶ ከማትረፍና ከመክሰር ጋር ያያይዙታል፡፡ በዚህ ክብረ በአል ላይ በገበጣ ጨዋታ የሚሳተፉ አባቶች ሃሳባቸውን በመሰብሰብ በአንድ ቦታ ተቀምጠው የሚጫወቱት ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው አካላዊ ቅልጥፍና ጥንካሬ የማይፈልግ በአንድ ቦታ ተቀምጠው ስላከባቢያቸው በመወያየት የሚጫወቱት የሚዝናኑበት የማስተዋል ጨዋታ ነው፡፡ በዚህ ጨዋታ ማህበረሰቡ ጥንት የነበረውን ባህልና ያሳለፈውን ያርብቶ አደር ህወት ጥንት የነበረውን የአርብቶ አደር ህይወት የነበረውን ታሪክ ያስታውስበታል፡፡

ፎቶ ግራፍ 7፡-ትላልቅ አባቶች አንድ ቦታ በመቀመጥ ገበጣ ሲጫወቱ የሚያሳይ



ቀን 17/01/2015 በስርአተ ከበራው ላይ በተመራማሪው የተወሰደ ምስል

## 5.4. የድህረ ኢሬቻ ስርአተ ክዋኔ

በኢርቻው ስርአት ላይ የተሰበሰበው ማህበረሰብ በአድባሩ በመሄድ የኢሬቻውን ስርአት በማከናውን የምግብና መጠጥ ስርአት ከተጠናቀቀ ብኋላ ሁሉም የበአሉን ስርአት በተለያዩ ዘፈኖችና ባህላዊ ጫወታዎች በማጀብ ስርአተ ከበረውንአጅበው ያውሉ በዶኒ የጉግስ መጫወቻ ሜዳላይ በመሰባሰብም ከተለያዩ የፈረስ ማህበር ውስጥ የተውጣጡ ፈረሰኞች ወደ ውድድር ሲመጡና ሲወዳደሩ በማበረታታት የዋለው ተሳታፊና ታዳሚው ማህበረሰብ ከውድድሩ ብኋላ ከአንድ እስከ ሶስት ለወጡ ለአሸናፊዎች 5.3 የፈረስ ጉድስ ጫወታ በሚለው ስር እንደተገለጸው የማበረታቻ ሽልማቱ በሁሉም እስፖርቶች ላሸነፉት እንደደረጃቸው የተለያዩ ሽልማቶችን ይሰጣሉ፡፡

በጉግስ ጨዋወታ ላይ ከአንድ እስከ ሶስት የወጡ ተወዳዳሪዎች ብቻ ተመርጠው በደረጃቸው አማካኝት ለሽልማት የሚቀርቡበት ስርአት ነው፡፡ በእለቱም ላሸናፊዎች የሚሰጡ ሽልማቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ትርጉም ያላቸው ናቸው እነዚህም አንደኛ ለወጣው ዋንጫ ወይም የፈረስ ኮርቻ ሲሸለም ሁለተኛ ለወጣው የፈረስ ሉጋምና ሶስተኛ የወጣውን የአለንጋ ሽልማት በመስጠት ተወዳዳሪዎቹን ያበረታቱ በታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አልፎ አልፎ በእለቱ ጋሻና ጦር የመሳሰሉ ሽልማቶችም ይቀርባሉ፡፡ ሽልማት የሚሰጠው አንድ ሰው በተሳተፈበት ውድድርም ሆነ በሰራው ስራ አሸናፊ ወይም የበላይ ሲሆንና ሲያጠናቅቅ በቀጣይነት ጠንክሮ እንዲሰራና ታዳጊዎች የሱን ፈለግ እንዲከተሉ ለማበረታታት ነው፡፡ በዚህ የውድድር ጫወታ ላይ ላሸናፊዎች የሚቀርበውን ሽልማት በተመለከተ የባህልና ቱርዝም ቢሮ የባህል ልማት ሃላፊ የሆኑ ወ/ሮ መርሻ (በቀን 01/18/2014ዓ/ም በተደረገ ቃለመጠይቅ) እንደገለጹት

> በዚህ ባህላዊ የፈረስ ጉግስ ውድድር ላይ የሚሰጡ ሽልማቶች የራሳቸው ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ አንደኛ ለወጣው ዋንጫ ወይም ኮርቻ ይሰጣል፡፡ ዋንጫ ሁልም ያሸናፊዎች መሆኗን ለማሳየት ሲሆን ኮርርቻ ከሆነ ሁሌም ፈረስ መቀመጥ ያምርባሃል ፈረስ አትጣ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ሁለተኛ ለወጣው የፈረስ ሉጋም የሚሸለመው ፈረስህን በሉጋም አትያዘው ልቀቀው አንደኛ የወጣው ላይ ትደርሳለህ የሚል ትርጉም ሲሰጥ ሶስተኛ ለወጣው አለንጋ ይሸለማል ይህ ደግሞ ትርጉሙ ፈረስህን ግረፈው አልገረፍከውም የሚል ትርጉም ያለው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ፎቶ ጋራፍ 8ና 9፡- በጉግሱ ጫወታ አሸናፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲሸለሙ የሚያሳይ





ምንጭ17/01/2014 በስርአተ ከበራው ላይ በረዳት መስከኛ የተነሳ ምስል፡፡

የከበራውን ማብቃት ተከትሎ የተለያዩ ሽልማቶችን ለውድድሩ አሸናፊዎች በመስጠት ና በማጠናቀቅ አባቶች በቦታው በቦታው በመቅረብ መርቀው ስርአቱን ለመዝጋት ይሞክራሉ ወጣቶች አሸናፊዎችን በማጀብ ሆ በማለትና ወቅቱን በተመለከተ እንዲሁም የተለያዩ ፈረሰኛውን እና ፈረሶቻቸውን የሚያወድሱ ዘፈኖች በመዝፈን ይጫወታሉ፡፡ ከነዚህ ዘፈኖች መካከል አንደሚከተለው ጎቤ መስቀላ የሚል ዘፈን በመዝፈን የውድድሩን አሸናፊዎች ያጅባሉ፡፡

a/ Goobee masqalumaa daggalumaa ጎቤ መስቀሉማ ደገሉማ

b/ Goobee ጎቤ

a/ Goobee masqalaa maaltu wallaalaa ጎቤ መስቀላን ማን ያጣዋል

b/ Goobee ጎቤ

a/ Goobe masqala mooti ayyaanaa ጎቤ መስቀል የሁሉም አውዳመት ንጉስ ነው

b/ Goobee ጎቤ

a/ Gooba gotee ya qabatee ጎቤ

b/ Goobee ጎቤ

a/ Gabatee nyaachisa looni ከብቶችህን በገበቴ አብላ

b/ Goobee ጎቤ

a/ Goobee marachisaa akka looni ጎቤ በደስታ እንደሰሳት የሚያስቧርቅ

b/ Goobee ጎቤ

a/ Woo ya goobee masqlumaa daggalumaa ዎ ያ ጎቤ ለመስቀል ረጃጅም ሳር ነው

b/ Daggalumaa masqala mooti ayyannaa ረጃጅም ስር ነው መስቀል ያመትባል ንጉስ ነው

a/ Masqala maaltuu wallaalaa(2) መስቀልን ማን ያጣዋል

b/ Masqala maaltuu wallaalaa(2) መስቀልን ማን ያጣዋ

ከዚህን ብኋላ አባቶች በቦታው በመገኘት የመዝጊያውን ምርቃት በመመረቅና ህዝቡን በሰላም ግቡ በማለት ሁሉም እንድበተን ያደርጋሉ፡፡ የሚመርቁት ምርቃትም

ላመት አመቱ በሰላም ያድርሰን ከፉውን ነገር ያርቅልን፤

እንዲሁ ዘሬ በደስታ እንዳከበርን ከቁጥር ሳያጎለን ለሚመጣው ያድርሰን፤

ሽማግሌዎቹን ጠብቆ ወጣቱን ለቁም ነገር ያብቃልን፤

ታድጊዎቹንም ያሳድግልን አገራችንን ሰላማ ያድርግልን፤

መንግስታችንን በዙፋኑ ያጽናልን

አገራችንን ከከፍ በሽታ፣ ጦርነትና ቸነፈር ጠብቆ ያቆይልን፤

የዶኒ አምላክ ቤታችሁን ይባርክላቹ ሙሉ ያድርግላቸሁ፤

በሰላም እሾህ ሳይወጋችሁ እንቅፋት ሳይመታችሁ በሰላም ለቤታችሁ ያብቃልን በማለትና በመመረቅ ስርአቱን ጨርሰው ያሰናብታሉ ከዚህን ብሁዋላ ሁሉም ወደ የአከባቢው በደስታ በቡድን በመሆን ሆ በማለት ወደቤቱ ያቀናል፡፡

## 5.5. በሎዴሄጦሳ ወረዳ የሚካሄደው የኢሬቻ በአል አከባበር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ፡፡

የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ለተጠኘው ማህበረሰብ ምን አይነት ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ እንዳለው በተለያዩ ርእሶች በመከፋፈል ከዚህ ቀጥሎ ባለው የገለጻ ክፍል በተለያዩ ርዕሶች ስር በሰፊው በትንታኔ ተዳሰው ቀርበዋል፡፡

### 5.5.1.ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የሚካሄደው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በርካታ ሲሆኑ እነዚህም ከማህበረሰቡ የእለት ከእለት ህይወት ጋር ይያያዛሉ ማህበረሰቡ በግብርና ህይወት የሚተዳደር ሲሆን ለግብርና የሚያስፈልገውን አየር ጸባይ ለማግኘት በዶኒ አድባር ስር በመውጣትና ዋቃን በመለመን በአመቱስጥ ሁለት ጊዜ በበልግና በመኸር ወቅቶች የተስተካከለ ዝናብ አግኝተን እናመርታለን በተጨማሪም ከብቶቻችን ቶሎ ቶሎ

ይረቡልናል፣ በድልብና በወተት ምርት የተሻለ ጥቅም ይሰጡናል ብለው በማሰብ በስርአተ ከበራው ወቅት የደም መስዋእት በማቅረብና አድባሩን ሙዳ በማለት ፈጣሪ አከባቢያችንን ጠብቆ በበረከት እንድንኖር ያደርገናል በማለት (አቶ ደዲሹ ቱርኬ እና ወ/ሮ ፀሀይ ሰንበታ በቀን 30/09/2014 በተደረገ በቃለ መጠይቅ) ይገልጻሉ፡፡

በየኣመቱ መስከረም አስራ ሰባት በመውጣት ላለፈው ምስጋና ለወደፊቱም እንዲጠብቃቸው የልመናቸውን በማቅረብ ቸርነቱ ሳይለያቸው መልካም ዝናብ ሰቶ ጤናቸውን ጠብቆ እንዲሁም የቤት እንሰሳቶቻቸው እንዲራቡ ላደረገ ፈጣሪ ምስጋና በማቅረብ እና ለአድባሩ የመስዋእት ከብት ማቅረብ አድባሩን ቅቤ መቀባት(ሙዳ ማለት) የገንዘብ ስጦታ መስጠት እና የመሳሰሉ ስርአቶችን በማከናውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን በዶኒ አማካይነት ፈጣሪ እንዲጠብቅላቸው ይለማመናሉ፡፡ ማህበረሰቡ በኢሬቻው ስርአት ላይ ያለውን አዝመራና ከብት በበረከት ለማስባረክ ካላቸውና ቤት ካፈራው ምግብና መጠጥ ወደ አድባሩ በማምጣት በኢሬቻው ስርአት ላይ ተሳታፊ የሆኑ እንግዶች በማብላት ሃብት ንብረታቸውን ዶኒ በበረከት እንዲባርክላቸው ያደርጋሉ በዚህ የኢሬቻ ስርአት ላይ  የሚቀርቡ የምግብና የመስዋእት አይነቶች በተመለከተም በምእራፍ አምስት ላይ ቀርቦ የተመለከትን ሲሆን ይህንን ስርአት በማካሄዳቸው ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳገኙ ይናገራሉ ይህን በማስመልከት (አቶ በቀለ ታደሰ በ22/09/2014 በተደረገ ቃለ መጠይቅ)

> ዶኒ አድባር የልጆቻችንን ጤና ይጠብቅልናል ከብቶቻችን ቶሎ ቶሎ ይረቡልናል በአመት ውስጥ ሁለት ጊዜ በበልግና በመኸር እናመርታለን ዶኒ ዝናቡን በማዝነብ ከተለያዩ አዝመራን ከሚያጠፉ ተባዮች በመጠበቅ ጥሩ ምርት እንድናገኝ ይረዳናል እንዲሁም ከብቶቻችን እንደልብ ሳር አጊንተው ይረቡልናል ልጆቻችን በጤና ያድጉልናል በዚህም ዶኒ ለኛ ትልቅ ነገር ያደርግልናል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ይህ ሃሳብ የሚያመለክተን ዶኒ አድባር ለአከባቢው ማህበረሰብ የሚሰሩትን እንደሚባርክላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ ከተለያዩ ከአራቱም መአዘን የሚመጡ ሰዎች ከስርአተ ከበራው ቀደም ብለው በቦታው ስለሚደርሱ በከተማ የትራንስፖርትና የሆቴል አገልግሎት በመስጠት በተጨማሪም በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ምግብ ለስላሳ መጠጦች ሻይና ቡና በመሸጥና የምግብ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ለአከባቢው ነዋሪዎች የስራ እድል ይከፍታል፡፡

በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ በሚካሄዱ ባህላዊ ጨዋታዎች ላይ የሚወዳደሩ ተጫዋቾች ውድድሩን ሲያሸንፉ በሚያገኙዋቸው የተለያዩ ሽልማቶች ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከመፍጠርም በተጨማሪ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ላከባቢው ማህበረሰብ ብሎም ለሃገር ማስገኘት የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ለምሳሌ በፈረስ ጉግስ፣ በሩጫና በጦር ውርዋሮ በመሳሰሉ ውድድሮች ካንድ እስከ ሶስት የወጡ ተወዳዳሪዎች በሚያገኙት ሽልማት በመበረታታት እስከ ትልቅ ውድድሮች መሳተፍና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን ማግኘት ያስችላቸዋል እንዲሁም በፈረስ ጉግስ አንደኛ የወጣ ሰው በሚያገኘው ዋንጫ ባከባቢው ከጓደኞቹ ጋር ሆ በማለት ከተለያዩ ግለሰቦች እንዲሁም የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚያገኘው የማበረታቻ ሽልማት ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ ስምንት፡-በኢሬቻው ከበራ ላይ የአከባቢው ወጣቶች የተለያዩ ምግቦችንና ሸቀጦችን ሲሸጡ የሚያሳይ ምስል




ምንጭ፡- ቀን 17/01/2015 በስርአተ ከበራው ላይ በመስከኛው የተነሳ ምስል

### 5.5.2 ማህበራዊ ጠቀሜታ

በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ትልቅ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚፈጥር ነው፡፡ ካራቱም አቅጣጫዎች የሚመጡ የስርአቱ ተካፋዮች እርስ በርስ እንዲተዋወቁ ከማድረግም በተጨማሪ በሀዘንና በደስታ አብረው እንዲያሳልፉ በግብርና ስራ እንዲተጋገዙና ስለአከባቢያቸው እንዲወያዩ በማድረግ ትልቅ ማህበራዊ ጠቀሜታ የሚሰጥና ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚፈጥር ነው፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት ወጣቶች በመተዋወቅ እስከ መተጫጨትና ቤተሰብ እንዲመሰርቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

በስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል እርስ በርስ በመቀራረብና በመደጋገፍ ትልቅ ቤተሰባዊ ቀረቤታ እንዲፈጠርና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ያከባቢው ማህበረሰብ እርስ በርስ እየተደጋገፈ ማህበራዊ ህይወታቸው ቀላል እንዲሆን አድርጎላቸዋል፡፡ ማህበረሰቡ በተለያዩ በማህበራዊ ችግሮቹ ዙሪያ በመገናኘት እንዲወያዩና

ችግሩን ፈተው እንዲያስተካክሉ የሚረዳ ሲሆን እርስ በርስ በማገናኘትና እንዲወያዩም ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚረዳ ነው፡፡ በስርአተ ከበራው ወቅት የፈረስ ጉግስ የሚወዳደሩ ቡድኖች የፈረስ ማህበር ያላቸው ሲሆን በማህበራቸው ውስጥ ያለ አንድ አባል ምንም አይነት ችግር ቢገጥመው እርስ በርስ በመደጋገፍ ለችግሩ ይደርሱለታል፡፡ ይህንንም በማስመልከት አቶ ደጀን በቀለ በቀን 26/12/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ) እንደሚከተለው ሃሳባቸውን ይገልጻሉ

> በፈረስ ጉግስ ጫወታ ላይ የሚሳተፍ ሁሉም ሰው የፈረስ ማህበር ያላቸው ሲሆኑ በጉግስ ጫወታው ወቅት ለሚደርስባቸው ማንኛውም ችግር ሁሉ የፈረስ ማህበሩ ይወጣል ለምሳሌ የፈረስ መሰበር የፈረሰኛው በጉግስ ሰአት ወድቆ መጎዳትም ሆነ በኑሮው ለሚገጥመው ችግር የፈረስ ማህበረተኞቹ በመተጋገዝ ሁሉንም ነገር ያስተካክላሉ፡፡ በዚህ የኢሬቻ ስርአት የተፈጠረ የፈረስ ማህበር ያከባቢውን ማህበረሰብ በማቀራረብና እርስ በርስ በማጣመር ፈረሰኛው በተጻነት እንዲጫወት ያደርጋል፡፡

ይህ ሃሳብ የሚያሳየን በፈረሰኛ ማህበሩስጥ ያሉ ሁሉም ግለሰቦች ባለማዊም ሆነ በአደጋ ጊዜ እርስ በርስ እንደሚተጋገዙ የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ በኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች እርስ በርስ በመገናኘት ከኩዮቻቸው ጋር በነጻነት እንዲጫወቱና ስለ አከባቢያቸው በመወያየት እንዲያውቁ በዚህም ውስጥ በሚፈጠር ጓደኝነት ከኩዮቻቸው እስከጋብቻ በመዝለቅ ትልቅ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

### 5.5.3. ስነ-ልቡናዊ ጠቀሜታ

ተጠኚው ማህበረሰብ ለረጅም ዘመናት በአከባቢው በመኖሩ ከዶኒ አድባር ጋር ትልቅ ስነ-ልቦናዊ ትስስር ያለው ነው፡፡ ማህበረሰቡ በቦታው ትልቅ መንፈሳዊ እምነት ያለው ስለሆነ በቦታው ለዶኒ የሚያስፈልጉትን ስርአቶች እየፈጸምን ባናከብር በድርቅ ይጎዳናል፣ዝናብ በዝቶ የዘራነውን አዝመራ ያጠፋብናል ከብቶቻችን ቶሎ ቶሎ አይራቡልንም ብለው በማሰብ ሁሉም ያከባቢው ማህበረሰብ ባንድነት ችግሩ እንዳይደርስበት በያመቱ ለዶኒ አድባር መስዋእት በማቅረብ ፈጣሪን የሚለምኑበት ቦታ ነው፡፡ ይህንንም አስመልክተው በቡድን ውይይት ወቅት አቶ በቀለ ታደሰ እና አቶ ተሸመ አለሙ (በቀን 10/10/2014ዓ/ም በቡድን ተኮር ውይይት) ላይ ሲገልጹ

ዶኒ እድባር ሁሌም ቢሆን የሚጠብቀን ነው ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ የሚያዘንብልን የምንዘራውን አዝመራ ባርኮ ለፍሬ የሚያቀርብልን ከብቶቻችን ቶሎ ቶሎ እንዲራቡ የሚያደርግልን ልጅ ብናጣ ልጅ የሚሰጠን ያከባቢውን ሰላም የሚጠብቅልን ዶኒ ነው፡፡ እኛም ለዚህ ውለታው አንድ ጊዜ ኢሬጫ ይዘን ምስጋና እናቀርብለታለን፡፡ ስርአቱ ወቅቱን ጠብቆ ሳይከበር ቢቀር ለእርሻ ስራችን የተመጣጠነ አየር አናገኝም፣ ባከባቢው ወረርሽኝ በሽታ ይከሰታል ከብቶቻችን ቶሎ ቶሎ አይራቡልንም፡፡

በማለት ይገልጻሉ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ማህበረሰቡ ከዶኒ አድባር ጋር ትልቅ ስነልቦናዊ ቁርኝት ያለው ሲሆን ለዶኒ አድባር የሚያስፈልገውን ምስጋና ብናቀርብ የሚያስፈልገንን ይሰጠናል ምስጋናውን ባንሰጠው የሚያስፈልገንን ይነሳናል ብለው በማሰብ የሚያምኑ ሲሆን ችግሩ እንዳይደርስባቸው ቀድመው ስርአተ ከበራውን በመፈጸም ለዶኒ አድባር የሚያስፈልገውን መስዋእት ያቀርባሉ፡፡

በዶኒ አድበር ስር የምስጋና ኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚሳተፍ ሰው በሆዱ ቂም ሳይዝ ከሁሉም ሰው ሰላም በመሆን ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ጸብ ካለበት የኢሬቻው ስርአት ከመጀመሩ በፊት መታረቅና ሰላም መፍጠር አለበት ይህ ካልሆነ ስርአቱን ከሚያከብሩ ሰዎች ውስጥ ተለይተው እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በምስጋናው ስርአት ላይ ሁሉም ሰው ንጹህ ሆኖ የሚያከብር ሲሆን ከምርቃት ብኋላ ፍቅር መሆናቸውን ሲገልጹ ሁሉም እጅ ለጅ በመጨባበጥ ይሳሳማሉ፡፡ በዶኒ አድባር ስር ሆዱን ንጹ አድርገው ካልቀረቡ የዶኒ አድባር መንፈስ ጥሎን ይሄዳል፤ በጥፋታችን ይቀጣናል በማለት ያስባሉ በዚህም የተነሳ ሁሉም ሰው ባንድነት ሃይማኖት ብሄር ጾታ ሳይለይ ባንድነት እንደ እህትና ወንድም በመተሳሰብ በንጽህና ስርአቱን ያከብራሉ፡፡

በረከት ለማግኘት ሲሉ እርቅ በመፍጠር የህሊና ጽዳት በማድረጋቸው ትልቅ ስነልቦነዊ ጠቀሜታ ይሰጣቸዋል፡፡ በኢሬቻው ስርአት ላይ ሲሳተፉ ሁሉም ከእኩዮቻቸው ጋር አብረው በመጫወትና በመደሰት ስነልቦናዊ ደስታን የሚያገኙ ሲሆን በተጨማሪም በስፖርታዊ ውድድሮች ላይ በመሳተፍ ባላቸው አካላዊ ቅልጥፍና በራስ መተማመን መንፈስ በማዳበር ትልቅ ስነልቦናዊ ጠቀሜታ ይሰጣቸዋል፡፡

### 5.5.4. ስነ-ምግባራዊ ጠቀሜታ

ማህበረሰቡን በአንድላይ ከማገናኘትና ባህሪ ለባህሪ ከማስተዋወቅም በላይ ወጣቶችም ሆኑ ጎልማሶች የአከባቢውን ባህልና ወግ በማክበር ስርአት ይዘው እንዲኖሩና መልካም ስነ-

ምግባር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው የአከባቢውን ባህል ሲያልፍና ካከባቢው ህግ ሲያፈነግጥ እንዲያስተካክሉ በስርአተ ከበራው እለት ፎሌዎች በዘፈኖቻቸው መካከል በቃል ግጥም መልካሙን በማወደስ አጥፊውን በማኮሰስና በመገሰጽ ለአከባቢው ባህል እንዲገዙና እንዲጠብቁ ያደርጋል፡፡ ባከባቢው የሚታዩ ችግሮችን ከማስተካከልም አንጻር ትልቅ ጥቅም ይሰጣሉ ለምሳሌ አንድ ወጣት ባከባቢው ያልተለመደ ባህሪ ሲያሳይ እንዲስተካከል ማድረግ፣ ባሏ የሞተባት ወይም የፈታች ሴት ጋር የገባን ወንድ ካከባቢው ባህል ውጪ በመሆኑ ገሌ (sigabaa) በማለት በስርአተ ከበራው ላይ በመያዝ የለበሰውን ልብስ በማውለቅ ሁሉም አይቶ እንዲስቅበት በማድረግ ባህሪው እንዲስተካከል ያደርጋሉ በዚህም ስርአት ያከባቢው ማህበረሰብ መልካም ስነምግባር እንዲኖረው በማድረግ ያከባቢውን ባህል ያስጠብቃሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ በማስመልከት አቶ በቀለ ታደሰ በቀን (15/09/2014 በተደረገ ቃለመጠይቅ) ይገልጻሉ ማህበረሰቡ ባህሉን በመጠበቅ እንዲኖር ፎሌዎች በአከባቢው የሚከሰቱ የተለያዩ ችግሮችን በመፍታትና በማስተካከል ላይ ይሳተፋሉ ይህ ማለት አንድ ሰው በቤት ትዳር ያለውም ሆነ ያሌለው ስርአቱን ጠብቆ ወደትዳር ሳይገባ ባሏ የሞተባት ወይም የፈታች ሴትጋ ወይም ባለትዳርን ሴት የሚያመግጥን ወንድ ፎሌዎች ይቀጣሉ፡፡ ጥፋተኛውን ግለሰብ በመያዝና የለበሰውን ልብስ በመቅደድ የተለያዩ ብልግናውን የሚገልጹ ዘፈኖችን ስሙን እየጠሩ በመዝፈን የተሰበሰበው ህዝብ እንዲስቅበት ያደርጋሉ ከዚህ በተጨማሪ በፎሌዎች ህግ ድግስ ደግሶ እንዲያበላ በማድረግ የሚቀጡት ሲሆን ድግሱን አልደግስም ቢል ፎሌዎች ከረገሙም እርግማናቸው ይደርሳል ተብሎ ይፈራል ስለዚህም ላለመረገም ሲሉ የተቀጣውን ቅጣት ይቀበላል፡፡ ጥፋተኛው ሰው የተጣለበትን ቅጣት በቤቱ አንድ ከብት ብቻ ያለው ቢሆን እንኳን ያንኑ አንዱን ከብት ደግሶና አርዶ ፎሌዎችን በቤቱ አብልቶ ጥፋቱን አምኖ ተስተካክሎ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ ማህበረሰቡ የፎሌዎችን ቅጣትና በኢሬቻው ስርአት ላይ መሳቂያ መሆንን በመፍራት ብቻ የተስተካከለ ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ወጣቶች ባከባቢው ጥሩ ስነማግባር ይዘው ከተበላሸ ማንነትና ዘመን ካመጣው አለባበስ ከተለያዩ ሱሶች ተጠብቀው እንዲያድጉ በማድረግ ጥሩና መልካም ስነምግባር ኖሯቸው እንዲያድጉ የአባቶቻቸውን ባህል የሚያስቀጥሉ ወጣቶች እንዲወጡ ከማድረግ አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

# ምእራፍ ስድስት፤ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ዋና ዋና ሀሳቦች ጠቅለል ተደርገው ባጭሩ የቀረቡበት፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች የተገለጹበት እና ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ወደፊት የሚመለከተው አካል ቢያስተካክላቸው ጥሩ ነው የተባሉ ይሁንታዎች አካቶ የያዘ ክፍል ነው፡፡

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት “የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ” በሚል ርዕስ የተካሄደ ሲሆን ይህንንም ርእሰ ጉዳይ ከዳር ለማድረስ ሲባል በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ ውስጥ የሚከበረውን የኢሬቻ በአል አከባበር መመርመርና ማሳየት የሚል አብይ አላማ ይዞ የተነሳነው፡፡ በዚህ ስርም የኢሬቻውን ክዋኔ መግለጽ፤የክብረ በዓሉን ፋይዳዎች ማብራራት፤ የኢሬቻውን የተለየ ባህሪ ማሳወቅ እና በክብረ በአሉ ወቅት የሚታዩ ትእምርቶችን መፈከር የሚሉ ዋናውን አላማ የሚያጎላምሱ ዝርዝር አላማዎች ተካተውበታል፡፡

1ኛ.ከርእርሰ ጉዳይ አንጻር ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ሁለት ሀሳቦች ሲሆኑ እነዚህም አንደኛው በዶኒ አድባር ስር የሚከበረው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ የአካባቢውን ማህበረሰብ አገር በቀል እውቀት፣ እሴት እና አጠቃላይ የማህበረሰቡ ልማድ በስርአተ ከበራው ክዋኔ እንዴት ይገለጻል የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በጥናቱ መመለስና ማመላከት ካለኝ ጽኑ ፍላጎት በመነሳት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የምስጋናው ኢሬቻ ባህላዊ ስርአቱን ሳይለቅ የተለያየ ብሄርና ሃይማኖት ያላቸው ቡድኖች ከተለያየ አከባቢ ተሰባስበው የሚከውኑበት እንዲሁም አብዛኛው ማህበረሰብ ከስርአቱ ጋር ተያይዘው የሚከውኑትን ባህላዊ የፈረስ ጉግስ፣ ሩጫ፣ በጦር ኮርቦ መውጋት (eboon gengo waraanu) የገበጣ ጨዋታና የገመድ ጉተታ የመሳሰሉ ጨዋታዎችን በጉጉት መጠበቃቸውን ስረዳ ይህ ስርአት የማህበረሰቡን የቆየ ባህል ለማወቅ የሚያስችል ሆኖ በማግኘቴ ለማጥናት የወሰንኩ፡፡

2ኛ.በኢሬቻ ስርአተ ከበራ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በማይበት ጊዜ በሁለት ወቅቶች (በጸደይ ወቅት/በውሃማ ስፍራዎች/ እና በበልግ ወቅት/ በጋራ) የሚከወኑ ጥናቶች በማየቴና ከእነዚህ ውጪ የእኔ ጥናት በአድባር ስር የሚከበር መሆኑን ማመላከት የሚሉት ሲሆኑ በዚህ ዙሪያ ያለውን ያመለካከት ክፍተት በተወሰነ መልኩ ያጠባል ብዬ በማሰብ ለማጥናት አነሳስቶኛል፡፡

ይህ ጥናት በወረዳው ካሉ 22 ቀበሌዎች መካከል በቱሉ የንቦ፣ በፉርሳ፣ በጉዴለቻ እና በወረዳው ዋና ከተማ በሁሩታ ላይ ተወስኖ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከካልአይና ከቀዳማይ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን ከቀዳማይ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ ናቸው፡፡ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በአላማ ተኮርና በጠቋሚ ናሙና ስልት ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ሆኖ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በትረካዊ ስልት ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ እንዲሁም ከመረጃ አቀባዎች የተሰበሰበ መረጃ በወገን በወገናቸው በማደራጀት ትንተና የተካሄደ ሲሆን፤ ክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ (performance theory)፣ ስነ ትእምርት ንድፈ ሃሳብ (Semiotics theory)እና በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functionalism theory) አማካኝነት እንደመረጃው ሁኔታ ገላጭ በሆነ መልኩ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

- በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት ዶኒ ማለት አቃፊ፣ አሰባሳቢ፣ ከማእበል የሚያሻግር መርከብ ማለት ነው፡፡ ጥንት ማህበረሰቡ በዚህ ቦታ በመውጣትና ክብ በመቀመጥ ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ (doyirii ta`ani waqa kadhatu) በማለት የገለጹ ሲሆን ከዚህም ቃል በመነሳት ዶኒ(ዶሪ) የሚል ስያሜ እንደያዘ ሲነገር ሁለተኛው ቦታው በድንጋይ የተከበበና የመርከብ ቅርጽ የያዘ በመሆኑ ከቦታው በመነሳት ዶኒ የሚል ስያሜ እንደሰጡት ተረጋግጧል፡፡
- በዚህ በሎዴ ሄጦሳ ወረዳ በዶኒ አድባር ስር የሚካሄደው የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ ባከባቢው የሚገኘው ማህበረሰብ ባጠቃላይ ብሄር ሃይማኖትና ጾታ ሳይለይ ባንድነት በአመት አንድ ጊዜ በአድባሩ ስር ወተው የምስጋና ኢሬቻ ስርአት እርጥብ ሰርዶ ሳር እና አደይ አበባ ከመንገዳቸው ነቅለው በአድባሩ ስር በሀገር ሽማግልዎች፣ ባባቶችና በእናቶች መሪነት በአድባሩ ስር በየአንዳድ ምትር ርቀት ላይ በአምት ቦታ በማስቀመጥ ኢሬቻውን እንደሚፈጽሙና አምስት ቦታ ማስቀመጣቸው አምስቱን የገዳ ክፍል የሚያሳይ እንደሆነ በተደረገው ጥናት ተረጋግጡዋል፡፡
- ለኢሬቻው ስርአተ ከበራ ያከባቢው ማህበረሰብ ሁሉም እንደ ማህበራዊ ደረጃው ቅድመ ዝግጅት እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን በዚህ ዝግጅት ወጣት ወንዶች ከዋዜማው ቀደም ብለው ሰንጋ ፈረሶቻቸውን ለጉግስ እንደሚያዘጋጁና የፈረስ እቃዎቻቸውን የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮች እንደሚያስጌጡ እንዲሁም ለጉግስ መጫወቻ የሚሆን ጋሻ ሲያዘጋጁ በጦር ምትክ ቀጫጭን እርጥብ ዱላ ቆርጠው እንደሚያዘጋጁ የተረጋገጠ ሲሆን ፎሌዎችም በዋዜማው ዳቤያቸውን በማጠብና ቅባት በመቀባት ዱላቸውን

በመወልወል ለስርአቱ ይዘጋጃሉ፡፡ በክብረ በአሉ ዋዜማ ልጅ አገረዶች በበኩላቸው ለእንቁጣጣሽ አበባ አየሾይ ጨፍረው በሚያገኙት ገንዘብ በድሮው ጊዜ የሃር ክር በአሁኑ ከረሜላ በመግዛትና በዋዜማውም ከአንድ ቀን ቀደም ብለው ልብሶቻቸውን በማጠብ፣ ፀጉራቸውን በመሰራትና በቤቱስጥ በተለያዩ ለበአሉ በሚዘጋጁ የምግብ ዝግጅት ላይ ሲሳተፉ እናቶችም በእለቱ ጠዋት ለፌጫሳና ለኢሬቻው በአል የሚሆን ምግብ በማዘጋጀትና ወተት በመናጥ ለሙዳ የሚሆን ቅቤ ሲያዘጋጁ አባወራዎችም በበኩላቸው በክብረ በአሉ ቀን ለሚታረድ የመስዋእት ከብት በረጅም ጊዜ ገንዘብ በማዋጣት ይገዛሉ በተጨማሪም በአድባሩ እና በፈረስ የፈረስ ጉግስ መጫወቻ ቦታዎች የማጽዳትና ለእንግዳ ማረፊያ ቦታ እንደሚያዘጋጁ በጥናቱ ሂደት ተረጋግጠዋል፡፡

- በስርአተ ከበራው ወቅት እናቶች ቅቤ በማምጣት አድባሩን ሙዳ የሚሉ ሲሆን ይህም ዋቃ የሰጠኸንን እርጥበት (ወዝ) አታሳጣን ላሞቻችን ይራቡልን ጥጆቻቸው ይደጉ ፤ልጆቻችን ትልቅ ቦታ ይድረሱልን በማልት አድባሩን ሙዳ እንደሚሉና በአድባሩ ስር የተለያየ ጥሩ ሽታ ያላቸውን እጣንና ሰንድል እንደሚያጨሱ በተደረገው ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በጊዜ አሬቻው ስርአተ ከበራውን በምርቃት የሚከፍቱ አባቶች መጀመሪያ ስርአተ ከበራውን ያስጀመሩ አባቶች ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት የነዚህ አባቶች ዝርያ የሆኑ በሃይማኖት ተጽኖ እና ካከባቢው በመልቀቃቸው ስርአቱን እንደ አከባቢው ባህል መሰረት የገላን፣ የገላን ኮራ ጂዳና ጉለሌ ጎሳ የሆኑ ሽማግልዎች በምርቃት እንደሚያስጀምሩ በጥናቱ መሰረት ታውቋል፡፡
- በዚህ በዶኒ አድባር በሚከበር የኢሬቻ ስርአተ ከበራ ላይ የሚካሄዱ ባህላዊ ዘፈኖች ወጣት ወንዶች፣ ልጅ አገረዶችና ፎሌዎች በቡድናቸውና በአንድ ላይ በመሰባሰብ እንደሚጫወቱ ተረጋግጠዋል፡፡ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ የሚካሄዱ ባህላዊ እስፖርት ጫወታዎች ፈረስ ጉግስ፣የጦር ርዋሮ፣ ሩጫ፣ ገመድ ጉተታና የገበጣ ጫወታ ሲሆኑ እነዚህ ጫወታዎች የማህበረሰቡን ጥንታዊ አመጣጥና ማንነት የሚያሳዩ እንደሆኑ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ወቅት በዶኒ አድባር ስር ለመስዋዕት የሚቀርብ ከብት መልክ ነጭ መልክ ያለው ተባእት ጾታ ያለው ነው፡፡ ነጭ ከብት ከጠፋ እንዳማራጭ ዳለቻ ከብት ሲመረጥ ባጋጣሚ ዳለቻም ካልተገኘ ቡሌ ከብት እንደ ወቅቱ እና እንደተገኘው መዋጮ ኮርማ በሬም ሆነ ወጠጤ በግ ይቀርባል፡፡ የኢሬቻው ስርአት የሚካሄድበት ቀኑ

እሮብ ወይም አርብ ከሆነ በእለ· ቀኑን ሳይለቅ ተከብሮ የእርዱ ስርአት በማግስት እንደሚካሄድ በቃል መጠይቅ ሲረጋገጥ ለአድባሩም የሚቀርብ የመስወእት ከብት መልክ የሚያሳየው ብርሃንን ወይም ከጭጋጋማው ክረምት ወደ ብርሃናማው ወቅት በሰላም አሸጋግረን የሚል ተስፋ ያሳያል በተጨማሪም ለአድባር የሚቀርብ የመስዋእት ከብት መልክ አድባር የሚወደው መልክ እንደሆነም በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

- ❖ በኢሬቻው ስርአተ ከበራ ላይ በሚካሄዱ ባህላዊ የእስፖርት ጫወታዎች ላይ አሸናፊ ለሆኑ ተወዳዳዎች ያከባቢውን ባህል ባማከለ መልኩ የተለያየ ሽልማት ይሰጣሉ እነዚህም ሽልማቶች ከአመት አመት ሊለያዩ ይችላሉ በሩጫ ላሸነፉ ወንዶች ፎጣ፣ ለሴቶቹ ሻርፕ፣ በጦር ውርዋሮው ላሸነፈው ጦር እና በፈረስ ጉግስ ጫወታው አሸናፊ ለሆኑ ተወዳዳሪዎች ሽልማት ይሰጣል ይህም ሽልማት አንደኛ ለወጣው ዋንጫ ወይም የፈረስ ኮርቻ ሲሸለም ሁለተኛ ለወጣው የፈረስ ሉጋምና ሶስተኛ ለወጣው አለንጋ የሚሸልሙ ሲሆን አልፎ አልፎ በእለቱ ጋሻና ጦር የመሳሰሉ ሽልማቶችም እንደሚቀርቡ በተደረገው ጥናት ተረጋግጡዋል፡፡
- ❖ ይህ በሎዴሄጦሳ ወረዳ የሚካሄድ የኢሬቻ ስርአተ ከበራ በአመት አንድ ጊዜ መስከረም አስራ ሰባት የሚከበር ሲሆን በዚህም ስርአተ ከበራ ያከባቢው ማህበረሰብ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊና ስነ ማግባራዊ ጠቀሜታ እንዳለው የታወቀ ሲሆን በተጨማሪም ማህበራዊ አንድነትን ከመፍጠርና ህዝቡን በማዋሓድ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 6.2. የይሁንታ ሃሳብ

- ❖ በአሁን ወቅት የእስልምና የክርስትና ሃይማኖት በመስፋፋቱ የኢሬቻው ስርአተ ከበራ እንዲዳከምና ሁሉም ማህበረሰብ በሃይማኖቱ ተጽእኖ ስርአቱን ከማክበር እየታቀበ በመሆኑ ባህልና ቱሪዝም ይህ ስርአተ ከበራ ከምንም አይነት ሃይማኖት ጋር እንደማይገናኝ ለማህበረሰቡ በማስረዳት ተከታዩ ትውልድ ጥንታዊ ባህሉን እንዲያስቀጥል ቢያደርጉና ስርአተ ከበራው ይዘቱን ሳይለቅ በቀጣይነት ቢከበር መልካም ነው፡፡
- ❖ የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ከተካሄደ ብኋላ ሁሉም ታዳሚ ባንድነት ወደ ባህላዊ እስፖርቶች መጫወቻ ሜዳ በመሄድ ስርአቱን በባህላዊ ጫወታ በማጀብ የሚያከናውኑ እንደ ሆነ ይታወቃል ነገር ግን ይህን ቅደም ተከተል በመተው አንዳንድ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች ከኢሬቻው ስርአት ይልቅ ለባህላዊ

ጫወታዎቹ ብቻ ትኩረት በመስጠት  አድባሩ ስር የሚከወነውን ስርአት ከመከናወኑ በፊት ቀጥታ ወደ ባህላዊ ጫወታው መግባት የስርአተ ከበራው ገጽታ ስለሚቀየር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ሳይቆራረጥ ቢከናወን ባህሉ ሳይበረዝ እና ይዘቱን ሳይለቅ ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

- በአድበሩና በስፖርት መጫወቻ ሜዳዎቹ ዙሪያ ሰፍሮ የሚገኘው ያከባቢው ማህበረሰብ ሜዳውን በእርሻና በቤት መስሪያ እያጣበቡ ስለሆነ ይህን የሚመለከተው አካል ለሜዳውም ሆነ ለአድባሩ ተከልሎ በባህልና ቱሪዝም ስም ቢቀመጥ፡፡
- ለኢሬቻው ቀን የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግብና መጠጥ እየቀሩ በዘመናዊ እየተተኩ መምጣታቸው የባህሉን ይዘት ስለሚቀይረው እንደድሮው ጠላና ቀሪቦ ቢዘጋጅና በስርአቱ ወቅት ቢቀርብ የተሻለ ነው፡፡
- እናቶች ጥንታዊ የባህል አልባሳታቸውን በመተው ወደ ዘመናዊ አልባሳት በመቀየሩ የአለባበስ ስርአታቸው ባህሉን በተከተለ መልኩ ቢቀጥል እንዲሁም በኢሬቻው ስርአት ላይ የሚያስፈልጉ ቁሶች እንደ ማለቢያ፣ ጋዲ፣ ጨሌ እና የመሳሰሉ ቁሶችን እንደ ቀድሞው በስርአተ ከበራው ላይ ቢገለገሉባቸው ስርአቱ ይዘቱን ሳይለቅ እንዲቀጥል ይረዳዋል፡፡

# ዋቢዎች


ሞገስ ሚካኤል፡፡ (2012፡፡ "ቁሳዊ ባህል፣ሥነ ማህዳርና ማንነት በዘጌ ማህበረሰብ" የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሉዛምና የኮሚዩኒኬሽን ኮላጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሐፌና ለፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሙዋያ የቀረበ አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ (20011)፡፡ "የፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ" አዲስ አበባ አረቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

----------------- ::( 2010)፡፡ ዓ.ም "በባሌ ዜን ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የ‹ሙዳ› ስርዓተ ከበራ እና መንፈሳዊ ጉዜ" የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሉዛምና የኮ ዩኒኬሽን ኮላጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሐፌና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ለዶክተሬት ዲግሪ የቀረበ አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አስቻለው ተስፋዬ (2014 ዓ.ም)፡- ‹‹የጉዲት አምልኳዊ ስርዓተ-ከበራ በመሐል ሳይንት ወረዳ ማህበረሰብ ማሳያነት››ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የፎክሎር (ባሕል ጥናት)ትምህርት ክፍል የቅድመ ምረቃ መርሓ ግብር ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ኮማንደር መሃመድ፡፡ (2005 ዓ.ም)፡፡ "የበሪ ሃገረሰባዊ ዕምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ"፡፡ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ

አለም እሸቱ፡፡ (2001) ፡፡ "የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ"፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (1948) ፡፡ "መጽሐፈ፡ሰዋስው፡ወግስ፡ወመዝገበ፡ቃላት፡ሐዲስ"፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2006) ፡፡ "የምርምር መሰረታዊ መረሆዎችና አተገባበር"፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

---------፡፡ (2011) ፡፡ "የምርምር መሰረታዊ መረሆዎችና አተገባበር"፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ዘሪሁን አስፋው: (1992) ፡፡ "የስነጽጉፍ መሰረታዊያን"፡፡አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና የፎክሎር ትምህርት ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (1962) ፡፡ "አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት"፡፡ አዱስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ፀዳለ ታደሰ: (2007) "በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች" የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና የፎክሎር ትምህርት ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ “የስነ ቃል መምሪያ”፡፡አዲስ አበባ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Lond.on EC4P4EE

Bell, C. (1992). Ritual Perspectives and Dimensions Oxford University Press Inc

______ (1997). Ritual theory, Ritual Practice Oxford University Press, Inc

Celene Reynolds1 and Emily Erikson (2017) Socius: Sociological Research for ADynamic World Volume 3: 1 14 Reprints and permissions: sagepub.com /journals per missions.nav DOI: 10.1177/2378023117710881 Rd. ssagepub Com

Daamxoo Banti (2011) Qaaccesa sirna raaawwannaa Ayyaana Irreecha .Awaash Mlkaa qunxurree kolleejji namoomaa Qo'annoo xfaanii, jornaalizimii Fi qunnamtiitti muummee afaan oromoo, OG brruu fi fookloorii Yuniivarsiitii Addis ababaa.

Dundes, A. (2007). The Meaning of Folklore Logan: Utah State University Press

Dorson, M. R. (1972). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago press

Frankn magill (1995).International encyclopedia of sociology university of Arizona Puplished in the u.k andus voll two

Frank A.Salamone, (2oo4), Editor Encyclopedia of religious rites, rituals, and Festivals routledg enew York London

Finnegan, R. (1992). Oral Traditions and the Verbal Arts a Quide To

Gladys Ifeoma Udechukwu (2019) SIGNIFICANCE AND USE OF CULTURAL SYMBOLS IN THE CONTEMPORARY AFRICAN SOCIETY: IGBO SYMBOLS AS A PARADIGM Mgbakoigba, Department of Igbo, African and Asian Studies Nnamdi Azikiwe University, Awka Journal Of African Studies.Vol 8, No. 1 gladudechukwu@gmail.com

Research Practices Published by Routledge, New Fetter Lane,

Goldstain, Kenneth (1964) a Guide to Fieldworkers in Folklore the American Folklore Society, Folklore Association.

Hyung, D., L. (2009). Comparative Study of the Ritual aspects Of Western and Asian Performance a thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Fine Arts at Virginia

(Unpublished) Common Wealth University
Joel Robbins (2001) Current Anthropology, Vol. 42, No. 5, pp. 591-614
Published By: The University of Chicago Press on behalf of
Wenner-Gren Foundation for Anthropological Research Stable URL:
https://www.jstor.org/stable/10.1086/32255
Matt Rossano (2015) the Evolutionary Emergence of Costly
Natash Mack (2005) Qualitative Research Methods: A DATA COLLECTOR'S
FIELD GUIDE Research Triangle Park, North Carolina Cornell
University Press Ithaca, New York
………….. (2005) Qualitative Research Methods in Public Relations and
Marketing Communications London and New York Christine Daymon
And Immy Holloway This edition published in the Taylor and Francis
E-Library 27709 USA http://www.fhi.org E-mail: publications@fhi.org
Nicholas, M. H. J., Schroeder, J. L., R, D., X. and Michael I. (2017) The
Psychology of Rituals: An Integrative Review and Process Based
Framework by the Society for Personality and Social Psychology Inc
Rappaport, Roy A. (1992) Folklore, Cultural Performances, and Popular
Inc Hatboro, Pennsylvania; Republished by Gale Research Company,
Book Tower, Detroit
Nilgun Aksan Mufit Aydına, Sumeyra Demirbuken (2009) Symbolic interaction
TheoryProcedia Social and Behavioral Sciences 1 (2009) 902—904
www.sciencedirect.com E-mail address: aksannilgun@yahoo.com.World
Rachel E. Watson-Jones and Cristine H. Legare (2016), the Social Functions of
GroupRituals Current Directions in Psychological Science, Vol. 25, No
1(Pp.42-46 Sage Publications, Inc. on behalf of Association for
Psychological Science Stable URL: https://www.jstor.org/stable/44318913
Roger Sapsford and Victor Jupp (2006) DATACOLLECTION AND ANALYSIS
SAGE Publications London Thousand Oaks New DelhiSecond edition
Samuel leykune (2014) .jornal of science and sustainable development (jssd)
Ambo university collej of social sciences and humanities
Department of English and Literature Adis Ababa University
Serawit Bekele (2018) Reading Prayers as Political Texts: Reflections

On Irreecha Ritual in Ethiopia POLITICS, RELIGION & IDEOLOGY 2018, VOL19 NO 3, 354—370 https://doi.org/10.1080/21567689.2018.1510393

Sims, Marth, and Marthine Stephens (2005).LivingFolklore: An Introduction of The Study of People and Their Tradition, State University press,

__________ (2011) Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their tradition Utah State university press. 2nd Edition

Thomas A. Green (Ed). (1997) Folklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art; Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England

----------- (2o11) Folklore an encyclopedia of custom`s, taes, music, andart Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England Second Edition

Tiruneh Rebuma (2o19) the Cultural Significance of Irreechaa at Malkaa Ateetee School of Graduate Studies in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Social Anthropology Addis Ababa University

Viktor Turner (1966) theritual process Structure and Anti Structure

----------- (2011) Blackwell Publishing on behalf of the American Anthropological AssociationStable URL: http://www.jstor.org/stable/66294916

Waktol Hailu (2019) Social event and environment: Inpact assessment Management practices Among the maccaa Oromo of and It`s Western Ethiopia

# አባሪ

በዚህ ስር ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃዎችን የሰጡኝ በቃለ-መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የተሳተፉ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ንዑሳን መረጃ አቀባዮች ግላዊ ዳራ እና ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች የቀረቡበትና በስርአተ ከበራው ላይ በመቅረጸ ምስል የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

**አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ግላዊ ዳራ**

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | ስራ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተሾመ በቀለ | ወንድ | 65 | ገበሬ | ቱሉ የንቦ |
| 2 | ጣፋ ቱፋ | ወንድ | 70 | ነጋዴ | ሁሩታ ከተማ |
| 3 | ዲንቁ ሰቦቃ | ወንድ | 81 | ገበሬ | ቱሉ የንቦ |
| 4 | ከተማ በቀለ | ወንድ | 24 | ስራ ፈላጊ | ቱሉ የንቦ |
| 5 | በቀለ ታደሰ | ወንድ | 48 | ገበሬ | ፉርሳ |
| 6 | ፀሀይ ሰንበታ | ሴት | 53 | የቤት እመቤት | ጉዴልቻ |
| 7 | ከበቡሽ ዘለቀ | ሴት | 51 | የቤት እመቤት | ዶዴ |
| 8 | ከፊያለው ፋንታ | ወንድ | 60 | ገበሬ | ዶዴ |
| 9 | ደጀን በቀለ | ወንድ | 40 | የመንግስት ሰራተኛ | ሁሩታ |
| 10 | ደምሴ በሂ | ወንድ | 46 | ገበሬ | ቱሉ የንቦ |

ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘሩትና ግላዊ ዳራቸው የተጠቀሱት በመረጃ ስብሰባው ወቅት በዋናነት የተሳተፉና ቁልፍ መረጃ ያቀበሉ ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | ስራ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ደዲሼ ቱርኬ | ወንድ | 67 | ገበሬ | የንቦ |
| 12 | ተሾመ አለሙ | ወንድ | 44 | ገበሬ | የንቦ |
| 13 | ወ/ሪት አበባ ንጉሴ | ሴት | 22 | የመንግስት ስራ | ፉርሳ |
| 14 | አበራ ደምሴ | ወንድ | 46 | ነጋዴ | ፉርሳ |
| 15 | ጀማል ታጁ | ወንድ | 40 | ገበሬ | ጉድልቻ |
| 16 | ንጉሴ ተሊላ | ወንድ | 61 | ገበሬ | ሁሩታ |
| 17 | አብዶ ሮባ | ወንድ | 48 | ገበሬ | ፉርሳ |
| 18 | ተሾመ ካሳ | ወንድ | 40 | መምህር | ሁሩታ |

**አባሪ ሁለት ፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች**

1. የኢሬቻ ማለት ምን ማለት ነው ስርአቱን በዶኒ አድባር ስር መጀመሪያ ያስጀመረው ማነው?

2. ዶኒ የማለት ምን ማለት ነው ከምን ተነስተው ስያሜውን አወጡለት?

3. በዶኒ አድባር ስር የኢሬቻ ስርአት መከበር የጀመረው መቼ ነው መነሻ ሃሳቡስ ምንድነው?

4. በዚህ በኢሬቻ ክብረ በአል ላይ የሚሳተፉት እነማን ናቸው?

5. በኢሬቻው ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ባህላዊ ጫወታና ውድድሮች ምንምን ናቸው?

6. ስርአተ ከበራው ባመት ስንት ጊዜ ይከበራል?

7. የኢሬቻው ስርአተ ከበራ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ እንዴት ይከበራል?

አባሪ ሶስት፡- በስርአተ ከበራውና በመረጃ ማሰባሰቢያ ወቅት የተነሱ ምስሎች፡፡





አባሪ 3 ፎቶ 1ና2፡- አጥኝው በቃለመጠይቅ መረጃ ሲሰበስብ እና ቡድን ተኮር ውይይት ወቅት መረጃ ሲሰበስብ (20/09/2014 ዓ/ም እና 8/10/2014ዓ/ም) የተካሄደ፡፡



አባሪ 3 ፎቶ 3፡- ልጅ አገረዶች ለዘመን መለወጫ አበባ የሾይ ጨፍረው ባገኙት ገንዘብ የገዙትን ከረሜላ ሲከፋፈሉ (01/17/2015) አጥኚው እየተከታተለ በረዳት መስከኛ የተወሰደ ምስል፡፡





አባሪ 3 ፎቶ 4 ና 5፡- አጥኝው በኢሬቻው ስርአት ላይ እናቶች ማለቢያ፣ ሲንቄና እርጥብ ሳር ባንድነት ይዘው የሚያሳይ ምስል እና ወጣቶች ፈረሶቻቸውን አጊጠው በጋሻ እና ጦር ይዘው የሚያሳይ ፎቶ 01/17/2012 ከባህልና ቱሪዝም የተነኘ ምስል፡፡





አባሪ 3 ፎቶ6፡-ግለሰቡ በአድባሩ ስር ሰንደል ሲያጨስና አድባሩ የተቀባውን የሙዳ ቅቤ ምስል የሚያሳይ በቀ (በቀን 01/17/2015) በመስከኛው የተወሰደ ምስል፡፡



አባሪ 3 ፎቶ 7፡- በፈረስ ጉግስ አሸናፊ የሆነውን ፈረሱንና ፈረሰኛውን በማወደስ ሲዘፍኑ የሚያሳይ ምስል በቀን (17/01/2015) በመስከኛው የተወሰደ ምስል



አባሪ 3 ፎቶ 8፡- ፈረስ ጉግስ ተወዳዳሪዎእ የፈረስ መጫኛ እቃዎቻቸውን አጊጠው ጋሻም እንደያዙ የሚያሳይ፡፡





አባሪ 3 ፎቶ9ና10፡- በጉድስ ውድድር አሸናፊ ለሆኑ እስፖርተኞች ሽልማት ሲሰጥና በስርአተ ከበራው ወቅት እንግዶች ሲጋበዙ የሚያሳይ ምስል፡፡

## አባሪ 4. ጥናቱ በቦታው መከናወኑን የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡

ቁጥር 0081/22-03
ቀን 2/2/2016

ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩመኒቲስ ፋኩልቲ (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

ባሕር ዳር- ኢትዮጵያ

ጉዳዩ፡- ተማሪ ስንታየሁ ታደሰ ጥናታዊ ፅሁፉን እኛ ወረዳ ላይ መስራቱን መጥቀስ ይሆናል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ተማሪ ስንታየሁ ታደሰ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲ ፋኩልቲ ፎክሎር (ባህል ጥናት) ት/ት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ (MA) የመመረቂያ ምርምር ስራውን "**የኢሬቻ በአል አከባበር በሎዴሄጦሳ ወረዳ**" በሚል ርዕስ እንደሚሰራ ተገልጦ ትብብር እንድናደርግ በደብዳቤ ቁጥር Reg. No ፎክ/32/2014 ቀን 28/07/2014ዓ/ም በተፃፈልን ደብዳቤ መሰረት የጠየቃችሁን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት ተማሪ ስንታየሁ ታደሰ ከወረዳችን የባህል ባለሞያዎች ጋር በመሆን የኢሬቻን በአል አከባበር በዶኒ አድባር ስር በሚከበረው ስርአተ ከበራ ላይ በቀን 01/17/2014 እና 01/17/2015 በመገኘት ለሁለት አመት በቦታው በአካል በመገኘት በጥልቀት ሲከታተልና እንዲሁም በቱሉ የንቦ፣ በጉዴልቻና በወረዳው ዋና ከተማ ሁሩታ ላይ መረጃዎችን ሲሰበስብ የቆየ መሆኑን እየገለጽን ከኛ ጋር በነበረበት ወቅት የተለያዩ እውቀቶችን ለኛም ያጋራና በበአሉ ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር ያከናወነ መሆኑን እየገለጽን ትምህርት ክፍሉ ይህንን ተገንዝቦ ያሰባሰበው መረጃውን ያሰባሰበው በትክክለኛው ቦታ ተገኝቶ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር!

Maakidaa Aliyyii Daatuu
ማክዳ አልይ ዳቱ
Gaafatamaa Waajjira Aadaa fi Turiizimii Aanaa Loodee Heexosaa
የሎዴ ሔጦሳ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ